# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ
## የተማሪ መጽሐፍ
## ፬(4)ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተስማማ

አስማምቶ አዘጋጆች

ትዘዘው አድጎ ደስታ
አልሃምዱ አብዶ አህመድ

የጥራት ክትትል

ፍሬህይወት አሠፋ ከበደ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለምዓቀፍ የልማት ድርጅት /United States Agency for International Development (USAID)/ በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮና በREAD TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የማስማማቱ ስራ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሆኖ የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም /General Education Quality Improvement Program (GEQIP) II /ተሸፍኗል፡፡

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2007 ዓ.ም. በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

ISBN: 978-99944-2-363-7

# ማውጫ

ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች ........ v

1ኛ ሳምንት ........ 1

2ኛ ሳምንት ........ 6

3ኛ ሳምንት ........ 10

4ኛ ሳምንት ........ 14

5ኛ ሳምንት ........ 19

6ኛ ሳምንት ........ 24

7ኛ ሳምንት ........ 28

8ኛ ሳምንት ........ 33

9ኛ ሳምንት ........ 37

10ኛ ሳምንት ........ 41

11ኛ ሳምንት ........ 45

12ኛ ሳምንት ........ 50

13ኛ ሳምንት ........ 54

14ኛ ሳምንት ........ 60

15ኛ ሳምንት ........ 65

16ኛ ሳምንት ........ 69
17ኛ ሳምንት ........ 73
18ኛ ሳምንት ........ 77
19ኛ ሳምንት ........ 81
20ኛ ሳምንት ........ 85
21ኛ ሳምንት ........ 89
22ኛ ሳምንት ........ 94
23ኛ ሳምንት ........ 99
24ኛ ሳምንት ........ 104
25ኛ ሳምንት ........ 108
26ኛ ሳምንት ........ 113
27ኛ ሳምንት ........ 118
28ኛ ሳምንት ........ 122
29ኛ ሳምንት ........ 126
30ኛ ሳምንት ........ 130

# ጠቃሚ መረጃ ለወላጆች

## መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ሕጻናትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የማዳመጥና የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ ለማበልፀግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ መርሃትምህርት አካል ነው:: መጽሐፉም ሲዘጋጅ መነሻ ያደረገው ሕጻናት ማንበብና መጻፍ እንዴት እንደሚማሩ የተደረጉ ጥናቶችንና የአማርኛ ቋንቋን መሠረታዊ ባህርያት ነው::

የዚህ የአፍመፍቻ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት እና መርሃትምህርት የተወሰኑ መሠረታዊ መርሆች የሚከተሉት ናቸው::

1. ሕጻናት እንግዳ ቃላትን ለማንበብና ቃላትን በተገቢ የፊደላት አሰዳደር ለመጻፍ፣ የቋንቋው ፊደላት የሚወክሏቸውን ድምፆች መማር ይጠበቅባቸዋል፤ ይህ ትምህርት የ1ኛና የ2ኛ ክፍሎች ሥርዓተ ትምህርትና መርሃትምህርት አካል ነው::

2. ሕጻናት በተቻለ መጠን ቃላትን ቀጥሎም ዓረፍተነገሮችን ማንበብ አለባቸው፤ እነዚህ ቃላትና ዓረፍተነገሮች በተማሯቸው ፊደላት የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፤
3. ሕጻናት በፍጥነት፣ በትክክልና ያለችግር እንዲያነቡና ራሳቸውን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በትክክልና በግልጽ ቋንቋ ለመግለጽ እንዲችሉ የማንበብ፣ የመናገርና የመጻፍ በርካታ ተከታታይ ልምምዶች ማድረግ አለባቸው፤

4. ሕጻናት አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የቃላቱንም ፍቺ አብረው መማር አለባቸው፤ በዚህም የሚያነቡትን ይረዳሉ፤ ቋንቋቸውንም በንግግርና በጽሑፍ በአግባቡ ይጠቀሙበታል፤

5. ሕጻናቱ ተረቶችን/ታሪኮችንና ሌሎች ጽሑፎችን አንብበው ለመረዳት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ማዳበር አለባቸው::

## ልጅዎን በቤት ውስጥ ይርዱ!

ወላጆች ልጆቻቸው ማንበብና መጻፍ እንዲማሩና ቋንቋውን በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ በቤት ውስጥ መርዳት ከሚችሉባቸው አጠቃላይ መንገዶች የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤

1. ለልጆችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን ይንገሯቸው።

2. ልጆችዎ ተረቶችን/ታሪኮችን እንዲናገሩ፣ ሁነቶችን መልሰው እንዲተርኩና ዜናዎችን እንዲለዋወጡ ይጠይቋቸው።

3. ልጆችዎን እርስዎ ስላነበቡላቸው ወይም ስለነገሯቸው ተረቶች/ታሪኮች ወይም ርዕሰጉዳዮች ያሏቸውን አስተያየቶች ለሌሎች እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው። ይህም የአንብቦ መረዳትንና በቋንቋቸው ራሳቸውን በአግባቡ የመግለጽ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል።

4. ለልጆችዎ ራስዎ ወይም ሌሎች ተረት/ታሪክ ያንብቡላቸው፤ ይህም የሚያነቡት ጽሑፍ በሌላ ሰው ሲነበብ ምን እንደሚመስል ለልጆቹ የማዳመጥ መልካም አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል፤ በራሳቸውም ለማንበብም ፍላጎት ያሳድርባቸዋል። ከልጆቹም ጋር ስላነበባችሁት ጽሑፍ ተወያዩ።

5. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጽሑፎችን ወይም ሌሎች ለደረጃቸው የሚመጥኑ ቀላል ጽሑፎችን እንዲያነቡ ያበረታቷቸው። ለማንበብ የሚቸገሩባቸውን ቃላትና ዓርፍተነገሮች እንዲያነቡ ያግዟቸው።

6. ልጆችዎ በራሳቸው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው።

7. ልጆችዎ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፤ ለምሳሌ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞቻቸው ደብዳቤ ወይም በዕለቱ ስለተፈጸመ አንድ ነገር ማስታወሻ በመጻፍ ስሜታቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው።

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

### የትምህርቱ ክፍሎች (ይዘቶች)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እያንዳንዱ ትምህርት በምልክት የተጠቆሙ ክፍሎች አሉት:: ጥቂት ክፍሎች በተወሰኑ ትምህርቶች ውስጥ ብቻ የሚከሰቱ ቢሆንም፣ ብዙዎቹ ክፍሎች ግን በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ ይገኛሉ፡

## የማዳመጥ ምንባብ

ይህ ክፍል የሚያተኩረው በአዳምጦ መረዳት ላይ ነው::

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- በመምህራቸው የሚነበበውን ተረት/ታሪክ ወይም መረጃ ሰጪ ጽሑፍ ያዳምጣሉ፤
- ርዕሱንና ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ/ያስባሉ፤
- ስላዳመጡት ምንባብ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በቃላቸው ወይም በጽሑፍ ስለምንባቡ ያላቸውን አስተያየት ለሌሎች ያጋራሉ::

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ስለምንባቡ የሚያስታውሱትን እንዲነግሯችሁ ይጠይቁ::
- የሚያስታውሷቸውን በጣም ተፈላጊ ቃላት ወይም ስለምንባቡ ያላቸውን ሀሳብ እንዲጽፉ ያድርጉ::
- ተረቱን/ታሪኩን እንዲያሳጥሩ ወይም መልሰው እንዲተርቱ/እንዲተርኩ ይጠይቁ::

## ማጣመር/መነጠል

ይህ ክፍል ቃላትን በማንበብና ወደተለያዩ አሀዶች በመነጠል ወይም በማጣመር ላይ ስለሚያተኩር፣ ልጆቹ ቃላቱን እንዲያነቡና በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲጽፉ ያግዛቸዋል:: በ4ኛ ክፍል ደረጃ ልጆች ፍቺ ባላቸው የቃላት አሀዶች (ምዕላዶች) ላይ የበለጠ ያተኩራሉ::

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፣

- ቃላትን "ማጣመር"፡- ቃላቱ የተመሠረቱባቸውን ፊደሎች ወይም የቃላቱን የተነጣጠሉ አሀዶች ለየብቻ ያነባሉ፤ መልሰውም አንድ ላይ ይሏቸዋል።
- ቃላትን "መነጠል"፡- ቃላቱን ያነባሉ፤ ቀጥለውም ወደፊደላት ወይም ወደአነስተኛ አሀዶች ይነጥላሉ።
- ፍቺ ያላቸውን የቃላቱን አሀዶች (ቅጥያዎች) ይለያሉ፤ ያነባሉ፤ ይረዳሉ።

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎን ቃላትን በተለይም በጽሑፉ/ በታሪኩ ውስጥ የሚገኙትን ረጃጅም ቃላት እንዴት እንደሚያጣምሩና እንደሚነጥሉ ይጠይቋቸው። ይሄ ለልጆቹ ጠቃሚ ልምምድ ነው።

## ግለንባብ

ይህ ክፍል ዓረፍተነገሮችን፣ አጫጭር ተረቶችን/ታሪኮችን ወይም መረጃ ሰጪ ምንባቦችን በማንበብ ላይ ያተኩራል። ከዚህ በተጨማሪም በአንብቦ መረዳትም ላይ ያተኩራል።

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፡-

- ግለንባቡን ያነባሉ፤
- ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ይመልሳሉ፤
- በግለንባቡ ላይ ይወያያሉ፤
- ስለምንባቡ በደረጃቸው ይጽፋሉ።

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- የዕለቱን ግለንባብ ይመልከቱና ልጆቹ እንዲያነቡ ይጠይቋቸው።
- የቀደሙ ግለንባቦችን ይመልከቱና እንዲያነቡ ይጠይቋቸው።
- ልጆችዎ በግለንባቡ ውስጥ ለማንበብ የሚቸገሩባቸው ማናቸውም ቃላት ካሉ ቃላቱን እንዲለዩዋቸውና ዓረፍተነገሩን መልሰው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው።
- ልጆችዎ ስለግለንባቡ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ይጠይቋቸው።

## ቃላት

ይህ ክፍል አዳዲስ ቃላትን በመማርና በመጠቀም እንዲሁም የቃላቱን ፍቺ ከዐውድ ፈልጎ በማግኘት ስልት (ዘዴ) ላይ ያተኩራል::

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ፣

- ከመምህራቸውና ከሚያዳምጡት ምንባብ አዳዲስ ቃላትን ይማራሉ::
- አዳዲስ ቃላትን ከብያኔዎቻቸው ወይም ከሌሎች ቃላት ጋር ያዛምዳሉ::
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ይሰጣሉ::
- ቃላቱን በዓረፍተነገር ውስጥ ይጠቀማሉ::
- በዓረፍተነገር ወይም በጽሑፍ ውስጥ ባላቸው ዐውድ መሠረት የቃላትን ፍቺ ለመወሰን ጥረት ያደርጋሉ::

### ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎ ስለተማሯቸው ቃላት እንዲናገሩ ይጠይቋቸው::

## መጻፍ

ይህ ክፍል ቃላትን፣ ዓረፍተነገሮችንና አንቀጾችን በመጻፍ ላይ ያተኩራል::

### በክፍል ውስጥ ልጆቹ:-

- ቃላትን መጻፍና በሥርዓቱ መሠረት የቃላቱን ፊደሎች መሰደር ይለማመዳሉ፤
- አጫጭር የቃል ጽሕፈትና የፊደል አሰዳደር ሙከራዎች ይወስዳሉ፤
- ሀሳባቸውን ለሌሎች ለማጋራት ዓረፍተነገሮችንና አጫጭር አንቀጾችን ይጽፋሉ::

## ወላጆች በቤት ውስጥ ልጆችን ለመርዳት፣

- ልጆችዎ የእጅ ጽሕፈታቸውን እንዲያሻሽሉ ፊደሎችንና ቃላትን እንዲገለብጡ ይጠይቋቸው፡፡
- ቃላትን በተገቢ የፊደል አሰዳደር ሥርዓት እንዲጽፉ ያለማምዱ፡፡
- ልጆችዎ በሚሳሳቱበት ጊዜ ያበረታቷቸው፡፡
- በተጨማሪም ልጆችዎ ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት አጫጭር ታሪኮችን/አንቀጾችን በመጻፍ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

## ግለንባብ

### ታታሪዎቹ ልጆች



በአንድ አካባቢ አስቴርና ሄኖክ የሚባሉ ጓደኛሞች ነበሩ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። የሚኖሩበት አካባቢ ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈነ ነበር። በአካባቢው የነዋሪዎች ቁጥር በመጨመሩ ጫካው ለእርሻ ሥራ ቀስ በቀስ ተመነጠረ፤ ተጨፈጨፈ።

በዚህም ምክንያት በአካባቢው ሙቀትና ድርቅ ተስፋፋ። አንድ ቀን ሄኖክና አስቴር በድንገት መስቀለኛ መንገድ ላይ ተገናኙ። አስቴር ከፊቷ ላይ ላብ ጠብ ጠብ ይላል። “ሄኖክ እንዴት ነህ?” አለችው። ሄኖክም፣ “ደህና ነኝ፤ አንቺ እንዴት ነሽ?” አላት። “ሙቀት እኮ አቀለጠን!” አለችው። “ልክ ነሽ” አላት። “ሙቀቱን የምንቀይርበት መላ ይኖር ይሆን?” አለችው። “አይጠፋም፤ እስኪ ባለሙያ እናማክራለን” አላት። ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ።

በማግስቱ ተገናኙ። ተያይዘው ወደአካባቢው የደን ልማት ቢሮ ሄዱ። ከቢሮው እንደደረሱ ጉዳዩ የሚመለከተውን ባለሙያ አገኙ። ወደቢሮው ገቡ። “እርስዎን ፈልገን ነበር” አሏቸው። “ለምን ጉዳይ ነው?” አሏቸው። አስቴር ቀደም ብላ፣ “የአካባቢያችን ሙቀት በመጨመሩ፣ መፍትሔ ፍለጋ ነው የመጣነው” አለቻቸው። አቶ አወቀም “መልካም፣ የሙቀት መጠን መጨመር የዓለምም ችግር እየሆነ መጥቷል፤ ለዚህ አሳሳቢ ችግር አንደኛው ምክንያት የአደጉት አገሮች በካይ መርዛማ

ጭስ ወደህዋ መልቀቃቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ የደን መጨፍጨፍ ነው፤ ለዚህም መፍትሔው፣ ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ መጠቀምና ደን ማልማት ነው" አሏቸው።

በሚቀጥለው ቀን ተገናኝተው የአካባቢያቸውን ነዋሪ ለስብሰባ ጠሩ። የአካባቢያቸውን የሙቀት መጨመር መፍትሔ በሚመለከት አወያዩ። ህዝቡን አሳመኑ። ደን ማልማትና መንከባከብ እንዳለባቸው ተስማሙ። ከግብርና ጽ/ቤት ችግኞች እንዲሰጣቸው ጠይቀው ተሰጣቸው። ችግኞቹን በተራቆተው አካባቢ ተከሏቸው። ችግኞቹን ያለመሰልቸት ተንከባከቡ፤ ጠበቁ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ማየት ቻሉ፤ በተገኘው ውጤት የአካባቢው ህዝብና እነአስቴር ተደሰቱ።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## የአየር ንብረት

### ቃላት

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።

ሀ. ውርጭ ለ. ቅዝቃዜ ሐ. ነፋሻ መ. ብርድ

### መነጠል

የባለቤትነት አመልካች ቅጥያዎችን በምሳሌው መሠረት ነጥላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- 1. ቤቱ = ቤት - ኡ 2. ቤቷ = ቤት - ዋ

ሀ. መጽሐፉ ሐ. አሻንጉሊቷ ሠ. ደረቱ

ለ. ቦርሳው መ. ችግኙ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

የሚከተለውን ጥያቄ በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

የጽሑፉ ባለታሪኮች እነማን ናቸው?

### ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. የአየር ንብረት ለ. መላ ሐ. ህዋ

### መጻፍ

የተራቆተ መሬት መልሶ እንዲያገግም ምን መደረግ እንዳለበት ተገቢ ስርዓተነጥብ በመጠቀም ስድስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### የአየር ንብረት

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ጻፉ።

ሀ. በምንባቡ የተገለጹት የአየር ንብረቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ውርጭ በብዛት የሚታይባቸው አካባቢዎች የትኞቹ ናቸው?

ሐ. ያዳመጣችሁትን ጽሑፍ መልእክት በሦስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

### ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ስሩ።

ሀ. ከፍተኛ ለ. ተመቻቸ ሐ. ተስማሚ መ. አዝርእት

### መነጠል

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ።

ሀ. በጉ ለ. ጠረጴዛው ሐ. ወፉ መ. ተማሪው

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

1. የሚከተለውን ጥያቄ በቃላችሁ መልሱ።

   ታታሪነት በምን ይገለጻል?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

   ሀ. "መስቀለኛ መንገድ" ምን ማለት ነው?

   ለ. ባለታሪኮቹ የሚኖሩት የት ነበር?

### ቃላት

የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. መላ ለ. መፍትሔ ሐ. ማሳመን መ. ፈነደቀ ሠ. በካይ

## መጻፍ

ካነበባችሁት ምንባብ የተገነዘባችኋቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ተገቢ ስርዓተነጥብ በመጠቀም በራሳችሁ አባባል በአራት ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ አንብቡ።

## ግለንባብ

# ሳይቃጠል በቅጠል

ደኖች ለሰው ልጅ በርካታ ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ። የአካባቢን የአየር ንብረት ይጠብቃሉ፤ ለዝናብ መዝነብ ምክንያት ይሆናሉ፤ የከርሰ ምድር ውሃን ጠብቀው ያቆያሉ፤ የአፈር መሸርሸርን ይከላከላሉ፤ የቅጠላቸው ብስባሽ ለማዳበሪያነት አገልግሎት ይውላል። የፀሐይን ሙቀት ይከላከላሉ።

ይሁን እንጂ፣ ጠቀሜታቸውን በውል ባልተገነዘቡና ኃላፊነት በማይሰማቸው ግለሰቦች ደኖች ይጨፈጨፋሉ፤ ይቃጠላሉ፤ ይመነጠራሉ። ህግ ሳይፈቅድላቸው በራሳቸው ፍላጎት ህገወጥ ሰፈራ ያካሂዳሉ። የመነጠሩትን መሬት ቁልቁል በማረስ ለም አፈሩ በጎርፍ ታጥቦ እንዲሄድ ያደርጋሉ። እነዚህ አሉታዊ ተግባራት ለምግብ እህል ምርት መቀነስ ሰበብ ሲሆኑ መሬቱ ከነአካቴው እህል እንዳይበቅልበት ያደርጋሉ። እነዚህ ሰውሠራሽ ጎጂ ተግባራት አካባቢን ወደበርሃማነት ይቀይራሉ። የምግብ እህል እጥረትን፣ ሞትንና ስደትንም ያስከትላሉ።

ከብቶችን በደኖች አካባቢ ለግጦሽ ማሰማራትም ሌላው ችግር ነው። ከብቶች በደኖች አካባቢ ሲሰማሩ ለጋ ተክሎችን ይሰባብራሉ፤ የዛፎችን ቅጠሎች ያራግፋሉ። በዚህ የተነሳ የደን ሃብት ይመናመናል። የደን ሃብት መመናመን ደግሞ ለዱር እንስሳት መሰደድ ምክንያት ይሆናል። ስለዚህ “ሳይቃጠል በቅጠል” እንደሚባለው ድርጊቱን ከወዲሁ ማስቆም የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## አረንጓዴው ዘመቻ



ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ደኖች ሲቃጠሉና ሲመነጠሩ የሚጎዱት እነማን ናቸው?

ለ. ደን አገገመ የምንለው ምን ዓይነት ለውጥ ሲያሳይ ነው?

### ቃላት

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቺ በቃላችሁ ስጡ፡፡

ሀ. አሳሳቢ ለ. ተሣታፊ ሐ. በነቂስ መ. ገጠማቸው

### መነጠል

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ሜዳዎች ለ. ችግሮች ሐ. ክፉዎች መ. ጎበዞች

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ህገወጥ ሰፈራ ምን ያስከትላል?

ለ. አካባቢን ከጎጂ ልማዳዊ ተግባራት ነጻ ማድረግ ምን ጠቀሜታ አለው?

ሐ. ከብቶችን በደኖች አካባቢ ለግጦሽ ማሰማራት ምን ችግር ያመጣል?

## ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ::

   ሀ. ጠቀሜታ ለ. ሰፈራ ሐ. መጠበቅ

2. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት የሚያስተላልፉትን መልእክት በቃል ግለጹ::

   ሀ. ደን ጭፍጨፋ ለ. ቃጠሎ ሐ. ህገወጥ ሰፈራ መ. መሰደድ

## መጻፍ

“የደን ጥቅም” በሚል ርእስ ተገቢ ስርዓተነጥቦችን በመጠቀም አንድ አንቀፅ ጻፉ::

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### አረንጓዴው ዘመቻ

## ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በቃላችሁ ስጡ::

   ሀ. ባለሙያ ለ. ማሠማራት ሐ. መከለል መ. ማጠቃለል

2. ለጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃላችሁ ስጡ::

   ሀ. የተመናመነን ደን ወደ ቀድሞው ለመመለስ መከናወን ያለባቸው ተግባራት ምን ምን ናቸው?

   ለ. የምንባቡ ዋና መልእክት ምንድን ነው?

## መነጠልና ማጣመር

1. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ::

   ሀ. ገበሬዎች ለ. በረሃዎች ሐ. ሰነፎች መ. ጠይሞች

2. ዋናውን ቃልና ቅጥያውን አጣምራችሁ ፃፉ::

ሀ. ድመት-ኦች ለ. ከተማ-ዎች ሐ. ረባሽ-ኦች ሐ. አሞራ-ዎች

3. መደበኛ የሆነውን ቃል ከሥሩ አስምሩበት::

ምሳሌ:- አልበልቸም/<u>አልበላሁም</u>

ሀ. አልጣፈም/አልጻፈም
ለ. አልመጥቶም/አልመጣም
ሐ. ጬስ/ቄስ
መ. በቅሎ/በእሎ
ሠ. ዴሞ/ደግሞ
ረ. ክፈተኝ/ክፈትልኝ

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ በመወያየት መልሶችን በቃላችሁ ስጡ::

ሀ. ትምህርት በአንድ ህብረተሰብ ላይ የሚያመጣው ለውጥ ምንድን ነው?
ለ. ከአደጋ በፊት የሚደረግ ጥንቃቄ ለምን ይጠቅማል?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃላችሁ ስጡ::

ሀ. በምንባቡ ውስጥ ያሉ ጎጂ ተግባራትን ግለጹ::
ለ. ከምንባቡ ምን ተማራችሁ?

## ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ::

ሀ. መነጠረ ለ. ቁልቁል ሐ. መሽርሽር መ. ብስባሽ

2. የሚከተሉትን ሐረጋት ፍቻቸውን ለጓደኞቻችሁ በቃላችሁ ግለጹ::

ሀ. የፀሐይ ሃሩር ለ. የደን መመናመን

## መጻፍ

በቡድን ተወያይታችሁ "የደኖች መጨፍጨፍ የሚያስከትለው ጉዳት" በሚል ርእስ አንድ አንቀፅ ጻፉ::

## ግለንባብ

### ሠራተኞቹ



ቦጋለና ፋጡማ የመንግስት ሠራተኞች ናቸው። በባህልና ቱሪዝም ቢሮ ለብዙ ዓመታት ሠርተዋል። ከቱሪዝም የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ በሚገባ ያውቃሉ። በየዓመቱ በርካታ የውጭ ሃገር ጎብኚዎች ሲመጡ አይተዋል። በሥራ ዘርፋቸው ምክንያት በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ተዘዋውረዋል። "ደኖችንና እንስሳትን በእንክብካቤ ይዞ በዘላቂነት መጠቀም" የሚለውን ሃሣብ ለሁሉም ሰው በማዳረስ ብዙ ሠርተዋል። በሄዱበት ሁሉ ስለደኖችና ስለፓርኮች አጠባበቅ ያስተምራሉ።

ስለኢትዮጵያ ብሔራዊ ፓርኮችና ደኖች አስፈላጊነት አዘውትረው ያስረዳሉ። በሃገራችን በርከት ያሉ ጥብቅ ደኖችና ፓርኮች መኖራቸውንም ያስተዋውቃሉ። የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ፣ የነጭ ሣርና የአዋሽ ብሔራዊ ፓርኮች እንክብካቤ ከሚያስፈልጋቸው መካከል ጥቂቶቹ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ጥብቅ ደኖችን መንከባከብ ዘላቂ ገቢ ከቱሪስቶች ለማግኘት እንደሚያስችልም ያስተምራሉ። ፓርኮችንና ደኖችን ለመንከባከብ ከሚያስችሉት መንገዶች አንዱ የቤት እንስሳትን በደኖች አካባቢ አለማሰማራት መሆኑን ያስገነዝባሉ። በአጠቃላይ ከደኖችና ፓርኮች ተጠቃሚ ለመሆን ደኖችን ከንክኪ ነጻ አድርጎ መከላከልና መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን አዘውትረው ይገልፃሉ።

በጥረታቸው መሰረት በአሁኑ ሰዓት በርካታ ቱሪስቶች ወደሃገራችን እየገቡ ነው። ጥረታቸውም እንደቀጠለ ነው። በደኖችና ፓርኮች አካባቢም ለውጦችን በዐይናቸው ማየት ችለዋል። እየሠሩት ባለው ጉዳይም መርካት ጀምረዋል።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



## እጽዋትንና እንስሳትን መንከባከብ

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተለውን ጥያቄ በቃላችሁ መልሱ።

የዱር እንስሳት ለአንድ አገር ምን ጥቅም ይሰጣሉ?

### ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።

ሀ. ብርቅዬ ለ. ዝርያ መ. መንከባከብ ሠ. ማደን

### ማጣመር

በሚከተሉት ቃላት ላይ "-ኦች" ወይም "-ዎች" በመጨመር ወደብዙ ቁጥር ቀይራችሁ ጻፉ።

ሀ. ብልህ ለ. ቀይ ሐ. መሪ መ. ጀግና ሠ. አዋቂ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ።

ሀ. የዱር እንስሳትን አለማደን ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ፓርኮች ለሃገራችን የሚሰጡት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ሐ. የምንባቡ ዋና መልእክት ምንድን ነው?

## ቃላት

በ"ሀ" ክፍል ላሉት ቃላት ፍቻቸውን ከ "ለ" ክፍል መርጣችሁ አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዘላቂ | ሀ. ቅያሬ |
| 2. መከለል | ለ. ተደሰተ |
| 3. በርካታ | ሐ. የማያቋርጥ |
| 4. ረካ | መ. ማጠር |
| 5. ለውጥ | ሠ. አያሌ |

## መጻፍ

"የዱር እንስሳትን የመንከባከብ አስፈላጊነት" በሚል ርዕስ ሁለት አንቀጾችን ጻፉ:: በጽሑፋችሁ ውስጥ ትክክለኛ ስርዓተነጥቦችን ተጠቀሙ::

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### እጽዋትንና የዱር እንስሳትን መንከባከብ

## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ተቃራኒ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ::

ሀ. ጨፈጨፈ ለ. ወጪ ሐ. ማጎልበት

## መነጠል

በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ::

ምሳሌ:- አገሮች አገር - ኦች

ሀ. ቢሮዎች ሐ. ጊደሮች

ለ. መንደሮች መ. ቀዮች

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ መልስ ስጡ።

ሀ. ቦጋለና ፋጡማ የሚሠሩት የት ነው?

ለ. ደኖች እንዳይጨፈጨፉ ምን መደረግ አለበት?

ሐ. ጥብቅ ደኖችን መንከባከብ ለምን ይጠቅማል?

## ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።

ሀ. ጥረት ለ. ወቅት ሐ. ጥብቅ ደን

2. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. ቅርስ ለ. ብሔራዊ ሐ. አሰረፀ መ. መሠረታዊ

3. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡ።

ሀ. በአርባ ምንጭ አካባቢ የሚራቡ አዞዎች አሉ።

ለ. እንስሳት ወደጎረቤት አገሮች ይሰደዳሉ።

ሐ. ጥብቅ ደኖችን መንከባከብ ያስፈልጋል።

መ. ደኖችን ከመጨፍጨፍ መቆጠብ አለብን።


## መጻፍ

"የደኖች እንክብካቤ ጥቅም" በሚል ርዕስ ተገቢ ስርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሁለት አንቀፆችን ጻፉ።

## 4ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎች



የመጓጓዣ ዓይነቶች ባህላዊና ዘመናዊ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ባህላዊ መጓጓዣዎች ታንኳ፣ አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎና ግመል ናቸው፡፡ ከታንኳ በስተቀር ባህላዊ መጓጓዣዎች ጉልበት ለማግኘት ፉርሽካ፣ ጥራጥሬና ሳር ይመገባሉ፡፡ ታንኳ ግን ምንም ዓይነት ነዳጅ አይጠቀምም፡፡ ሁሉም ባህላዊ መጓጓዣዎች ሰውና እቃ ለማጓጓዝ የሚወስድባቸው ጊዜ ረዥም ነው፡፡

ዘመናዊ መጓጓዣዎች የየብስ፣ የአየርና የውሀ ተብለው በሶስት ይከፈላሉ፡፡ የየብስ ዘመናዊ መጓጓዣዎች መኪና ታክሲ፣ ባጃጅ፣ ብስክሌት፣ አውቶቡስና ባቡር ናቸው፡፡ የአየር ዘመናዊ መጓጓዣዎች ደግሞ አውሮፕላን፣ ሄሊኮፕተር፣ ጀትና የመሳሰሉት ሲሆኑ ዘመናዊ የውሀ መጓጓዣዎች ደግሞ መርከብና ጀልባ ናቸው፡፡ ዘመናዊ መጓጓዣዎች መንገድ፣ ሀዲድ፣ የአየር ማረፊያ፣ ማኮብኮቢያና ውሃ ስለሚያስፈልጋቸው ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃሉ፡፡

✶✶✶“ከወጪ ቁጠባ አንጻር የሚሻለው ዘመናዊ ወይስ ባህላዊ መጓጓዣ ነው? የትኛውን የመጓጓዣ ዓይነት ትመርጣላችሁ?”✶✶✶


በዘመናዊ መጓጓዣዎች መካከል በአገልግሎት አንድነትና ልዩነት አለ፡፡ ለምሳሌ አውሮፕላን፣ ጀትና ሄሊኮፕተር ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይደርሳሉ፡፡ ባቡር ደግሞ ዘግይቶ ይደርሳል፡፡ መርከብ ግን ከሁሉም ባነሰ ፍጥነት ይጓዛል፡፡

ዘመናዊ መጓጓዣዎች በጥንቃቄ ካልተያዙ በሰዎችና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ በአንፃሩ ባህላዊ መጓጓዣዎች የሚያደርሱት ጉዳት የዘመናዊ መጓጓዣዎችን ያህል የከፋ አይደለም፡፡

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

ጥረትና ስኬት



ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. የእንጨት ሥራ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ከመንግስት አካላት ምን ተሰጣቸው?

### ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን በፅሁፍ ስጡ።

ሀ. ስኬት ሐ. ማስገረም ሠ. ሽልማት

ለ. አነስተኛ መ. ደስታ ረ. ቁጭት

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያቸውን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ አሳዩ።

ሀ. ትምህርታቸው ሐ. ድርጅትሽ ሠ. ጓደኞቻቸው

ለ. ቤታችሁ መ. ወንበሮችህ ረ. ሠፈራችን

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ።

ሀ. የየብስ መጓጓዣ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ዘመናዊ መጓጓዣ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

ሐ. በባህላዊና በዘመናዊ መጓጓዣ ዓይነቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ጽፋችሁ አንብቡ።

   ሀ. ፋርሽካ　　ሐ. ጥራጥሬ

   ለ. ማኮብኮብ　　መ. አስከተሉ

2. የሚከተሉትን የመጓጓዣ ዓይነቶች አገልግሎት በቡድን በመወያየት በቃላችሁ ግለጹ።

   ሀ. ታንኳ　　ሐ. መርከብ　　ሠ. ባቡር

   ለ. ጀልባ　　መ. ግመል　　ረ. መኪና

## መጻፍ

ከምትወዱት የመጓጓዣ ዓይነት አንዱን መርጣችሁ፣ ለምን እንደወደዳችሁት ተገቢ ስርዓተነጥብ በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ አንብቡ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ጥረትና ስኬት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሁለቱ እህትና ወንድም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኃላ በምን የስራ ዘርፍ ተሰማሩ?

ለ. ባለታሪኮቹ የድርጅታቸውን ምርት ይዘው የት ሄዱ?

## ቃላት

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ከስራቸው የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረግ ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡- ኀደኛማኞቹ በሠሩት ሥራ ለሠፈራቸው ወጣቶች አርአያ ሆኑ። (ምሳሌ)

ሀ. ስለሚያቋቁሙት ድርጅት ማውጣት ማውረድ ጀመሩ።

ለ. ልጆቹ የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ ከድርጅቱ ተቀበሉ።

ሐ. የእንጨት ስራ ድርጅት ማቋቋም ፈለጉ።

## መነጠል

1. ባለንብረትን አመልካችን ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ አሳዩ።

አልጋህ፤ አልጋሽ፤ ጠረጴዛችን፤ ወረቀቴ ፤ ወረቀታችሁ

2. በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ቃላት "ቅፅል ፣ ስም ፣ ግስ" በማለት ጻፉ።

ምሳሌ፡- ትልቅ ቁምሳጥን ሠሩ ።

| ቅፅል | ስም | ግስ |
|---|---|---|
| ትልቅ | ቁምሳጥን | ሠሩ |

ሀ. ሠሬ አልጋ ገዛ።

ለ. ትንሿ ወፍ ታምራለች ።

ሐ. ብዙ መኪና አሏቸው።

መ. ትልቁ ወንበር ተሰበረ።

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. በቡድን ሆናችሁ በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ።

ከባህላዊና ከዘመናዊ መጓጓዣዎች የቱን ትመርጣላችሁ? ለምን?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት አጫጭር መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. ፈጣን የመጓጓዣ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ረጅም ርቀት በእግር መሄድን እንዴት ማስቀረት ይቻላል?

ሐ. ከፍተኛ ወጪ የማይጠይቀው የመጓጓዣ ዓይነት የትኛው ነው?

መ. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች የሚንቀሳቀሱት በምንድን ነው?

## ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሠርታችሁ አንብቡ።

ሀ. ጋሪ ለ. ንብረት ሐ. ሃዲድ መ. ሸቀጥ

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ በቃላችሁ አብራሩ።

ሀ. የከብት መኖ　　ለ. አየር ማረፊያ　　ሐ. መመልከት


## መጻፍ

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ተገቢ ስርዓተነጥቦችን ተጠቅማችሁ እንደገና ጻፏቸው።

ሀ. ውይ ለምን መጣሽ
ለ. ፈተና ስለደረሰ ማንበብ አለብን
ሐ. መምህሩ ለምን አታጠናም አለው
መ. ማንበብ መጻፍ ማዳመጥና መናገር የቋንቋ ክሂሎች ናቸው

## ግለንባብ

### ሐናና አየለ



ሐናና አየለ ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው። የህብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት በጣም ይወዳሉ። በትምህርቱም ጥሩ ውጤት ያስመዘግባሉ። በክፍል ውስጥ የተማሩትንና ወደፊት የሚማሩትን በማንበብ ይረዳዳሉ። አየለ ያወቀውን ለሐና ያስረዳታል። ሐና በበኩሏ የምታውቀውን ለአየለ ታስረዳዋለች። ከነሱ አቅም በላይ የሆነ ጥያቄ ሲገጥማቸው መምህራቸውን ይጠይቃሉ።

ነገር ግን ሁለቱም ስለባህላዊ መጓጓዣ የነበራቸው እውቀት ውስን ነው። ይህን የእውቀት ውስንነት ለመሙላት አሰቡ። ቁጭ ብለው በሚጠያየቁበት ዛፍ ስር ተገናኙ። “አሁን መጠያየቅ እንችላለን” አለች ሐና። አየለ ጥያቄውን አስቀደመ።

“ባህላዊ መጓጓዣ ምንድን ነው?” አላት። ሐናም፣ “ዕቃዎችና ሰዎች የሚጓጓዙበት ዘዴ ነው” ብላ መለሰችለት። ሐናም በተራዋ፣ “ባህላዊ መጓጓዣ ምን ጠቀሜታ አለው?” ብላ አየለን ጠየቀችው። አየለም፣ “ከስር መሰረቱ ጀምሮ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የነበረው፣ አሁንም ያለው፣ ሰዎች ወደገጠር፣ ወደከተማ፣ ለመመላለስ በሰፊው የሚጠቀሙበት፣ የግብርና ምርታቸውን የሚያጓጉዙበት ነው” በማለት መለሰላት።


አየለም በተራው፣ “ባህላዊ መጓጓዣ በስንት ይከፈላል?” አላት። ሐናም፣ “የየብስና የውሀ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የየብስ መጓጓዣ የጋማ ከብቶችን (አህያ፣ ፈረስና

በቅሎን) ያጠቃልላል። በአሁኑ ሰዓትም ለአርሶአደሩ ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው” ብላ መልስ ሰጠችው። ቀጥላም፣ “ግመል የበርሃ መርከብ የተባለችው ለምንድን ነው?” ብላ ጠየቀችው። “ግመል በበረሃ አካባቢ ያለውሃ ለረጅም ጊዜ ስለምትቆይ ነው። እግረመንገዬን ስለጋሪ ልንገርሽ። ጋሪ በፈረስ ወይም በበቅሎ እየተጎተተ ሰውንና ዕቃን የሚያጓጉዝ ነው” አላት። ከዚያም አየለ “ባህላዊ የውሃ ላይ መጓጓዣ ምንድን ነው?” አላት። ሐናም፣ “ባህላዊ የውሃ ላይ መጓጓዣ ታንኳ ሲሆን፣ ሰዎች ዓሣ ለማጥመድ የሚጓጓዙበት ነው” ብላ መልስ ሰጠችው። በዚህ ዓይነት የነበረባቸውን የእውቀት ክፍተት በጋራ በመወያየት አሟሉ። በውይይታቸው ሁለቱም ተጠቃሚ በመሆናቸው ደስተኛ ነበሩ።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነትና ጥቅሙ



**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ፡፡**

ሀ. በአካባቢያችሁ ጋሪዎችን የሚጎትቱ እንስሳት የትኞቹ ናቸው?

ለ. ከባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ሁለቱን ጥቀሱ፡፡

### ቃላት

**ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ፡፡**

ሀ. ማጥመድ ለ. ጎተተ ሐ. የብስ መ. አመረተ ሠ. ጋለበ

### መነጠልና ማጣመር

1. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን መድረሻ ቅጥያዎች ነጥላችሁ ጻፉ፡፡

   ሀ. ወረዳዎችን ሐ. ደብተራቸውን ሠ. ታንኳዎች

   ለ. ዘመኖች መ. መልመጃዎች ረ. ወሮች

2. የባለንብረትነት አመልካች ቅጥያዎች ያሏቸው አምስት የተለያዩ ቃላትን ጽፋችሁ አንብቡ፡፡

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ አጫጭር መልሶችን ስጡ፡፡**

ሀ. “የዕውቀት ውስንነት” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በገጠር አካባቢ የጋማ ከብቶች አለመኖር የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?

ሐ. ባለታሪኮቹ ችግራቸውን የፈቱት በምን ዓይነት መንገድ ነው?

መ. የባህላዊ መጓጓዣዎች የሚሰጧቸውን ጥቅሞች ግለጹ::

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት በዓረፍተነገሮች ውስጥ አስገብታችሁ በገቡበት ዐውድ መሠረት ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ::

   ሀ. ቀደመ ለ. መወሰን ሐ. ለመደች መ. ተራ

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ::

   ምሳሌ ወጣ - ገባ

   ሀ. አገኘ ለ. ቀደመ ሐ. ገጠመ መ. ዘመናዊ

## መጻፍ

ሐናና አየለ ያከናወኗቸውን መልካም ተግባራት በአምስት ዓረፍተነገሮች በጽሑፍ ግለጹ::

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነትና ጥቅም

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ::

ሀ. ባህላዊ የውሃ ላይ የመጓጓዣ ዓይነት ምን ተብሎ ይጠራል?

ለ. በበቅሎና በግመል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

## መነጠልና ማጣመር

1. “ቅፅል፣ ስም፣ ግስ” ያላቸው አራት አጫጭር ዓረፍተነገሮችን ሥሩ::
2. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ቅጥያቸውን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ::

   ሀ. ዓይነቶች ለ. እቃዎች ሐ. ሥርዓቶች

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።

   ሀ. ሰዎች እርስበርሳቸው ለመማማር የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?

   ለ. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ባህላዊ ያሰኛቸው ምንድን ነው?

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ በጽሑፍ ስጡ።

   ሀ. በደጋማ አካባቢዎች በብዛት የሚያገለግል የጋማ ከብት ምን ተብሎ ይጠራል?

   ለ. ታንኳ ለምን ያገለግላል?

### ቃላት

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን ከመዝገበቃላት ፈልጋችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።


ሀ. አጠመዱ ለ. እግረመንገድ ሐ. ስር ሰደደ መ. መጐተት

### መጻፍ

ከባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች አንዱን መርጣችሁ ስለአገልግሎቱ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ አንብቡ።

## ግለንባብ

### ታሞ ከመማቀቅ...



በዓለም ላይ የሰውን ልጅ ሕይወት በመቅጠፍ ቀዳሚነቱን የያዘው የትራፊክ አደጋ ነው፡፡ በየዕለቱ አደጋ ሳይደርስ የሚውልበት ቀን የለም፡፡ በንብረትና በሕይወት ላይ የሚያደርሰው ጉዳትም ቀላል አይደለም፡፡ የትራፊክ አደጋ በርካታ ሰዎችን ያለጧሪ ያስቀራል፤ ለአካል ጉዳትም ይዳርጋል፡፡ ለሥነልቦናዊ ጉዳትም ያጋልጣል፡፡

ለትራፊክ አደጋ አንደኛው ምክንያት ራሳቸው አሽከርካሪዎች ናቸው፡፡ አሽከርካሪዎች የመንገድ ምልክቶችን እያዩ፣ በተፈቀደ ፍጥነት መንዳት ሲገባቸው፣ ከልክ በላይ በመፍጠን ለጉዳት ይዳርጋሉ፡፡ በከፍተኛ ፍጥነት የሚያሽከረክር ሾፌር በድንገት ከፊት ለፊቱ እንስሳ ወይም ሰው ቢገባበት መኪናውን መቆጣጠር አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት ራሱንና ሌሎችን ሊጎዳ ይችላል፡፡

አልኮል ጠጥቶ መንዳት የመኪና መገልበጥንና መጋጨትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በዚህም በርካታ ሰዎች ይሞታሉ፤ አጥንታቸው ይሰበራል፤ እግራቸው ይቆረጣል፤ ንብረታቸው ይወድማል፡፡ በዚህም ሳቢያ ቤተሰቦቻቸው ይበተናሉ፤ ለስደትም ይዳረጋሉ፡፡

ስለሆነም የትራፊክ አደጋን ለመከላከል በቅድሚያ መንገዶችን ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የትራፊክ ምልክቶችንም በተገቢው ሁኔታ መትከል ይገባል፤ ሾፌሮችንም ማሠልጠንና መቆጣጠር ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ከመጠን በላይ አለመጫን፣ ለእግረኛ ቅድሚያ መስጠት፣ ከሾፌር የሚጠበቁ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እግረኞችም ቢሆኑ ሁልጊዜ የመንገዱን ግራ ጠርዝ መስመር ይዘው መሄድ ይኖርባቸዋል፡፡

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

መሬምና ሰሎሞን

### ቃላት

በቅንፍ ውስጥ ካሉት ቃላት መካከል ተስማሚውን ቃል መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ::

ሀ. ፖሊሱ የአደጋው መንስኤ ምን እንደሆነ ________::
(አጣራ፣ ለካ፣ ታዘበ::)

ለ. የአደጋው ደረጃ በጣም ________ ነው::
(አደገኛ፣ ክፉኛ፣ ከባድ)

ሐ. መንገዱ ________ የበዛበት በመሆኑ ለተሽከርካሪ አይመችም::
(ጥምዝ፣ ተጣጣፊ፣ ጠመዝማዛነት)

### መነጠል

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ዋና ቃሉንና ቅጥያውን ነጥላችሁ ጻፉ::

ምሳሌ ልጆቻችን ልጅ - ኦች - ኣችን

ሀ. ላሞችሽ ለ. ዘመዶቻችሁ ሐ. ተማሪዎቹ መ. ዶሮዎቹ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

በምንባቡ መሠረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ::

ሀ. የትራፊክ አደጋ በሰዎች ላይ ሲደርስ ምን ያስከትላል?

ለ. በከፍተኛ ፍጥነት የሚያሽከረክር ሾፌር ምን ሊገጥመው ይችላል?

ሐ. አልኮል ጠጥቶ መንዳት የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?

## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በጽሑፍ ፍቺ ስጡ።

ሀ. አጋለጠ ለ. ንብረት ሐ. ጥራት መ. ጠርዝ

## መጻፍ

በአካባቢያችሁ የሰማችሁትን ወይም የተመለከታችሁትን የትራፊክ አደጋ ያስከተለውን ጉዳት በሚመለከት ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጻፉ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### መሬምና ሰሎሞን

የሚከተሉትን ጽንሰሐሳቦች በራሳችሁ አባባል በጽሑፍ ግለጿቸው።

ሀ. የአደጋውን መንስኤ አጣሩ።

ለ. በጉጉት ወደቀ።

ሐ. አልፎ አልፎ ለሽርሽር ይወጣሉ።

መ. የትራፊክ ደንብ ማክበር

## ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።።።

ሀ. ተቆረጠ ለ. ሽርሽር ሐ. ተጠጉ መ. ተጋጩ

## መነጠልና ማጣመር

1. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ብዙ ቁጥርና ባለንብረት አመልካች ቅጥያዎችን ነጣጥላችሁ ጻፉ።

ሀ. መፅሐፎቻቸው

ለ. ደብተሮችህ

ሐ. እርሳሶችሽ

መ. ቤቶቻችን

2. ከዚህ በታች ካሉት ቃላት መርጣችሁ በማጣመር ሦስት ዓረፍተነገር ጻፉ።

| |
|---|
| ቤት፣ ጠባብ፣ አልወድም፣ ሰላም፣ መልካም፣ ጉረቤት፣ ይሰጣል፣ ልጅ፣ ጠይሙ፣ ሄደ |

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።
   ሀ. "ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ" ከሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ምን እንማራለን?
   ለ. በጠንቃቃነትና በግዴለሽነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።
   ሀ. "በርካታ ሰዎችን ያለረዳት ማስቀረት" ለሚለው አባባል ከምንባቡ አቻ ፍቺ ፈልጋችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ።
   ለ. "ከልክ በላይ መጫን" ማለት ምን ማለት ነው?
   ሐ. እግረኞች ከቦታ ወደቦታ ሲንቀሳቀሱ የትኛውን የመኪና መንገድ ጠርዝ ይዘው ቢሄዱ ይሻላል? ለምን?

## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ግለጹ።

ሀ. አደጋ ለ. መገልበጥ ሐ. መበተን መ. ድንገት ሠ. መንዳት

## መጻፍ

"ታሞ ከመማቀቅ..." የሚለውን ምንባብ የመጨረሻውን አንቀጽ ሀሳብ በራሳችሁ አባባል እንደገና ጻፉት።

# 7ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ሾፌሩ

ሾፌሩ የሚተዳደረው መለስተኛ አውቶብስ በማሽከርከር ሥራ ነው። በሙያው ጎበዝ ነው። "አነስተኛ አውቶብስ" ማሽከርከር ከጀመረ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ሆኖታል።

አንድ ቀን በጧት ተነሥቶ ወደመናኸሪያው በእግሩ ሄደ። ከመናኸሪያው ገብቶ መኪናውን አስነሣ። ረዳቱም በቦታው ነበር። ሾፌሩም "ተሳፋሪ ጥራ!" አለው። ረዳቱም፣ ቦታዎችን እየጠቀሰ ተሳፋሪ ይጣራ ጀመር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መኪናዋ ሞላች። የመኪናዋ የመጫን አቅም አሥራሁለት ሰዎች ቢሆንም፣ ሰባት ትርፍ ሰው ጨምረው በአጠቃላይ አሥራዘጠኝ ሰዎች አሳፈሩ። ጉዞው ተጀመረ። መንገድ ላይ ትራፊክ ፖሊስ ያዛቸው። የቅጣት ካርኒ ሰጣቸው። ተናደዱ።

ሾፌሩ መለስተኛ አውቶብስዋን በከፍተኛ ፍጥነት ማሽከርከር ጀመረ። ከሾፌሩ ጎን የተቀመጠች አንዲት ሴት፣ "እባክህ ቀስ ብለህ ንዳ! ለአደጋ እንጋለጣለን፤ በዚያ ላይ ሰውን እንደዕቃ አጭቀህ እኮ ነው የጫንከው" ትለው ነበር። እሱም፣ "እባክሽ ዝም በይ! ምን አገባሽ!" ይላት ነበር።

አንድ ቦታ እንደደረሱ ጎማው "ዶሽ…ሽ…ሽ…" ማለት ሲጀምር ፍጥነቱን ቀነስ እያደረገ መኪናዋን አቆማት። የጎማ ቅያሬ ስላልነበረው ረዳቱን ወደአቅራቢያው ከተማ ልኮ እስኪያስመጣ ድረስ ተሳፋሪው ተጉላላ። ከተሳፋሪዎች አንዱ፣ "ይህን ያህል ሰው ጭነህ በዚህ ፍጥነት! ፈጣሪ ነው በጥበቡ ያተረፈን" ይላል። በዚህ ወቅት ከጎኑ ተቀምጣ የነበረችው ሴት፣ "አንተ ግን የትራፊክ ደንብ ለምን አታከብርም?" አለችው በቍጣ። ሾፌሩም፣ "ይህ እኮ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው እንጂ ሆን ተብሎ የተፈጠረ አይደለም" አላት።

“ይኸውልህ! ይህ አደጋ ቢደርስ በአንተም በእኛም የሚመጣውን ጉዳት አስብ:: ስለዚህ፣ ‘ለቀባሪው አረዱት’ እንዳይሆን እንጂ የሚከተሉትን የትራፊክ ሕጎች መከተል አለብህ:: አንደኛ፣ ከማሽከርከርህ በፊት መኪናህን መፈተሽና ተቀያሪ ጎማ መያዝህን ማረጋገጥ፤ሁለተኛ፣ ሁሌም ቀኝ መስመር ይዘህ ማሽከርከር፤ሦስተኛ ፣ ትርፍ ሰው አለመጫን፤ አራተኛ፣ ባልተፈቀደ ቦታ መኪና አለማቆም፤ አምስተኛ፣ ጠመዝማዛ መንገድ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ፤ ስድስተኛ፣ ከእግረኛ መንገድ ስትደርስ ለእግረኛ ቅድሚያ መስጠት፤ ሰባተኛ፣ የመንገድ ምልክቶችን እየተከተሉ ማሽከርከር፤ ስምንተኛ፣ ትምህርትቤት አካባቢና ሕዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች የበለጠ ጥንቃቄ ማድረግ አለብህ! አይመስልህም?” አለችው:: የያዘውን ትርፍ ሰው በሌላ መኪና ከላከ በኋላ በጥንቃቄ እየነዳ መድረሻው ከተማ በሰላም ደረሰ::

## 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የትራፊክ ደንቦችን ማክበር





ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ::

ሀ. ከተገቢው ፍጥነት በላይ መንዳት ምን የሚያስከትል ይመስላችኋል?
ለ. የትራፊክ ደንቦች በአግባቡ መከበራቸውን የሚከታተለው ማን ነው?

## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ::

ሀ. ያላሰለሰ   ለ. ጥፋት   ሐ. አወደመ   መ. አቋረጠ

## መነጠልና ማጣመር

1. የሚከተሉትን ጥምር ቃላት ነጥላችሁ ጻፉ::

ሀ. ወፍዘራሽ   ለ. ትምህርትቤት   ሐ. አመለወርቅ   መ. ፈርጀብዙ

2. ተጣማሪ የሆኑ ቃላትን በማጣመር ጥምር ቃላትን መስርቱ::

| | |
|---|---|
| ሀ. ውሃ- | ዘመድ |
| ለ. ሆድ- | ወለድ |
| ሐ. ቤት- | ገብ |
| መ.ግብር- | ሰፊ |

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሁፍ መልሱ።

ሀ. ተሳፋሪዎች የተጉላሉት በምን ምክንያት ነው?

ለ. ተሳፋሪዋ ለሾፌሩ የነገረችው ምንድን ነው?

ሐ. ሾፌሩ የፈፀመው ስህተት ምንድን ነው?

### ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።

ሀ. መናኸሪያ ለ. ነዳች ሐ. ተገለበጠ መ. አጨቀ

### መጻፍ

ከሚከተሉት አንዱን መርጣችሁ መልሱ።

1. የትራፊክ ደንቦችን ማክበር ስለሚሰጠው ጥቅም አንድ አንቀጽ ጻፉ።
2. "የማይደንቀው ሾፌር" በሚል ርዕስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## የትራፊክ ደንቦችን ማክበር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።

1. የትራፊክ አደጋ እንዳይደርስ ምን መደረግ አለበት?
2. ሕይወትና ንብረትን ከውድመት መታደግ ማለት ምን ማለት ነው?

### መነጠልና ማጣመር

በምሳሌው መሠረት ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ ቃላቱን "ቅፅል፣ ስም፣ ግስ" በማለት ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ ልጅ መጣ ቀጭኑ። → ቀጭኑ ልጅ መጣ።

| ቅፅል | ስም | ግስ |
|---|---|---|
| ቀጭኑ | ልጅ | መጣ |

ሀ. አለው ጠረጴዛ ሰፊ።

ለ. ትምህርትቤት ተመረቀ አዲሱ።

ሐ. አየሁ ሥዕል አስደሳች።

መ. እርሳስ ጥሩ ገዛሁ።

ሠ. ውሻ ይናከሳል ክፉ።

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።

   ሀ. የመኪናዎች መነሻና መድረሻ ሥፍራ ምን ተብሎ ይጠራል?

   ለ. ቀኝ መስመር ይዞ ማሽከርከር ለምን ይጠቅማል?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

   ሀ. አንድ ሰው "ጠጥቶ መንዳት ይቻላል" ቢላችሁ ምን ትሉታላችሁ? ለምን?

   ለ. የጽሑፉን ዋና መልእክት በሦስት ዓረፍተነገሮች ግለጹ።

### ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሠርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

   ሀ. ሙያ ለ. መታቀብ ሐ. መጫን መ. ፍጥነት

2. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ በቃላችሁ ተናገሩ።

   ሀ. ደረሰ ለ. ቀየረ ሐ. ፈጠረ መ. አጋጠመ

### መጻፍ

የምንባቡን ፍሬ ሐሳብ በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ።

# ግለንባብ

## ደቦ



ደቦ ሰዎች ተናጠላዊ የሥራ ጫናን የሚቀንሱበት ባህላዊ የሕብረት ሥራ ነው። ደቦ በአገራችን በሚገኙ በርካታ የገጠር አካባቢዎች የተለመደ የጋራ ሥራ ነው። በገጠር አካባቢዎች በተለይም አርሶአደሩ የሥራ ጫናን ለማቅለል አዘውትሮ ይጠቀምበታል።

በአብዛኛው የሀገራችን የገጠር አካባቢዎች የግብርና ሥራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አይደለም። ይህም በመሆኑ ሰፋፊ የእርሻ ማሳን በአንድ ሰው ወይም በአንድ ቤተሰብ ኃይል ለማረስ፣ ለመዝራት፣ ለማረም፣ ለማጨድና ለመውቃት ከባድ ነው። ይህን የሥራ ጫና ለመቀነስ ደቦ ወሳኝ የቡድን አሠራር ዘዴ ነው። ደቦ በአርሶአደሩ መካከል የቡድን ሥራን ያጠናክራል። ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሲመጣም ከአደጋ ያድናል።

✶✶✶"የደቦ ጥቅም ምንድን ነው?"✶✶✶

በአንዳንድ የመኸር ወራት፣ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሰብሎችን ሊያበላሽ ይችላል። ስለሆነም አርሶአደሮች የለፉበትንና የደከሙበትን ምርት እንዳያጡ ደቦ ከፍተኛ ሚና አለው። ሰብልን በአጭር ጊዜ ለመሰብሰብ፣ ለመከመርና ለመውቃት ያስችላል። የደቦ ሥራ በእርሻ ሥራ ብቻ ሳይሆን አርሶአደሩ የመኖሪያ ቤቱን በደቦ ይሠራል። ደቦ የተለያየ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች እንኳ ሳይቀር በጋራ የመሥራት ባህልን እንዲያዳብሩ ይረዳል። በአጠቃላይ ደቦ የመተጋገዝና የመደጋገፍ ባህልን ያጐለብታል።

## 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የመልካም ሥራ ፍሬ



## ቃላት

በዐረፍተነገሮች ውስጥ ለተሠመረባቸው ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ሥራ በጋራ ይሠራሉ።

ለ. እርጅና ተጫናቸው።

ሐ. ሥራ ማከናወን ተሳናቸው።

መ. መልካም ተግባር ነው።

ሠ. ወቅቱን አልጠበቀም።

## ማጣመርና መነጠል

1. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ነጥላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ዳቦቤት = ዳቦ + ቤት

ሀ. ትምህርትቤት ለ. መዝገብቤት ሐ. ፍርድቤት መ. መሥሪያቤት

2. የሚከተሉትን ቃላት አጣምራችሁ ጥምር ቃላትን መሥርቱ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ወሬ | ቀደም |
| ለ. ግንባር | ነጋሪ |
| ሐ. ሥራ | አፋሽ |
| መ. አመድ | ፈት |

## 2ኛ ቀን

## ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልሶችን ጻፉ።

ሀ. በጋራ የመሥራት ባህልን የሚያዳብረው አሠራር የቱ ነው?

ለ. የሥራ ጫና እንዴት ሊቃለል ይችላል?

ሐ. በሥራ መባዘን ማለት ምን ማለት ነው?

መ. ሰብል በወቅቱ ካልተሰበሰበ ምን ችግር ሊከሰት ይችላል?

## ቃላት

**በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ዓረፍተነገሮችን ሠርታችሁ ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ።**

ምሳሌ፡- <u>አብሮ መሥራት</u> ጊዜና ጉልበት ይቆጥባል።(በጋራ መሥራት።)

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. መተጋገዝ | ሐ. ማቀላጠፍ | ሠ. አብሮ ማደግ |
| ለ. ሥራን ማቃለል | መ. መደጋገፍ | ረ. ስጋት መቀነስ |

## መጻፍ

**የቡድን ሥራን ጥቅም በሚመለከት አንድ አንቀጽ ፃፉ።**

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የመልካም ሥራ ፍሬ

**በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።**

ሀ. በዕድሜ የገፉ ሰዎች ከወጣቶች የላቀ ማኀበራዊ ተሳትፎ የሚኖራቸው ለምንድን ነው?

ለ. ባለታሪኮቹ በማኀበረሰቡ ተወዳጅ ባይሆኑ ኖሮ ምን ችግር ይገጥማቸው ነበር?

ሐ. በምንባቡ ዐውድ መሠረት "ፈተና" ምንን ይገልጻል?

## መነጠልና ማጣመር

1. የተጣመሩ ቃላትን ነጥላችሁ ጻፉ።

ሀ. ፍሬነገር ለ. ቃልአባይ ሐ. ሆደባሻ መ. ልበተራራ

2. የሚከተሉትን ተጣማሪ ቃላት አጣምራችሁ ፃፉ።

| | |
|---|---|
| ሀ. መልክ | መራራ |
| ለ. አመል | ጠባብ |
| ሐ. እጅ | ቢስ |
| መ. ደም | መልካም |

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።
   ሀ. የደቦ ሥራ በአብዛኛው የሚከናወነው በየትኛው አካባቢ ነው? ለምን?
   ለ. የደቦ ሥራ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው መቼ ነው?
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።
   ሀ. የደቦ ሥራ ጠቀሜታዎች ምን ምን ናቸው?
   ለ. "ጎጆ ቀለሰ" ሲባል ምን ማለት ነው?
3. የሚከተሉትን የድርጊት መግለጫ ቃላት በቅደምተከተል አስፍሩ።

ማጨድ፣ ማረስ፣ ማረም፣ መውቃት፣ መሸጥ፣ መሰብሰብ፣ መዝራት፣

## ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሠርታችሁ ዐውዳዊ ፍቻቸውን አሳዩ።

ሀ. ባህል  ለ. አመለካከት  ሐ. አጐለበተ  መ. ተናጠል

## መጻፍ

"ደቦ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ በራሳችሁ አባባል በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉት።

# ግለንባብ


## አርአያነት

በአንድ ከተማ የሚኖሩ ሁለት ልጆች ያሏቸው ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ልጆቻቸው ሁልጊዜ ስለሚጋጩ ቤተሰቡና ጎረቤቱ ሰላም አልነበራቸውም፡፡ በዚህም የሰፈሩ ሰዎች “በጥባጮቹ ልጆች” በማለት ይጠሯቸዋል፡፡ በሰፈሩ ሰዎች ዘንድ የሚረገሙና የሚወገዙ ነበሩ፡፡ ርስበርስ አይከባበሩም፤ አይዋደዱም፡፡ ትምህርታቸውን ስለማያጠኑ ውጤታቸው ዝቅተኛ ነበር፡፡ ወላጆቻቸውንም በሥራ ስለማያግዟቸው አይወዷቸውም፡፡

ከጎረቤት ደግሞ ርስበርስ የሚከባበሩ፣ የቤትሥራቸውን በጋራ የሚሠሩ፣ ጥሩ ሥነምግባር ያላቸው ሁለት ልጆች ነበሩ፡፡ በየዓመቱ ተሸላሚዎች ናቸው፡፡ ቤተሰብ፣ መምህራንና የሰፈሩ ሰዎች ይወዷቸዋል፡፡ አንዱ ሌላውን ይመክራል፤ ያበረታታል፤ ያስተምራል፡፡

አንድ ቀን በጥባጮቹና ጥሩ ሥነምግባር ያላቸው ልጆች በድንገት መስቀለኛ መንገድ ላይ ተገናኙ፡፡ በጥባጮቹ ልጆችም፣ “ቤተሰብ፣ የሰፈር ሰዎችና ወላጆች ለምን ይወዷችኋል?” ብለው ጠየቋቸው፡፡ እነሱም “ርስበርሳችን በመመካከርና በመረዳዳት የቤት ሥራችንን በጊዜ ስለምንሠራና ስለምናጠና ነው፡፡ በዚህም ደስተኞች ነን” አሏቸው፡፡ በጥባጮቹ ልጆች ሐሳቡን ተቀበሉት፤ በተግባርም አዋሉት፡፡ ቤታቸው ውስጥ ሰላም ሰፈነ፡፡ ወላጆቻቸው ቤተሰቡን በሰላም መምራት ቻሉ፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድም በጥሩ አረአያነታቸው ክብር እያገኙ መጡ፡፡ ውስጣቸው ከመቼውም ጊዜ በላይ ሰላም አገኙ፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል ያላገኙትን ደስታ አገኙ፡፡

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

#### የቤተሰብ ኃላፊነትና ተግባር

### ቃላት

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሠመረባቸው ቃላትናሐረጋት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ስጡ።

ምሳሌ፡- ቤተሰብ ማኅበራዊ ተቋም ነው። (ድርጅት)

ሀ. በቤተሰብ ሥር እነማን ይገኛሉ? መ. ሕፃናት ታላቃቸውን ያከብራሉ።

ለ. ልጅቷ በጎ ተግባር ትፈጽማለች። ሠ. ልጆች በፍቅርና በሰላም ይኖራሉ።

ሐ. የትዳር ጓደኛን ማክበር ይጠቅማል።

### ማጣመር

ለሚከተሉት ቃላት ከሳጥኑ ውስጥ ተስማሚ የሆኑ ተጣማሪ ቃላትን መርጣችሁ አጣምሩ።

1. ቁም 2. ሥጋ 3. ባሕር 4. ኩታ 5. አብሮ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. መዝገብ | ለ. አደግ | ሐ. ነገር | መ. በል | ሠ. ገጠም |

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት አጫጭር መልሶችን በጽሁፍ ስጡ።

ሀ. ጥሩ ስነምግባር ያላቸው ልጆች አርአያነት ምን ነበር?

ለ. የባሕሪ ችግር ያለባቸው ልጆች በተሰጣቸው ምክር ምን ዓይነት ለውጥ አሳዩ?

ሐ. በቤተሰብ ውስጥ “የሰላም መስፈን” ፋይዳ ምንድን ነው?

መ. የባሕሪ ችግር ያለባቸው ልጆች ጥሩ ስነምግባር ያላቸውን በመጠየቃቸው ምን ጥቅም አገኙ?

## ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ፡፡

ሀ. ሕፃን ሐ. ሰላም ሠ. መደገፍ

ለ. ማክበር መ. ማስተማር ረ. መምራት

## መጻፍ

“የመልካም ቤተሰብ ምሳሌነት” በሚል ርዕስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የቤተሰብ ኃላፊነትና ተግባር

1. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ትክክለኛ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ፡፡

ሀ. መልካም ስነምግባር ያላቸው ልጆች ለማፍራት የቤተሰብ ኃላፊነት ምንድን ነው?

ለ. ወላጆች የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ባይወጡ ምን ይፈጠራል?

## ቃላት

ከሚከተሉት ቃላት መካከል መደበኛ የሆኑትን ቃላት ብቻ መርጣችሁ አስምሩ፡፡

ሀ. አልበልተህም/አልበላህም ሐ. መኪና ሰፊ/ልብስ ሰፊ

ለ. አልጽፈሽም/አልጻፍሽም መ. ቂጣ/ቃርያ

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. በሰላም ለመኖር የልጆች ሚና ምንድን ነው?

ለ. የልጆች ባሕርይ ጥሩ እንዲሆን የወላጆችና የመምህራን ሚና ምንድን ነው?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. በሰፈር የሚወገዙ ምን ዓይነት ልጆች ናቸው?

ለ. "ስነምግባር" የሚለው ቃል ምን ይገልጻል?

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት በምንባቡ ውስጥ በገቡበት ዐውድ መሠረት ፍቻቸውን ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

ሀ. በጠበጠ ለ. መከረ ሐ. ሰፈነ መ. አርኣያ

## መጻፍ

መልካም ሥነምግባር ባላቸውና በሌላቸው ተማሪዎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት በሁለት አንቀጾች ጽፋችሁ አንብቡ፡፡

10ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ትኩረት ለአካል ጉዳተኞች


አካል ጉዳተኛ የሚባሉት ዓይነሥውራን፣ መስማት የተሳናቸው፣ የእግር ጉዳት፣ የእጅ ጉዳት ወዘተ. ያለባቸው ናቸው። እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸው ውጤታማ ሥራ መሥራት ይችላሉ።

ዓይነ ስውራን ማንኛውንም የትምህርት ዓይነት ከማንም ባልተናነሰ መልኩ መማር ይችላሉ። ያዳመጧቸውን ትምህርታዊ መልእክቶች በብሬል መጻፍ ይችላሉ። በብሬል የጻፏቸውን ማስታዎሻዎች በእጆቻቸው እየዳሰሱ ያነባሉ፤ ይረዳሉ።

በሌላ በኩል መስማት የተሳናቸው፣ በምልክት ቋንቋ በአግባቡ አቀላጥፈው መግለፅን ይማራሉ። እነዚህና ሌሎች የአካል ጉዳት ያለባቸው ወገኖች ተገቢውን ድጋፍና እገዛ ካገኙ ከሌላው ሰው ጋር እኩል የመሥራት አቅም አላቸው።

መምህራን የልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች በአግባቡ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል። የአካል ጉዳት ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የአእምሮ አቅም ችግር የለባቸውም። መምህራን ለእንደነዚህ ያሉ ተማሪዎች ልዩ ድጋፍ የማድረግና የማበረታታት ኃላፊነት አለባቸው። ስለሆነም፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ከሌላው ሰው ጋር እኩል መሆናቸውን በመገንዘብ በልዩ ልዩ ሙያ የማሠልጠን፣ የማስተማር፣ ችግሮቻቸውን የማማከርና የመፍታት ኃላፊነት የሁሉም ሰው ትኩረት ሊሆን ይገባል።

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

**የነገዎቹ ታላቅ ዜጎች**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃላችሁ ስጡ፡፡

ሀ. የልዩ ፍላጎት ትምህርት ምንድን ነው?

ለ. ባለታሪኮቹ ወደትምህርትቤት የገቡት እንዴት ነው?

### ቃላት

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት ባዳመጣችሁት ምንባብ ዐውድ መሠረት ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ፡፡

ሀ. ጉዳት ለ. ልዩ ፍላጎት ሐ. ቃል ገባ መ. አስቸኳይ

### ማጣመርና መነጠል

1. ለሚከተሉት ቃላት ተጣማሪዎች በመፈለግ ጥምር ቃላትን መሥርቱ፡፡

ሀ. ቡና ለ. መሥሪያ ሐ. ላብ መ. ሠርቶ ሠ. ጤና ረ. ፍርድ

2. የሚከተሉተን ጥምር ቃላት ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. አንደበተቀና ለ. እግረቀላል ሐ. ፍርደገምድል መ. አይነአፋር

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

ሀ. የአካል ጉዳት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የማማከርና ችግራቸውን የመፍታት ድርሻ የማን ነው?

ለ. የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በተመለከተ የመምህራንና የወላጆች ድርሻ ምንድን ነው?

## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. አጋጣሚ　　ሐ. ስጦታ　　ሠ. ማሠልጠን

ለ. ተመሳሳይ　　መ. አስተዋይ　　ረ. ማማከር

## መጻፍ

የምንባቡን ዋና መልእክት በራሳችሁ አባባል በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የነገዎቹ ታላቅ ዜጎች

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. "ልበብርሃን" ምንን ይገልፃል?

ለ. ባለታሪኮቹ ከባለሙያ ያገኙት ምክር ምንድን ነው?

## ቃላት

ለሚከተሉት የዘዬ ቃላት መደበኛ አጠቃቀማቸውን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ሀ. ባጩላ　　ሐ. ምጎጎ　　ሠ. አረጪ

ለ. አሻቦ　　መ. መኺና　　ረ. አሽከር

## ማጣመርና መነጠል

በ "ሀ" ምድብ የሠፈሩትን ከ "ለ" ጋር በማጣመር ጥምር ቃልን መስርቱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1.ውሎ | ሀ. አጠር |
| 2.ብረት | ለ. ቤት |
| 3.ሻይ | ሐ. ጉዳት |
| 4.ዝናብ | መ. አበል |
| 5.አካል | ሠ. ድስት |

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

የሚከተለውን ጥያቄ በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ::

1. በትምህርትቤት ደረጃ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች መሟላት የሚገባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?
2. በአንቀፅ አንድ "እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች" የተባሉት እነማን ናቸው?

## ቃላት

የሚከተሉትን ሐረጋት ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ::

ሀ. የእውቀት እናት ለ. የቀለም ትምህርት

## መጻፍ

ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ትክክለኛ ሥርዓተነጥቦችን በተገቢው ቦታ በማስገባት እንደገና ጻፏቸው::

ሀ. እሰይ እንኳን ደህና መጣሽ

ለ. መቼ ትሄዳለህ

ሐ. ወደሱቅ ሄዶ ፓስታ ስኳር ቡና ሻይ ቅጠልና ዳቦ ገዛ

መ. ለምን ውጭ ቆምክ ግባ እንጂ

ሠ. ወይ ጉድ ምን ዓይነት ቀን ነው

ረ. እፍ ቢሉት ነፋስ የሚወስደው እንጀራ በላሁ

11ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### የሥራ ክፍፍል



በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ አካባቢ የሚኖሩ እህትና ወንድም ነበሩ:: ሁለቱም የሥርዓተፆታ ክበብ አባላት ናቸው:: ወንድምዬው በሥራ ክፍፍል አያምንም፤ ሥራም አይወድም፤ የቤቱን ሥራ ሁሉ የምትሠራው እህቱ ናት:: በክበቡ ብዙም ተሳትፎ የለውም:: እህትዬው ግን ብዙ ስለምትሳተፍ ከክበቡ በርካታ ቁምነገሮችን ተምራለች::

✶✶✶"እህትየዋ የሥራ ጫና ስለበዛባት ምን የምታደርግ ይመስላችኋል? ወንድምየው በሥራ ክፍፍል የማያምነው ለምንድን ነው?"✶✶✶

ሆኖም በቤት ውስጥ ባለባት የሣራ ጫና ምክንያት የትምህርት ውጤቷ ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ መጣ:: በዚህም በጣም ተቆጨች:: መብቷን በማስከበር ውጤቷን ለማሻሻል ወሰነች:: ቤተሰቦቿ ባሉበት ጮክ ብላ፣ "ለመሆኑ ምግብ ማብሰልና ሕፃናትን መንከባከብ ለሴቶች፣ የሀብት ባለቤትነት፣ የመወሰንና ሥልጣንን ለወንዶች ብቻ የሰጠው ማን ነው?" አለች:: ወንድሟ፣ "አያቶችሽ ይሆናሏ!" አላት:: እሷም፣ "ያለንበት ዘመን ይህን አስተሳሰብ አይፈቅድም፤ ይህ አስተሳሰብ በማንኛችንም ቤት ውስጥ ሊኖር አይገባም" አለችው::


አባትዬው፣ "ዛሬ ምን አዲስ ነገር መጣ ልጄ?" አሏት:: እሷም፣ "ለውጤቴ መቀነስ ምክንያቱ ገብቶኛል" አለች:: አባትዬውም ቶሎ ተረዷት:: "ልጄ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ! ከወንድምሽ ጋር ርስበርሳችሁ ትተጋገዛላችሁ ብዬ ነው፤ የቤት ውስጥ ሥራውንም እኩል ተከፋፍላችሁ የምትሠሩ መስሎኝ ነው" አሏት::

“አባዬ ወንድሜኮ የሚያጠፋው እያወቀ ነው፤ የሥርዓተፆታ ክበብ ተጠሪያችን ‘በወንድና በሴት መካከል ሥነሕይወታዊ እንጂ ሌላ ልዩነት የለም’ ብላለች። በመሆኑም፣ በቤታችን ውስጥ ልዩነት ሳይፈጠር፣ ላንዱ ባለማዳላት፣ በማኅበራዊ ኑሯችን እኩል እንድንሆን ሊደረግ ይገባል፤ የድሮው አመለካከት እዚህ ላይ መቆም አለበት!” አለች ምርር ብላ። አባቷም፣ ወንድሟም፣ እናቷም ትክክለኛነቷን ተረዷት። አባቷም፣ “በይ ልጄ፣ ከዛሬ ጀምሮ ሁላችንም የቤት ውስጥ ሥራችንን እኩል ተከፋፍለን እንሠራለን” አሏት። በቤተሰቡ አዲስና የተሳካ የሥራ ክፍፍል መሥመር ተዘረጋ። እሷም በትምህርቷ ጥሩ ውጤት እያስመዘገበች በሕግ ትምህርት በዲግሪ ለመመረቅ በቃች።

# 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### በአውራ አምባ ማኅበረሰብ የሥራ ክፍፍል





ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. "ለጋ ዕድሜ" ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. "ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸው" የሚለው ምንን ይገልጻል?

ሐ. በማኅበረሰቡ ወጥ መሥራትና እንጀራ መጋገር የማን ተግባር ነው?

መ. በጽሑፉ ውስጥ የወንድ የበላይነትን የሚገልጸው ሐሳብ የትኛው ነው?

## ቃላት

በ"ሀ" ረድፍ ያሉትን ሀረጋት በ"ለ" ረድፍ ካሉት ቃላትና ሀረግ ተስማሚያቸውን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ወጣ ወረደ | ሀ. መንደር |
| 2. የጉረቤት ስብስብ | ለ. ተሞክሮ መጋራት |
| 3. ልምድ መቅሰም | ሐ. ተንገላታ |

## መነጠል

የሚከተሉትን ጥምር ቃላት ነጣጥላችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- እጀርጥብ → እጅ ርጥብ

ሀ. አየርወለድ

ለ. ቤተዘመድ

ሐ. ልበቢስ

መ. ሠርቶአደር

ሠ. ደመበራድ

ረ. ውሃገብ

# 2ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ሥዕሉ ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?

ለ. የሥራ ክፍፍል ለምን ይጠቅማል?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልሶችን ጻፉ።

ሀ. በአባትና በልጅ መካከል የስራ ክፍፍል በተመለከተ የተደረገው ውይይት በምን ተቋጨ?

ለ. የሥራ ክፍፍልን በተመለከተ የዘመኑ አስተሳሰብ ምንድን ነው?

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን በቃላችሁ አብራሩ።

ሀ. የሥራ ክፍፍል ሐ. የሥራ ጫና ሠ. ሥርዓተፆታ

ለ. ሥነሕይወታዊ መ. አለማዳላት

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሀረግ በዐረፍተነገሮች ውስጥ በማስገባት የቃላቱንና የሀረጉን አውዳዊ ፍቺ በፅሁፍ መልስ ስጡ።

ሀ. ጫና ለ. ተቆጨች ሐ. ድሮ መ. ምርር ብላ

## መጻፍ

1. "በቤት ውስጥ ያለኝ የሥራ ድርሻ" በሚል ርእስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### በአውራ አምባ ማኅበረሰብ የሥራ ክፍፍል

ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. የአውራ አምባ ሴቶች ከሌላው ማኅበረሰብ ሴቶች በምን ይለያሉ?

ለ. ምንባቡ ስለምን ያስተምራል?

ሐ. የአውራ አምባ ማኅበረሰብ የሌሎችን ሰዎች ትኩረት የሳበው ለምን ይመስላችኋል?

## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. እንግልት ሐ. ሥልጣን ሠ. ነቀፌታ

ለ. እንጀራ መ. ጠመደ

## ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላት በማዛመድ ጥምር ቃል መስርቱ

| ተጠማሪ ቃላት | ተጣማሪ ቃላት |
|---|---|
| 1. ነገር | ሀ. መጽሐፍ |
| 2. ዓይን | ለ. ጡር |
| 3. ቤት | ሐ. ገብ |
| 4. ልብ | መ. ፈጅ |
| 5. ነፍስ | ሠ. ቢስ |

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።
   ሀ. ሥርዓተፆታ ማለት ምን ማለት ነው?
   ለ. ስለሥራ ክፍፍል ከቤተሰብ አባላት ጋር ውይይት አድርጋችሁ ታውቃላችሁ? ለምን?
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ።
   ሀ. ሥራን በተመለከተ “በወንዶችና በሴቶች መካከል ምንም ልዩነት የለም” ሲባል ምን ማለት ነው?
   ለ. የምንባቡን መልዕክት በሁለት ዓረፍተነገሮች ለጓደኞቻችሁ በቃላችሁ ግለጹ።

## ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።
   ሀ. እየቀነሰ  ለ. አዲስ መንፈስ  ሐ. ጠፋ
2. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ፃፉ።
   ሀ. ፈጠረ  ለ. ነቀፈ  ሐ. ተጋራ  መ. ተረዷት

## መጻፍ

በቤተሰባችሁ ውስጥ ስላለው የሥራ ክፍፍል አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

12ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ያለእድሜ ጋብቻ

ያለእድሜ ጋብቻ ወላጆች በራሳቸው ፍላጎትና ውሳኔ ብቻ ሴት ልጆቻቸውን ገና በለጋ እድሜያቸው የሚድሩበት ልማዳዊ ጋብቻ ነው። ይህ ዓይነት ጋብቻ በሃብት በመደለልና ዝምድናን በመሻት "ሃብት ንብረቴ ሳያልቅና ከመሞቴ በፊት ልጄን ከጥሩ ሰው ላስጠጋት" የሚል ባህላዊ ስርአትን በመከተል ይፈፀማል። በርካታዎችን ለጤና፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ችግር የሚያጋልጥ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው።

✶✶✶"ወላጆች ልጆቻቸውን ያለዕድሜያቸው ከዳሩ የሚገጥማቸው ችግር ምንድን ነው?"✶✶✶

ይህ ልማዳዊ ጋብቻ በሴት ህጻናት ላይ የሚያስከትላቸውን ችግሮች ዘርዘር አድርገን እንመልከት። አንደኛ፣ ህጻናት የእናትን፣ የአባትን፣ የእህትንና የወንድምን ፍቅርና እንክብካቤ ሳይጠግቡ ከቤተሰብ በመለየት ለከፋ ሕይወት ይዳረጋሉ። ሁለተኛ፣ የትምህርት እድል እንዳያገኙና ትምህርት የጀመሩትንም እንዲያቋርጡ ያደርጋል። ሶስተኛ፣ በግዳጅ በሚፈፀምባቸው የወሲብ ጥቃት ምክንያት ለተለያዩ በሽታዎች ይጋለጣሉ፤ ካለእድሜያቸው የሚያረግዙና በወሊድ የሚሞቱትም ብዙ ናቸው። አራተኛ፣ ካለእድሜያቸው የትዳር ሕይወትን የመምራት ግዴታ ስለሚኖርባቸው የስራ ጫና፣ የወንዶች ዱላ፣ ጭቅጭቅና ጭንቀት ያጋጥማቸዋል።

በዚህም ምክንያት ወደማያውቁት አካባቢ በመሰደድ ለእንግልትና ለሞት ይዳረጋሉ። ወላጆችም ለሰርግና ምላሽ ሲባል በኢኮኖሚ ከመራቆታቸው በተጨማሪ በልጆቻቸው ላይ ለሚከሰቱት ተደራራቢ ችግሮች ምክንያት በመሆናቸው ሃዘናቸው መሪር ይሆንባቸዋል። ስለሆነም ማንኛውም ህብረተሰብ ይህንን ዓይነት አጉል ልማድ የማስቀረት ኃላፊነት አለበት።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



የተሳካ ራእይ

### ቃላት

ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ፃፉ::
(እኩልነት፣ ባለፀጋ፣ ግልፅ፣ ራዕይዋ፣ ጓጓች፣ ተወሰነ)

ሀ. ጽሑፋችን ________ ነው::

ለ. የወደፊት ________ ዶክተር መሆን ነው::

ሐ. ጥሩ እውቀት ለማግኘት ________::

መ.________ የሰፈነበት ህብረተሰብ መፍጠር ራዕይዋ ነው::

ሠ. ያለዕድሜ ጋብቻው ተግባራዊ እንዳይሆን________::

### መነጠልና ማጣመር

1. የሚከተሉትን ቃላት ዋና ቃሉን ከቅጥያዎች ነጥላችሁ ፃፉ::

   ሀ. ጥሩነት ለ. እድለኛነት ሐ. የበታችነት መ. ህጋዊነት ሠ. ወቅታዊነት

2. “-ነት” ያላቸውን አምስት ቃላት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. በቡድን በመወያየት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ በቃላችሁ ስጡ::

   ሀ. ያለእድሜ ጋብቻ ማለት ምን ማለት ነው?

   ለ. በአካባቢያችሁ ጋብቻ እንዴት ይፈጸማል?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. “ከጥሩ ሰው ላስጠጋት” ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. “ወላጆች ልጆቻቸውን በእኩልነት አያዩም” ሲባል ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል?

ሐ. በአካባቢያችሁ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የሚያስከትሉ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

መ. ያለዕድሜ ጋብቻ እንዳለ ቢቀጥል ስለሚከሰቱት ማህበራዊ ችግሮች ከቤተሰቦቻችሁ ጋር በመወያየት ያገኛችሁትን መረጃ ፅፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።

ሀ. እኩልነት ለ. ሥራ ሐ.ማዳላት መ. መለየት ሠ. ጋብቻ ረ. አለመወሰን

## መጻፍ

“ያለእድሜ ጋብቻ የሚያስከትላቸው ችግሮች” በሚል ርዕስ ተገቢውን ስርዓተነጥቦች በመጠቀም ሁለት አንቀጾችን ጻፉ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የተሳካ ራእይ

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሰላም አባቷን “የእኔን ራእይ ልታጨናግፍ አይገባም” ስትል ምን ማለቷ ነው?

ለ. ለሰላም ውጤታማ መሆን ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሐ. ሰላም “ዕድሜዬ ገና አስራአራት ነው” ስትል ምን ማለቷ ነው?

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. ሰፈነ ለ. እድል መንፈግ ሐ. መታደግ መ. አወጣ አወረደ

## ማጣመር

የተሠመረባቸውን ቃላት አስተካክላችሁ ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፉ::

ሀ. እሱ መጽሐፍ አነበቡ::　　ሐ. እኔ ትምህርት ቤት ነገ ሄድኩ::

ለ. እኛ ልብሴን ለበስን::　　መ. እኛ ጎበዞች ናችሁ::

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ::

   ሀ. ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ያለዕድሜያቸው በመዳራቸው ለምን ለምን ችግሮች ይዳርጋሉ?

   ለ. ያለዕድሜ ጋብቻ "ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው" የተባለው ለምንድን ነው?

   ሐ. በምንባቡ መሠረት ስደትና ሞት በምን ምክንያት ይከሰታሉ?

   መ. ያለዕድሜ ጋብቻ ከሚያስከትላቸው ጉዳቶች ሁለቱን ጥቀሱ::

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ከመዝገበቃላት ፈልጋችሁ ጻፉ::

   ሀ. ገፋ　ለ. አካለመጠን　ሐ. ያረጀ ያፈጀ　መ. ግዳጅ　ሠ. አዳበረ　ረ. መራ

2. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ::

   ሀ. ተንገላታ　ለ. ተደራራቢ　ሐ. ለጋ　መ. መሪር　ሠ. ንብረት

## መጻፍ

"ያለዕድሜ ጋብቻ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋና መልእክት በአንድ አንቀጽ ጻፉ::

## ግለንባብ

### የያሬድና የጥሩነሽ ጉብኝት



የያሬድና ጥሩነሽ የሚባሉ ባልና ሚስት በአዲስ አበባ ከተማ ይኖሩ ነበር:: እነዚህ ባለትዳሮች ባለጸጎች ነበሩ:: በግራር ዛፍ ስር ተቀምጠው ስለሃገራቸው ይጨዋወታሉ:: ጥሩነሽ፣ “ግን መቼ ነው አገራችንን የምንጎበኘው? ጊዜው ራቀኝ!” አለችው:: “አንድ ቀን” አላት:: “ያ ቀን ነው የናፈቀኝ” አለችው:: በድንገት አንድ ፈረንጅ በአጠገባቸው አለፈ:: ሁለቱም ፍዝዝ ብለው ተመለከቱት:: ጥሩነሽ ቀደም ብላ፣ “ይኸውልህ፣ እኛ እዚህ ቁጭ ብለን የብሔራዊ ሙዚየምን ፣ የአንበሳ ግቢንና ሌሎች ቅርሶቻችንን አላየናቸውም:: እነሱ ግን ባህርማዶ ተቀምጠው ስለቅርሶቻችን አሳምረው ይነግሩናል” አለችው:: “እውነትሽን ነው፤ ስለቅርሶቻችን በሬድዮ ሰምተናል፤ በቴሌቪዥን አይተናል” አላት::

★★★ “ባዶነት” ማለት ምን ማለት ነው? “ሠርተን ማለፍ አለብን” ማለት ምን ማለት ነው? ★★★

ያሬድ ባዶነት ተሰማው:: ጊዜ አላጠፋም፤ በቂ ገንዘብ ያዙ:: ከሶስት ወር በኋላ ጉብኝታቸውን በአምስት ኪሎ ብሔራዊ ሙዚየም “ሀ” ብለው ጀመሩ:: በውስጡ ባሉት ቅርሶችና መስህቦች ተገርመው ሳይጨርሱ ወደሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ተጓዙ:: ዋልያዎችንና ጭላዳ ዝንጀሮዎችን ተመለከቱ፤ ወደዷቸው:: በማግስቱም ጉዟቸውን ወደባህርዳር አደረጉ:: በጀልባ እየተዘዋወሩ ጣና ሃይቅንና ደሴቶችን ጎበኙ:: ከዚያም ወደጢስ አባይ ሄደው የአባይን ፏፏቴ አደነቁ፤ በደስታም ተፍነከነኩ::


በሦስተኛው ቀን ወደላሊበላ ተጉዘው ውቅር አብያተክርስቲያናትን ጎበኙ። ጥሩነሽ “እነዚህ የአባቶቻችን ድንቅ የኪነህንፃ ጥበብ ሥራዎች እንዴት ያምራሉ! ኮራሁባቸው” አለችው።

የላሊበላ ጉብኝታቸውን አጠናቀው ወደአክሱም አመሩ። በአክሱም ረጃጅም ድንቅ የሃውልት ስራዎች የበለጠ ተደነቁ። ጉብኝታቸውን አጠናቀው ወደአፋር አቀኑ። የኤርታኢሌን እሳተጎሞራ ሐይቅ ጎበኙ። ከጎድጓዳማው ቦታ እንደወጥ የሚንተከተከውን ቅልጥ ብርቱካናማ የአለት ፈሳሽ እያዩ ተደመሙ። በነጋታው ወደደቡብ ተጉዘው የስምጥ ሸለቆ ሃይቆችን፣ የጢያ ትክል ድንጋይንና የኮንሶ እርከን ስራን ተመለከቱ። ከዚያም ወደኦሮሚያ ሄደው የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክን፣ በጅማ የአባጅፋር ቤተመንግስትንና የባሌ ተራሮችን ጎበኙ። ወደሃረር ተጉዘውም፣ የጀጎል ግንብን አዩ። በመጨረሻም በሃገራቸው ተፈጥሯዊና ሰውሠራሽ ታሪካዊ ቅርሶች እየተነጋገሩ ጉዟቸውን ወደትውልድ ቀያቸው አዲስ አበባ አደረጉ።

# 1ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የቱሪስት መስህቦቻችን




ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ ስጡ::

ሀ. የላሊበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት የተሠሩት ከምንድን ነው?

ለ. አንበሳ ግቢ የት ይገኛል?

ሐ. ባለታሪኮቹ በኦሮሚያ ክልል የጎበኟቸው የቱሪስት መስህቦች ምን ምን ናቸው?

መ. የአክሱም ሀውልት የት ይገኛል?

## ቃላት

በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ::

ሀ. ቅርስ ለ.ማራኪ ሐ. ተፈለፈለ መ. አቅፎ ሠ. እምብርት

## ማጣመርና መነጠል

1. "-ነት" የሚል መድረሻ ቅጥያ ተጠቅማችሁ ስድስት ቃላትን ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ::

2. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በምሳሌው መሠረት ነጥላችሁ አሳዩ::

ሀ. ብልህነት ለ. ክፉነት ሐ. ባዶነት መ. ሆዳምነት ሠ. አሸናፊነት ረ. ለምነት

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ ስጡ፡፡**

ሀ. ያሬድና ጥሩነሽ የት ይኖራሉ?

ለ. ለነጥሩነሽ ጉብኝት መነሳሳት ምክንያት የሆናቸው ምንድን ነው?

ሐ. ባለታሪኮቹ በቅድሚያ የጎበኙት የትኛውን የቱሪስት መስህብ ነው?

መ. ባለታሪኮቹ በጣም የተደነቁበት የመስህብ ቦታ የትኛው ነው? ለምን?

### ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ለጓደኞቻችሁ በቃላችሁ ግለጹ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ግንብ | ሐ. ባህርማዶ | ሠ. ሸለቆ |
| ለ. ሃውልት | መ. ሃይቅ | ረ. ተራራ |

2. የሚከተሉትን ቃላት የመዝገበቃላት ፍቻቸውን ፃፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ጎበኘ | ሐ. ጥበብ | ሠ. ተፍነከነኩ |
| ለ. ተጨነቀች | መ. ሃሴት | |

### መጻፍ

**የጉብኝት ቦታዎችን በአካል ተገኝተው ከመጐብኘትና በቴሌቪዥን ከማየት የትኛው እንደሚሻል በቡድን በመወያየት ሁለት አንቀጽ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡ በፅሁፋችሁ ውስጥ ተገቢ ስርዓተነጥቦችን ተጠቀሙ፡፡**

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### የቱሪስት መስህቦቻችን

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

   ሀ. የቱሪስት መናኸሪያ ማለት ምን ማለት ነው?

   ለ. "ደሴት" ምንድን ነው?

   ሐ. በደቡብ ክልል የሚገኙትን የቱሪስት መስህቦች ግለፁ?

## ቃላት

2. በ "ሀ" ረድፍ ለሚገኙት ቃላት ከ "ለ" ረድፍ ተስማሚያቸውን መርጣችሁ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እርከን | ሀ. ቋጥኝ |
| 2. ቅርስ | ለ. ጥብቅ ቦታ |
| 3. ብሄራዊ ፓርክ | ሐ. ቋሚ |
| 4. አለት | መ. ውርስ ሃብቶች (እሴት) |
| 5. ትክል | ሠ. ደረጃ |

## መነጠል

1. በዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ቃላት "ቅፅል፣ ስም፣ ግስ" በማለት ነጥላችሁ ጻፉ።

ሀ. ብልሁ አሊ እርሻውን አረሰ። 
ለ. ህጻኗ ልጅ ዳቦ በላች። 
ሐ. ጥቁሩ በሬ ተሸጠ። 
መ. ጉበዟ ተማሪ ታጠናለች። 
ሠ. ላሟ ነጭ ናት።

2. የሚከተሉትን ቃላት መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. እንደበላህ ለ. ስለመጣች ሐ. ከመሄድሽ መ. እንደወጣህ

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱትን የአዲስ አበባ ከተማ መስህብ ቦታዎችን ጥቀሱ?

ለ. "ባዶነት" የሚለው ቃል ምንን ይገልፃል?

ሐ. "ሠርተን ማለፍ" አለብን ሲባል ምን ማለት ነው?

2. በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. መስህቦችን ለመጎብኘት ምን ያስፈልጋል?

ለ. ባለታሪኮቹን በደስታ እንዲፍነከነኩ ያደረጋቸው ምንድን ነው?

ሐ. የኤርታኢሌ ልዩ ባህሪ ምንድን ነው?

መ. የምንባቡን የመጨረሻ አንቀጽ ዋና መልዕክት በአንድ ዓረፍተነገር ጻፉ።

## ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩና አውዳዊ ፍቻቸውን በቃላችሁ ተናገሩ፡፡

ሀ. ናፈቀ　　ሐ. ተገረመ　　ሠ. ማድነቅ

ለ. አለፈ　　መ. ማግስት　　ረ. ሃሴት

2. በሚከተሉት አያያዥ ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ፡፡

ምሳሌ፡- አንሻ አንደኛ ወጣች፡፡

አንሻ አልደነቃትም፡፡

በአያያዥ ሲጣመሩ፡- አንሻ አንደኛ ወጣች፤ ግን አልደነቃትም፡፡

ሀ. ስለዚህ　　ሐ. እና　　ሠ. እንዲሁም　　ሰ. ምክንያቱም

ለ. ግን　　መ. እንጂ　　ረ. ይሁን እንጂ

## መጻፍ

የባለታሪኮቹን የጉብኝት ሂደት የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

## ግለንባብ

### በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች

በአዲስ አበባ ከተማ በርካታ ሠው ሠራሽና ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች አሉ፡፡ ሠው ሠራሽ ከሆነት መካከል የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግስት፣ የአርበኞች የድል ሀውልት፣ አራት ኪሎ፣ አምስት ኪሎና ስድስት ኪሎ አካባቢ የሚገኙ ሙዚየሞች ይጠቀሳሉ፡፡ አንበሳ ግቢ እና የጉለሌ የእፅዋት ማዕከል ደግሞ ከተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግስት በ1879ዓ.ም እንጦጦ ተራራ ላይ በንጉስ አፄ ምኒልክ ተመሠረተ፡፡ በውስጡም ንጉሱ ይገለገሉባቸው የነበሩ የመመገቢያ እቃዎች፣ አልባሳት፣ የጦር መሳሪያዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶችን ለቱሪስት በሚስብ መልኩ ይዞ ይገኛል፡፡ ይህ ቤተ መንግስት ለአሁኗ አዲስ አበባ ከተማ መመስረት መሠረት ሆኗል፡፡

የአርበኞች የድል ሀውልት በ1944ዓ.ም በንጉስ አፄ ኃ/ስላሴ አማካኝነት አራት ኪሎ አደባባይ ተገነባ፡፡ ይህ የድል ሀውልት የቆመው ሀገራቸውን በጣልያን ጦር ላለማስደፈር አምስት አመታት ያህል መራር ትግል ያደረጉ አርበኞችን ለመዘከር ነው፡፡ ሀውልቱ ታሪካዊ ከመሆኑም ባሻገር ለአካባቢው ውበትን አጎናፅፏል፡፡

የአራት ኪሎ ዩኒቨርስቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም በ1947 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ በኢትዮጵያ ብቸኛው የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም ነው፡፡ በሙዚየሙ ውስጥ በርካታ ልዩ ልዩ የፍጥረታት ዝርያዎች ይገኛሉ፡፡ በአብዛኛው ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ ፍጥረታትን ይዟል፡፡ በርካታ ፍጥረታት አካላቸው እንዳይበሰብስ ኬሚካል ተቀብተው በሥርዓት ተቀምጠዋል፡፡ ሙዚየሙ በሁሉም ዝርያዎች አስራ ሦስት ሺህ አምስት መቶ የሚደርሱ ስብስቦች አሉት፡፡

አምስት ኪሎ የሚገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም በ1936 ዓ.ም ተቋቋመ፡፡ የቀድም ስሙም “አርኪዮሎጂ ሙዚየም” በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ ሙዚየም ውስጥ ከ1 ሚሊዮን የሚበልጡ በርካታ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡ ከቅርሶቹም መካከል የአርዲን፣ የሠላምን እና 3.4 ሚሊየን እድሜ ያላትን የሉሲን ቅሪተ አካሎች እናገኛለን፡፡ ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የተሰበሰቡ ቅርሶች ስላሉት ትንሿ ኢትዮጵያ እየተባለም ይጠራል፡፡

የስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ሙዚየም በ1968 ዓ.ም ተመሠረተ። በውስጡም ወደ 10 ሺህ የሚጠጉ ቅርሶች ይገኛሉ። ይህ ሙዚየም የአፄ ኃ/ስላሴ ቤተ መንግስት ስለነበር ንጉሱ ይገለገሉበት የነበሩ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቅርሶች ይገኛሉ።

ስድስት ኪሎ አካባቢ የሚገኘው አንበሳ ግቢ በ1948 ዓ.ም ተቋቋመ። በውስጡ የተለያዩ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ይገኛሉ። እነሱም አንበሳ፣ ጦጣ፣ ጭላዳ ዝንጀሮ፣ ጥንቸልና የመሣሠሉት ይጠቀሳሉ። ይህን ግቢ በተለይ ህፃናት ብዙ ጊዜ ለጉብኝት ይመርጡታል።

የጉለሌ የእፅዋት ማዕከል በ2005 ዓ.ም ተመሠረተ። ምንም እንኳን በቅርብ ጊዜ የተመሠረተ ቢሆንም በውስጡ በርካታ የእፅዋት ዓይነቶችን ይዞ ይገኛል። ይህም የከተማዋ መስህብ ከመሆን ባሻገር ለከተማዋ ነዋሪዎች ስለእፅዋት አያያዝ ግንዛቤ ይሠጣል።


በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ሠው ሠራሽና ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች በአገር ውስጥም በአለም አቀፍ ደረጃም በርካታ ጎብኚዎች ያሏቸው ሲሆኑ ተጎብኚተው የሚሠለቹ አይደሉም።

ምንጭ፡ ከአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዚም ቢሮ፣ (2002 ዓ.ም) መፅሔት፣ለክፍል ደረጃው እንዲስማማ ተደርጎ የተወሠደ።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ከተማ መስሕቦች




ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ከተማ መስህቦች

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች

1. የአፄ ምኒልክ ቤተመንግስት
2. --አንበሳ ግቢ
3. የአርበኞች የድል ሃውልት
4. የጉለሌ እፅዋት ማዕከል
5. አራት ኪሎዩኒቨርስቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ሙዚየም
6. አምስት ኪሎ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሙዚየም
7. የስድስ ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ሙዚየም

### ቃላት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጭ ቃላት ተስማሚውን መርጣችሁ ዓረፍተነገሮቹን አሟሉ።**

| ጥንታዊ | መርሃ ግብር | መስህብ | አስጎብኚ |
|---|---|---|---|

1. ቱሪስቶችን የሚመሩ ሰዎች ------------------------ ይባላሉ።
2. እንጦጦ የሚገኘው የአፄ ምኒልክ ቤተመንግስት የቆዬ ነው።

   የቆዬ ማለት ----------------------- ማለት ነው።
3. መምህርቷ ለጉብኝት የሚሆን ዕቅድ አውጡ፤ በሚለው ዓረፍተነገር፣ ዕቅድ ማለት ---------- ማለት ነው።
4. አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብዙ የሚታዩ ቦታዎች አሉ።

   የሚታዩ ቦታዎች ማለት -------------------------ማለት ነው።

### መነጠል

1. የሚከተሉትን ቃላት መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. በየዋህነት | ሐ. ከቅንነት | ሠ. በገራምነት |
| ለ. ከሞኝነት | መ. በወዳጅነት | ረ. በሠራተኝነት |

2. የሚከተሉትን ቃላት ዋና ቃሉን ከቅጥያው ነጥላችሁ ፃፉ።

ሀ. ህፃንነት　　ሐ. ብልህነት　　ሠ. ሰውነት

ለ. ደግነት　　መ. ሊቅነት　　ረ. አሻሚነት

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።
   ሀ. በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች ማን ማን ናቸው?
   ለ. “ሠው ሠራሽ የቱሪስት መስህቦች” ምንድን ናቸው፡
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሶቻችሁን በፅሑፍ ሰጡ።
   ሀ. የሉሲ ወይም የድንቅነሽ ቅሪተ አካል እድሜ ስንት ነው?
   ለ. ሠው ሠራሽና ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦችን መንከባከብ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?
   ሐ. ስድስት ኪሎ አካባቢ የሚገኙት መስህቦች እነማን ናቸው?

### መጻፍ

“የምወደው የቱሪስት መስህብ” በሚል ርዕስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሁለት አንቀፆችን ፅፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ከተማ መስህቦች

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።
   ሀ. “ቅሪተ አካል” ምንድን ነው?
   ለ. እንጦጦ ተራራ ላይ የሚገኘው ታሪካዊ የመስህብ ቦታ ማን ይባላል?
   ሐ. ተፈጥሯዊ የሚባሉት የቅርስ አይነቶች ሰው ሠራሽ ከሆኑት የቅርስ አይነቶች በምን እንደሚለዩ ዘርዝሩ።
   መ. በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው ሆቴል ማን ነው?
2. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሠርታችሁ ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለፁ።

ሀ. ወሠነ ትምህርት　　ሐ. ድል　　ሠ. ዝርያ

ለ. አስደናቂ　　መ. መረጃ　　ረ. ቁርኝት

## ማጣመር

በምሣሌዎች መሠረት በነጠላና ብዙ ቁጥር ስድስት ዓረፍተነገሮችን ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

| | በነጠላ ቁጥር | በብዙ ቁጥር የተፃፉ |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | <u>የተፃፉ ዐረፋተነገሮች</u> | <u>ዐረፍተነገሮች</u> |
| 1. | በጉ ሳር ይበላል፡፡ | በጎች ሳር ይበላሉ ፡፡ |
| 2. | አሊ ልብሱን ይለብሳል፡፡ | እነአሊ ልብሳቸውን ይለብሳሉ፡፡ |

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. በቡድን ሆናችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃላችሁ ስጡ፡፡

   ሀ. የቱሪስት መስህቦች ለከተማችን የሚሰጡት ፋይዳ ምንድን ነው?

   ለ. ተፈጥሯዊ መስህቦች የሚባሉት ምን አይነት ናቸው?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በፅሑፍ ስጡ፡፡

   ሀ. በሠው ሠራሽና በተፈጥሮ መስህቦች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለፁ፡፡

   ለ. የአፄ ምኒልክ ቤተመንግስት የት ይገኛል?

   ሐ. የምንባቡ ዋና መልእክት ምንድን ነው?

## ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበ ቃላት ፍቻቸውን ፃፉ፡፡

   ሀ. አጎናፀፈ    ለ. በርካታ    ሐ. ታሪካዊ    መ. ማዕከል    ሠ. ፍጥረት

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት ምንነት በቃላችሁ ግለጿቸው፡፡

   ሀ. መሠረት    ሐ. ሠው ሠራሽ    ሠ. ብርቅዬ ፍጥረታት

   ለ. ቤተመንግስት    መ. ተፈጥሯዊ    ረ. አርበኛ

## መጻፍ

“በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች” በሚል የቀረበውን ምንባብ በራሳችሁ አባባል በአንድ አንቀፅ አሳጥራችሁ ፃፉ፡፡

15ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ለትውልድ የሚተርፍ ስራ

በአንድ ከተማ ሁለት የባህልና ቱሪዝም ልማት ጽህፈትቤት ባለሙያዎች ነበሩ:: በአካባቢያቸው በሚገኘው መስህብ ቦታ ቱሪስቶችን በአግባቡ አለማስተናገድና አልፎ አልፎ የሚከናወን የእንስሳት አደን አሳሰባቸው፤ በተለይም የአንዳንዶቹ ድርጊቶች መደጋገም እንቅልፍ ነሳቸው::

✶✶✶ "ስለመስህብ ቦታዎች ሰዎችን የምናስተምርባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው? የጉብኝት ሥፍራዎችን ለመንከባከብ ደንቦችን የማክበር ኃላፊነት የማን ነው?" ✶✶✶

ችግሮቹን እንዴት መፍታት እንዳለባቸው መላ ማፈላለግ ጀመሩ:: ሲመካከሩም ችግሮቹ በእነሱ አካባቢ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ በሌሎችም አካባቢዎች እንደሚዘወተሩ አረጋገጡ:: ችግሮቹን ለማስወገድም የመጀመሪያው መፍትሄ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማስተማር እንደሆነም ተስማሙ:: ለማስተማሪያም ፖስተሮችንና በራሪ ወረቀቶችን አዘጋጁ::

ሰዎች በሚሰባሰቡባቸው አካባቢዎች ፖስተሮችን ለጠፉ፤ የአካባቢውን ማህበረሰብ፣ አስጎብኚዎችንና ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸውን ድርጅቶች በማወያየት አስተማሩ:: በትምህርቱ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች መካከልም ቱሪስቶችን በአግባቡ ማስተናገድ፣ የመስህብ ቦታዎችን ከብክለት መከላከል፣ እፅዋትንና እንስሳትን ከጉዳት ማዳን የሚሉት ይገኙባቸዋል:: ከትምህርቱም በኋላ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች የሁሉንም ችግሮች ከምንጫቸው ለማድረቅና የጎብኚና የአስጎብኚ ደንቦችን ለማክበርና ለማስከበር ተስማሙ:: በገቡት ቃል መሰረትም ጠንክረው መስራታቸውን ቀጠሉ::

በሂደትም ችግሮቹ እየተቃለሉ መጡ:: ሁለቱም ባለሙያዎች መስህቦችን ዘመን ተሻጋሪ የሚያደርጉ ስራዎች በመስራታቸው ተደሰቱ:: በአካባቢው ማህበረሰብም አድናቆትንና ዝናን አተረፉ::

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የጉብኝት ደንቦችን ማክበር**





**ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ።**

ሀ. የጉብኝት ቦታዎች በቆሻሻ እንዳይበከሉ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

ለ. አስጐብኝዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ ደንቦች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ቱሪስቶች በጉብኝታቸው እንዲደሰቱና እንዲኮሩ ምን መደረግ አለበት?

### ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በፅሁፍ ግለፁ።

ሀ. ተገነቡ ለ. ወከባ ሐ. አስደሳች

2. የተለያዩ ዘዬዎችን በራሳችሁ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡- "አወድ፣ ጩስ፣ በእሎ፣ ምጅምር ..."

### መነጠል

**የብዙ ቁጥርና የመደብ አመልካች ቅጥያዎች ያሏቸውን አምስት አምስት ቃላት ጻፉና ዋናውን ቃል ከቅጥያው ነጥላችሁ አሳዩ።**

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡
   ሀ. ርእሱ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?
   ለ. ከስዕሉ ምን ተረዳችሁ?
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡
   ሀ. የጉብኝት ደንብ ማውጣት ለምን ይጠቅማል?
   ለ. የጉብኝት ደንብ አለማክበር ምን ያስከትላል?
   ሐ. ከምንባቡ ያገኛችሁት ትምህርት ምንድን ነው?

### ቃላት

1.በሚከተሉት ቃላት በቡድን በመወያየት የተረዳችሁትን መልእክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በተወካያችሁ አማካይነት አቅርቡ፡፡

ሀ. ደንብ ለ. መጉብኘት ሐ. መስህብ መ. ቱሪስት

2. ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበቃላት ፍቻቸውን ጽፋችሁ አንብቡ፡፡

ሀ. ድርጅት ለ. መላ ሐ. ባለሙያ መ. መለጠፍ

### መጻፍ

የምንባቡን ሦስተኛ አንቀጽ ዋና መልዕክት በራሳችሁ አባባል በአምስት ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ አንብቡ፡፡

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

"የጉብኝት ደንቦችን ማክበር"

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡
   ሀ. ከቱሪስት የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
   ለ. ጎብኚዎችን ማስተናገል ክልክል መሆኑን መረዳት ያለባቸው እነማን ናቸው?
   ሐ. የአስጎብኚ ሥራ ለመሥራት ምን ማሟላት ያስፈልጋል?
2. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ሀ. ፍሬያማ ለ. ተገደቡ ሐ. ጥንቃቄ

## መነጠል

1. በብዙ ቁጥር የተገለጹ ስድስት ቃላትን ጻፉና ቅጥያዎቹን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ ሀ. ቁጥሮች — ቁጥር –ኦች

ለ. ምሳሌዎች — ምሳሌ –ዎች

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. "በሂደት" ለሚለው ቃል የሚስማማው ፍቺ ምንድን ነው?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

ሀ. "የጽሕፈትቤት ባለሙያ" የምንለው ምን ዓይነቱን ሰው ነው?

ለ. አንድ የቱሪስት መስህብ አስጎብኚ ሊከተላቸው የሚገቡ ደንቦች ምን ምን ናቸው?

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ከመዝገበቃላት ፈልጋችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ጠነከረ ለ. አስወገደ ሐ. አተኰረ መ. ቀጠለ ሠ. አደነቀ

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በቃላችሁ አብራሩ፡፡

ሀ. ዝና አተረፉ ሐ. ዘመን ተሻጋሪ

ለ. አስጎብኚ መ. አስከበረ

## መጻፍ

"ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ መሥራት" በሚል የቀረበውን ምንባብ ዋና መልዕክት በአምስት ዓረፍተነገሮች ፃፉ፡፡

16ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### የባህላዊ ስፖርት ጨዋታዎች



ባህላዊ ስፖርት ረጅም ታሪክ ያለው የመዝናኛና የጊዜ ማሳለፊያ ጨዋታ ነው። በዚህም ሰዎች የርስበርስ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ፤ አባቶችና እናቶች ጠብቀው ያቆዩትን ባህል፣ ወግና ልማድ ይለዋወጡበታል። ሁለንተናዊ ትውፊታቸው እንዲቀጥል ጠንካራ መሠረት ይጥላል።

ትግል፣ ገና ጨዋታ፣ ፈረስ ጉግስ፣ ገበጣ፣ ውሃ ዋና፣ ድብብቆሽና ልቅሞሽ የባህላዊ ስፖርት ዓይነቶች ናቸው። ትግል በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ፉክክር ነው። ፉክክሩ ተጋጣሚዎች ሁለት እጃቸውንና እግራቸውን ተጠቅመው አንዱ ሌላውን ለመጣል ሌላው ላለመውደቅ የሚያደርጉት ግብግብ ነው።

✶✶✶ "ትግል ምን ዓይነት ስፖርት ነው? በገና ወቅት የሚዘወተረው ስፖርት ምን ዓይነት ነው?" ✶✶✶

የገና ጨዋታ፣ በገና ወቅት ይከወናል። በየቡድኑ ያሉት ተጫዋቾች በአካባቢው ወይም በየጎጡ ባሉ ወጣቶች ብዛት ይወሰናል። ተጫዋቾች ነጭ እጀጠባብ ይለብሳሉ። የሚጫወቱበት ድቡልቡል ሩር (ጥንግ) ይይዛሉ። ሩሯን ለመለጋት የሚያስችል ጫፉ ቆልመም ያለ ዱላ ይጠቀማሉ። በገና ጨዋታ ጊዜ አንድ ሰው ቢጎዳ ግጭት (ጠብ) የለም። "በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ" አይደል አባባሉ።

የፈረስ ጉግስ የፈረስ ግልቢያ ጨዋታ ነው፡፡ ፈረስ ጋላቢዎች በጥንድ በመሆን ዘንግና ጋሻ በመያዝ በሽምጥ እየጋለቡ አንዳቸው አንዳቸውን በዘንግ በመምታት ሌላው በጋሻው በመከላከል ጨዋታው ይከናወናል፡፡ በፈረስ ግልቢያው በፍጥነት ደርሰው ተባራሪን የመቱ ወይም ያልተያዙ ተባራሪዎች አሸናፊ ይሆናሉ፡፡

ሌላው ባህላዊ ጨዋታ ገበጣ ነው፡፡ ገበጣ እንደአስፈላጊነቱ በመሬት ላይ አለዚያም በእንጨት ላይ ይዘጋጃል፡፡ ሁለት ተጫዋቾች ስድስት ስድስት ጉድጓድ ይዘው ይጫወታሉ፡፡ በየጉድጓዶቹ አራት አራት ጠጠሮች ይኖራሉ፡፡ ሁሉንም ጠጠሮች ካንዱ ጉድጓድ በማንሣት በሌሎች ጉድጓዶች ላይ አንዳንድ በመጨመር በተቃራኒው ንጉስ ላይ ሲደርሱ አንድ ጠጠር በማንሳት ጨዋታው ይቀጥላል፡፡ ልቅሞሽ ደግሞ በሁለት ልጆች መካከል የሚደረግ የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ ጠጠሩን ወደላይ በማጓንና ሲመለስ በመያዝ ይከናወናል፡፡

ድብብቆሽም ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆች የሚጫወቱት የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ አንዳቸው አጫዋች ሲሆኑ ሌሎች ይደበቃሉ፡፡ አንዳቸው ፈላጊ ሌሎቹ ተፈላጊ ይሆናሉ፡፡ ተፈልገው የተገኙት ተሸናፊ ይሆናሉ፡፡

ውሃ ዋና ደግሞ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ተፎካካሪዎች በውሃ ላይ የሚከውኑት ውድድር ሲሆን፣ ቀዳሚው አሸናፊ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ የባህል ስፖርት ጨዋታዎች በጣም የሚያስደስቱና በአብዛኛውም በማኅበረሰባችን ዘንድ የሚወደዱና የሚዘወተሩ ናቸው፡፡

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## ስፖርት ለሰላም

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለጥያቄዎች መልስ በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. እነአልማዝ በውሃ ዋናና በሌሎች ውድድሮች አሸናፊ የሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው?

ለ. የስፖርት ጥቅሞች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ።

### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. ደረጀ ለ. ባልንጀራ ሐ. አባረረ መ. የበላይነት ሠ. ሰላም ረ. ትግል

### ማጣመር

"-ኣማ" ና "-ኣም" የሚሉትን ቅጥያዎች በመጠቀም በምሳሌው መሠረት አምስት አምስት ቃላት መሥርቱ።

ምሳሌ፡- 1. ድንጋይ - ኣማ = ድንጋያማ 2. ሆድ - ኣም = ሆዳም

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ?

ለ. ስለባህላዊ ጨዋታዎች የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ግለጹ?

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. የባህላዊ ስፖርት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. የባህላዊ ስፖርትና ጨዋታዎች ጥቅም ምን ምን እንደሆኑ ግለጹ።

ሐ. ከባህላዊ የስፖርት ዓይነቶች መካከል ልዩ የሆነ የአለባበስ ሥርዓት ያለው የቱ ነው? ለምን?

### ቃላት

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ።

ሀ. ጉግስ ለ. ትግል ሐ. ገበጣ መ. ገና ሠ. ዋና ረ. ልቅሞሽ

## መጻፍ

የምትወዱትን አንድ የባህላዊ ስፖርት ጨዋታ መርጣችሁ ለምን እንደምትወዱት ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሁለት አንቀጾች ጻፉ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ስፖርት ለሰላም

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. ተማሪዎች በባህላዊ ስፖርቶች ለመወዳደር ያስቻላቸውን ሐሳብ ያፈለቀው ማን ነው?

ለ. የስፖርት ውድድሮች ለተማሪዎችና ለአካባቢው ልጆች ምን ጥቅም አስገኙ?

ሐ. ከምንባቡ ምን ተገነዘባችሁ?

## መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎቹን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ተራራማ    ለ. ጥርሳም    ሐ. አሸዋማ    መ. አለታማ

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

   ሀ. በዘመናዊና በባህላዊ ስፖርት ጨዋታዎች መካከል ምን ልዩነት አለ?

   ለ. ስፖርት ለአንድ አገር ሕዝብ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

   ሀ. "የባህላዊ ስፖርት ጨዋታዎችን" ለትውልድ ለማስተላለፍ ምን መደረግ አለበት?

   ለ. የፈረስ ጉግስ ባህላዊ ጨዋታ ሥርዓት ምን ዓይነት ነው?

## ቃላት

1. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቺ ጻፉ፡፡

   ሀ. ተጋጨ    ለ. ጣለ    ሐ. ጋለበ    መ. ቀዳሚ    ሠ. ተሸነፈ    ረ. መለሰ

2. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

   ሀ. ጀመረ    ለ. ጎዳ    ሐ. ማጓጓ    መ. አዘወተረ    ሠ. ለጋ

## መጻፍ

"የባህላዊ ስፖርት ጨዋታዎች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋና መልዕክት በራሳችሁ አባባል በስድስት ዐረፍተነገሮች ጽፉችሁ አንብቡ፡፡

# 17ኛ ሳምንት

## ግለ ንባብ

### የሰፈሬ ልጆች




ጊዜው 2000 ዓ.ም. ዕለቱ ኃይሌ ገብረሥላሴ በበርሊን ከተማ የማራቶን ውድድር የሚያደርግበት ነበር፡፡ እኔና የሰፈሬ ወጣቶች በየቤታችን ቴሌቪዥን ስለሌለ፣ በእማማ ትርንጎ ቤት ወለል ላይ ተኮልኩለናል፡፡ የእነኃይሌ የሩጫ ውድድር ተጀመረ፡፡ በቤቱ ውስጥ ያለነው ሁላችንም ኃይሌ ሲቀድም ከመቀመጫችን ቁጭ ብድግ እያልን በቴሌቪዥን መስኮት ላይ አፍጠናል፡፡ በመጨረሻም፣ ኃይሌ ከሯጮች መሃል አፈትልኮ በመውጣት በ2፡03፡59 ሰዓት አሸናፊ ሆነ፡፡ ሁላችንም በአንድነት ዘለልን፤ የደስታ እንባም አነባን፡፡

✶✶✶ "መቀመጫ ላይ እንዳሉ መቁነጥነጥ የምን ምልክት ነው?
የደስታ እንባ አነቡ ሲል ምን ማለት ነው?" ✶✶✶

ከጎኔ የተቀመጡትን ወጣቶች፣ "ደስ አይልም?" አልኳቸው፡፡ እነሱም፣ "ከዚህ የበለጠ ደስታ ምን አለ?" አሉኝ፡፡ "እንግዲያውስ፣ እኛስ ለምን በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች ልምምድ አናደርግም?" አልኳቸው፡፡ ሁለተኛው ልጅ፣ "በምን በምን ዓይነት?" አለ፡፡ ሦስተኛው ልጅ፣ "የሰፈሮቻችንን ወጣቶች ሰብስበን እንደየችሎታችን፤ በእግር ኳስ፣ በመረብ ኳስ፣ በቅርጫት ኳስ፣ በጠረጴዛ ቴኒስ፣ በአካል እንቅስቃሴ፣ በክብደት ማንሣት፣ በሩጫ፣ በውርወራ፣ በዝላይ፣ በቦክስ፣ በትግል፣ በዋና፣ በገመድ ጉተታ ወይም በብስክሌት መለማመድ እንችላለን" አለ፡፡ ሁለተኛው ልጅ፣ "ችሎታችንን ማን ገምግሞ እንደየችሎታችን ይመድበናል?" እኔም፣ "እሱ ችግር የለውም፤ የሰፈራችን ጎበዝ የስፖርት መምህር ጋሼ ቀለሙን እናስቸግራቸዋለን" አልኳቸው፡፡ መምህሩም ፈቃደኛ በመሆን በየችሎታችን መደቡን፡፡ በየተመደብንበትም ልምምድ በመጀመራችን ትርፍ ጊዜያችንን ለስፖርታዊ ተግባር ማዋል ቻልን፡፡ ልምምዳችን ቀጠለ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን በወረዳችን በተከናወነው የስፖርት ውድድር ተሳታፊ ሆንን፡፡

ከመካከላችን ሁለት ወንድና ሦስት ሴት ወጣቶች በሩጫ፣ በእግር ኳስ፣ በውሃ ዋና፣ በዝላይ፣ በብስክሌት አሸናፊ ሆኑ፡፡ የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ዋንጫዎች ተሸለሙ፡፡ የሰፈሩ ሰው አጨበጨበላቸው፡፡ የደስታ እንባ ከዓይናቸው ዱብ ዱብ አለ፡፡

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## ዘመናዊ ስፖርት

### ቃላት

1. ለተሠመረባቸው ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ፡፡
   ሀ. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ለጤና ይጠቅማል፡፡
   ለ. ከአለው ባሕርይ አንጻር ልጁ ተወዳጅ ነው፡፡
   ሐ. እግር ኳስ ጨዋታ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አተረፈ፡፡
   መ. የሌሎችን መብት ማክበር ይገባል፡፡
2. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጧቸው፡፡
   ሀ. ብቃት ለ. ባህርይ ሐ. አተረፈ መ. ማክበር ሠ. ዘመናዊ

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት መድረሻ ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ረግረጋማ ለ. ልባም ሐ. ዝናባማ መ. ሰንሰለታማ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡
   ሀ. ርዕሱ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?
   ለ. ጥሩ ሯጭ ለመሆን ምን መሟላት አለበት?
2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶችን በጽሑፍ ስጡ፡፡
   ሀ. ሰዎች በስፖርት ውድድር ፍፃሜ ለምን ያለቅሳሉ?
   ለ. በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀሱ የስፖርት ውድድር ዓይነቶችን ዘርዝራችሁ ጻፉ፡፡
   ሐ. የሠፈሩን ወጣቶች በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች የመደባቸው ማን ነው?

### ቃላት

1. የሚከተሉትን የስፖርት ዓይነቶች የአጨዋወት ሥርዓት በቃላችሁ አብራሩ፡፡
   ሀ. የጠረጴዛ ኳስ ለ. የመረብ ኳስ ሐ. የእግር ኳስ መ. የቅርጫት ኳስ

2. በሚከተሉት ቃላትና ሐረግ ዓረፍተነገሮችን ሥርታችሁ ዐውዳዊ ፍቻቸውን በጽሑፍ ግለጹ፡፡

ሀ. ተኮለኮሉ ለ. ተፈተለከ ሐ. ዱብዱብ መ. የደስታ እንባ

## መጻፍ

በቅርጫት ኳስና በመረብ ኳስ ጨዋታዎች መካከል ያለውን ልዩነት የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ዘመናዊ ስፖርት

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. የመረብ፣ የቅርጫትና የጠረጴዛ ኳስ ጨዋታዎችን ልዩ የሚያደርጓቸው ምን ምን ናቸው?

ለ. “ሩ.ው.ዝ.” የሚለው ምኅጻረቃል የሚያካትታቸው የስርፖት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን በቃል አብራሩ፡፡

ሀ. የሚያስተሳስር ሐ. እርካታ ሠ. ስያሜ

ለ. በራስ መተማመን መ. ማቀራረብ

## ማጣመርና መነጠል

1. የሚከተሉትን ቃላት መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጣጥላችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ስለአንድነት ሐ. በዓይናቸው

ለ. ወደሰፈራችን መ. እንደጕረቤታችን

2. “-ኣማ”፣”-ኣም”፣ “-ኧኛ”፣ “-ተኛ” የሚሉ የመድረሻ ቅጥያዎች ያሏቸውን ስድስት ስድስት ቃላት ጽፋችሁ አንብቡ፡፡

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. የሰፈሩ ወጣቶች በእማማ ትርንጎ ቤት የተሰበሰቡት ለምንድን ነው?

ለ. በአካል እንቅስቃሴና በክብደት ማንሳት መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. "ወርቅ፣ ብርና ነሐስ" በስፖርት ውድድር ውስጥ ምን አገልግሎት አላቸው?

ለ. የሰፈሩ ሰዎች ለተወዳዳሪ ስፖርተኞች ያጨበጨቡላቸው ለምንድን ነው?

ሐ. በ2000 ዓ.ም. ኃይሌ ገብረሥላሴ የማራቶን አሸናፊ የሆነበት ከተማ ማን ይባላል?

መ. ተወዳዳሪ ስፖርተኞችን መምረጥ የሚችል ሰው ምን ዓይነት ነው?

### ቃላት

1. ቀጥሎ ባሉት ዐረፍተነገሮች የተሠመረባቸውን ቃላት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ሀ. ልምምዳቸውን <u>ቀጠሉ</u>።

ለ. የሰፈሩ ሰዎች <u>አጨበጨቡ</u>።

ሐ. ከመሐል <u>ተፈትልኮ</u> ወጣ

መ. ወጣቶች በተለያዩ ስፖርት ውድድሮች <u>ተሳታፊ</u> ሆኑ።

2. ከምንባቡ ለወጡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በጽሐፍ ስጡ።

ሀ. ደስታ ለ. ወጣት ሐ. ከባድ መ. መሀል ሠ. ተሳታፊ

### መጻፍ

የምንባቡ ባለታሪኮች የፈጸሟቸውን ድርጊቶች በቡድን ሆናችሁ በቅደምተከተል ጽፋችሁ አንብቡ።

18ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች




በቀዳሚዎቹ የኢትዮጵያ ታዋቂ አትሌቶች አማካይነት ኢትዮጵያ በዓለም የታወቀችበት የአትሌቲክስ ድል በመካከል ቀዝቀዝ ያለ ቢመስልም፣ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ መሰረት ደፋር፣ ቀነኒሳ በቀለ ዳግም ሕይወት ከዘሩበት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

ኃይሌ ገብረስላሴ በ10 ሺህ ሜትር የሁለት ጊዜ የኦሎምፒክ ባለድል ነው፡፡ ለአራት ተከታታይ ጊዜያት በበርሊን፣ ለሶስት ጊዜያት በዱባይ ክብረወሰኖችን በማስመዝገብ የርቀቱ ንጉስ ለመባል በቅቷል፡፡

✶✶✶ "ኃይሌ ገብረሥላሴ የርቀቱ ንጉሥ ለመባል የበቃው በምን ምክንያት ነው?" ✶✶✶

"ፍልቅልቂ" በሚል ቅፅል ስም የምትጠራዋ ደራርቱ ቱሉ ደግሞ በአስደናቂ ብልሀት፣ በጽናትና በጠንካራ ልምምድ ከታጀበው ውብ አሯሯጧ ጋር ተፎካካሪዎቿን እንዳልነበሩ አድርጋ የማሸነፍ ብቃት ያላት ድንቅ አትሌት ነች፡፡ ዓለማቀፋዊ ድል መጀመሪያ ያገኘችው በትራክ ወይም በመም ውድድር ነው፡፡ እ.አ.አ. በ1990 ዓ.ም. በቡልጋሪያዋ ፕሎቭዲቭ ከተማ በተካሄደው በታዳጊ ወጣቶች የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በ10 ሺህ ሜትር አንደኛ ወጥታ የመጀመሪያ የሆናትን ዓለምአቀፋዊ የወርቅ ሜዳሊያ አግኝታለች፡፡ እንዲሁም እ.አ.አ. በ1991 ዓ.ም. ቶክዮ ጃፓን ውስጥ በተካሄደው የአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በግማሽ ፍጻሜ 10 ሺህ ሜትር

በርቀቱ የኢትዮጵያን ክብረወሰን በመስበር የአለም የሴቶች ረጅም ርቀት ሩጫ ትኩረት ወደእሷ እንዲዞር አድርጋለች፡፡ እ.አ.አ. በ1992 ዓ.ም. በሶስት የ10 ሺህ ሜትር ውድድሮች ስታሸንፍ ከባርሴሎናው ኦሎምፒክ መጀመር ጥቂት ቀደም ብሎ በተካሄደው የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ርቀቱን በጊዜው የአህጉሪቷን ክብረወሰን ሰብራ አንደኛ በመውጣት የወርቅ ሜዳሊያ አግኝታለች፡፡

የሩጫ ፈርጥ የምትባለዋ ጥሩነሽ ዲባባም ለአምስት ጊዜያት ያህል የዓለም ኦሎምፒክ ባለክብረወሰን ነች፡፡ ሁለት የኦሎምፒክ ወርቆችን ለማጥለቅ የቻለችው ሌላዋ አትሌት ደግሞ መሠረት ደፋር ናት፡፡ በተለይም በ3 ሺህ ሜትርና በ5 ሺህ ሜትር በተደጋጋሚ ተሳትፋለች፤ አሸናፊም ሆናለች፡፡

ሌላው ድንቅ ብቃት ያለው አትሌት ደግሞ ቀነኒሳ በቀለ ነው፡፡ በ5 ሺህ ሜትርና በ10 ሺህ ሜትር የዓለም ኦሎምፒክ ክብረወሰን ባለቤት ሆኗል፡፡ ቀነኒሳ በአጨራረስ ብቃታቸውና በአይበገሬነታቸው ከሚታወቁት የዓለም አትሌቶች ተርታ ስሙ የሰፈረ አትሌት ነው፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ብርቅዬ አትሌቶች በሩጫው መስክ ኢትዮጵያን ከማስተዋወቅ አልፈው ለራሳቸውም ሆነ ለአገራቸው ዝናን ያተረፉ ናቸው፡፡ የእነሱን ፈለግ በመከተልም በተለያዩ ጊዜያት አመርቂ ድሎችን እያስመዘገቡ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በርካታ ናቸው፡፡

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የቀደምት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ገድል**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ፡፡**

ሀ. ከቀድሞ ኢትዮጵያውያን ሯጮች በጣም የምታደንቋቸው እነማንን ነው? ለምን?

ለ. “አትሌት” ማለት ምን ማለት ነው?

### ቃላት

**የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በቃል ተናገሩ፡፡**

ሀ. ማራቶን ለ. ሜዳሊያ ሐ. ብቸኛ መ. ወኔ

### መነጠልና ማጣመር

1. “-ኣዊ” የሚል መድረሻ ቅጥያ ያላቸውን አምስት ቃላት በምሳሌው መሠረት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

   ምሳሌ፡- ሀ. ዘመን - ኣዊ = ዘመናዊ ለ. አገር - አዊ = አገራዊ

2. የሚከተሉትን ቃላት መድረሻ ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

   ሀ. አሃዛዊ ለ. ጊዜያዊ ሐ. አመታዊ መ. አድሏዊ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት አጫጭር መልሶችን ስጡ፡፡**

ሀ. በ10ሺህ ሜትር ሩጫ ባለድል የሆኑት ሯጮች ማን ማን ናቸው?

ለ. ሁሉም በምንባቡ የተገለፁት አትሌቶች የረጅም ርቀት ሯጮች ናቸው ወይ?

### ቃላት

**በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ. ሯጭ ለ. ፈለግ ሐ. አንጋፋ መ. ፈርጥ ሠ. ፍልቅልቅ

### መጻፍ

በቡድን ሆናችሁ ከምታደንቋቸው ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አንድ በመምረጥ አድናቆታችሁን የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የቀደምት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ገድል**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።**

ሀ. "ማርሽ ቀያሪው" እየተባለ የሚጠራው አትሌት ማን ነው? ለምን ተባለ?

ለ. አበበ ቢቂላ በሜልቦርን ኦሎምፒክ በሕመም ሳቢያ ከውድድሩ አቋርጦ ሲወጣ አሠልጣኙ ምን አደረጉ?

### ቃላት

**የሚከተሉትን ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለፁ ።**

ሀ. አስታወሰ　　ለ. ፋናወጊ　　ሐ. ምኞት　　መ. ጀግና

### መነጠል

**የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያቸውን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ።**

ሀ. ኢትዮጵያውያን　　ለ. ዝናችን　　ሐ. አርአያነት

### መፃፍ

**"ልጁ ኀበዝ አይደለም" በሚለው ምሳሌ መሠረት አምስት ዓረፍተነገሮችን ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡ።**

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።**

ሀ. ጥሩ ሯጭ ለመሆን ምን የሚያስፈልግ ይመስላችኋል?

ለ. ለሴት አትሌቶች መበራከት ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሐ. ኃይሌ ገብረስላሴ "የሩጫ ንጉስ" ለምን ተባለ?

### ቃላት

**1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ።**

ሀ. አጠለቀ　　ለ. ሰፈረ　　ሐ. ደበዘዘ

**2. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ በገቡበት ዐውድ መሠረት ፍቻቸውን ጻፉ።**

ሀ. የማይረሳ ታሪክ　　ለ. ባለድል　　ሐ. ሕይወት ዘራ

### መጻፍ

**በቡድን ሆናችሁ ከኢትየጲያውያን አትሌቶች መካከል አንድ ወንድና አንድ ሴት መርጣችሁ አትሌቶቹን የሚገልፅ አንድ አንድ አንቀፅ ፅፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።**

19ኛ ሳምንት

# ግለንባብ

## መምህር በቃሉ

መምህር በቃሉ በአንድ ወቅት የአንድ ትምህርትቤት የአራተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ መምህር ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው ክፍለጊዜ የርሳቸው ነበር፡፡ "እንደምን አደራችሁ ተማሪዎች?" አሉ፡፡ ተማሪዎች ከመቀመጫቸው ተነሥተው፣ "እንደምን አደሩ መምህር?" አሏቸው፡፡ ሰሌዳውን በዳስተር አጸዱ፡፡ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ጻፉ፡፡ የዕለቱ ትምህርት ርዕስ "የውሃ መገኛዎች" የሚል መሆኑን ጠቁመው ለመግቢያ ያህል ትንሽ ገለጻ ከሰጡ በኋላ ለተማሪዎች የሚከተለውን ጥያቄ አቀረቡ፡፡

"ልጆች ለመሆኑ ውሃ ከምን ይገኛል?"

ተማሪዎች የተወሰኑትን ዘረዘሩ፡፡ "በጣም ጥሩ ነው ልጆች!" አሉ መምህር በቃሉ፡፡ "ውሃ ሕይወት ላላቸው ሁሉ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ከምድራችን ¾ኛው ክፍል በውሃ የተሸፈነ ነው፡፡ ውሃ ከዝናብ፣ ከጉድጓድ፣ ከምንጭ፣ ከሐይቅ፣ ከባሕር፣ ከውቅያኖስ ይገኛል" አሉ፡፡

✶✶✶ "ዝናብ እንዴት ይገኛል ብላችሁ ትገምታላችሁ?" ✶✶✶

"ውሃ ከተለያዩ ውሃማ አካላት በፀሐይ ሙቀት ምክንያት ይተናል፡፡ ይህም የትነት ውሃ ሞቃትና ቀላል ስለሆነ ወደከፍተኛ ቦታ በመጓዝ ከባቢ አየር ውስጥ ይገባል፡፡ ከዚያም ወደደመናነት ይለወጣል፡፡ ቆይቶም ወደዝናብነት ይለወጣል፡፡"

ጥያቄዎችን ለተማሪዎች እያቀረቡ፣ ተማሪዎችንም እያሳተፉ ማስተማራቸውን ቀጠሉ፡፡

"የዝናብ ውሃ ከትነትና ከሌሎች ተፈጥሯዊ ሂደቶች የሚገኝ በመሆኑ ጨውነት የለውም፡፡ ሌሎች የውሃ መገኛዎች ግን ጨውና ሌሎች ጠቃሚ ማዕድናት ሊኖራቸው ይችላል" አሉና፣ "የዛሬው ትምህርታችን በዚህ አብቅቷል፤ ያልገባችሁ ነገር ካለ መጠየቅ ትችላላችሁ" አሏቸው፡፡ ተማሪዎችም "ግልጽ ነው መምህር" አሉ፡፡ ተማሪዎች በተሰጣቸው ትምህርት ስለረኩ መምህሩ ደስ አላቸው፡፡ ተማሪዎችም ያላወቁትን አወቁ፡፡ ባገኙት እውቀትም በጣም ደስተኞች ሆኑ፡፡

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

### የውሃ መገኛዎች

### ቃላት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት መርጣችሁ በክፍት ቦታው በማስገባት ዓረፍተነገሮችን አሟልታችሁ ፃፉ። (ቀለጠ፣ ኩሬ)

ሀ. በጎድጓዳ ቦታ ላይ ተጠራቅሞ የሚገኝ ውሃ __________ ተብሎ ይጠራል።

ለ. በረዶው በፀሐይ ሙቀት __________።

### ማጣመርና መነጠል

"-ኣዊ" "-ኣማ" "-ኣም" የሚሉ ቅጥያዎች ያለባቸውን አምስት አምስት ቃላት ፈልጋችሁ ቅጥያውን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ አሳዩ።

ምሳሌ፡- ኢትዮጵያ - ኣዊ = ኢትዮጵያዊ

ድርጅት - ኣዊ = ድርጅታዊ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ርዕሱ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ።
2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ተገቢ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. መምህር በቃሉ ለተማሪዎቻቸው ያቀረቡት ትምህርት ምንድን ነው?

ለ. ውሃ የሚተነው በምን ምክንያት ነው?

ሐ. የውሃ ትነት መኖር ለዝናብ መፈጠር ምን አስተዋጽኦ አለው?

### ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ለጓደኞቻችሁ በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. ጉድጓድ ለ. ባሕር ሐ. ዝናብ መ. ሐይቅ ሠ. ወንዝ ረ. ጅረት

2. በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት አስተካክላችሁ ዓረፍተነገሮችን በማሟላት ጻፉ።

ሀ. ተማሪው ጥቁር ሰሌዳውን (ማጽዳት)።

ለ. ስለጤና አጠባበቅ ለተማሪዎች (አገላለጽ) ተደረገላቸው።

ሐ. በክልላችን ጠቃሚ (ማዕድን) ይገኛሉ::

መ. በተሰጣቸው ትምህርት (መርካት) በጣም ደስ አላቸው::

ሠ. (ምድር) ብዙው ክፍል ውሃማ ነው::

## መጻፍ

በቡድን ሆናችሁ "የውሃ ጥቅም" በሚል ርዕስ ሦስት አንቀጾችን ጻፉ::

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የውሃ መገኛዎች

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን ስጡ::

ሀ. ግግር በረዶ እንዴት ይፈጠራል? ለ. በአገራችን የሚገኙትን ሐይቆች ዘርዝሩ::

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ::

ሀ. ምንጭ ለ. ጥልቀት ሐ. ተከማቸ መ. ግግር ሠ. ዋስትና

## ማጣመር

1. "-ኣዊ"፣ "-ኣማ"፣ "-ኦች፣" "-ዎች" ቅጥያ ያሉባቸውን ስምንት ቃላት "መምህር በቃሉ" ከሚለው ምንባብ በማውጣት ጻፉ ::
2. አምስት አወንታዊና አምስት አሉታዊ ዓረፍተነገሮችን ጽፋችሁ አንብቡ::

   ምሳሌ፡- ከበደ ምሳ በላ:: → ከበደ ምሳ አልበላም::

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ::

   ሀ. "የውሃ ማማ" ማለት ምን ማለት ነው?

   ለ. የውሃና የሕይወት ግንኙነት ምንድን ነው?
2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ::

   ሀ. ምንጭ ከጅረት በምን ይለያል?

   ለ. ከምድራችን በውሃ የተሸፈነው ቦታ ምን ያህል ነው?

## ቃላት

1. በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላት ዐውዳዊ ፍቻቸውን በጽሁፍ ስጡ።

   ሀ. ውሃ በፀሐይ ሙቀት ይተናል።

   ለ. የውሃ መገኛዎች ብዙ ናቸው።

   ሐ. ውሃ ጠጥተው ጥማቸውን አረኩ።

   መ. ከምድራችን ብዙው ክፍል ውሃ ነው።

2. የሚከተሉትን ቃላት የመዝገበቃላት ፍቻቸውን ጽፋችሁ አንብቡ።

   ሀ. ቆየ ለ. ተለወጠ ሐ. ሰሌዳ መ. አጠፋ

## መጻፍ

ውሃ በቤት ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጻፉ።

# 20ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### የውሃ ጥቅም

ውሃ ባለበት ሕይወት አለ፤ ሕይወት የሚኖረው በተለያዩ የውሃ ጥቅሞች ላይ ተመስርቶ ነው። በመሆኑም ውሃ ለሕይወት አስፈላጊ ነገር ነው። ለተክሎች እድገት ውሃ ያስፈልጋል። ተክሎች ከሌሉ ሰዎችና እንስሳት ምግብ ለማግኘት ይቸገራሉ። ሰዎች ውሃን ለመስኖ፣ ለመጠጥና ለሌሎችም ተግባራት ይጠቀማሉ። በመሆኑም ውሃ ለሰዎች፣ ለተክሎችና ለእንሳስት ሕይወት መሰረት ነው። ለዚህም ነው “ውሃ ባለበት ሕይወት አለ” የሚባለው።

የህዝብ ቁጥር እየጨመረ በሄደ ቁጥር የሰው ልጅ የውሃ ፍላጎትም እየጨመረ ይሄዳል። በምድራችን ያለው ውሃ በቤት ውስጥና ከቤት ውጪ በሚሰጠው አገልግሎት መሰረት ይወሰናል። በከተማና በገጠር አካባቢዎች ውሃ ለግል ንፅህና ለምግብ ማዘጋጃ፣ ለመጠጥ፣ ለአካባቢና ለመፀዳጃቤት ንፅህና አገልግሎት ይውላል።

✶✶✶ “ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ውሃ ለምን ለምን አገልግሎት ይውላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?” ✶✶✶

ከዚህ በተጨማሪ በገጠር አካባቢ የአትክልት፣ የፍራፍሬ፣ የጥራጥሬ ወዘተ ምርቶች ለማግኘት የመስኖ ውሃ ጠቃሚ ነው። በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች ስልሳ ዘጠኝ በመቶውን ውሃ ለመስኖ ስራ ይጠቀሙበታል። ውሃን በሁለት መንገድ ለመስኖ አገልግሎት መጠቀም ይቻላል። አንደኛው የጠብታ መስኖ ሲሆን ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ቢሆንም ውሃ ቆጣቢ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በቦይ መጠቀም ነው፤ ይህ ዓይነቱ ዘዴ ከፍተኛ ወጪ የማይጠይቅ ቢሆንም ውሃን ግን ያባክናል።

ሃያ ሁለት በመቶው የምድራችን ውሃ ለኢንዱስትሪ፣ ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫነትና ለሌሎችም አገልግሎቶች በጥቅም ላይ ይውላል። ይህም ውሃ ለሰው ልጆች ያለውን አስፈላጊነት በግልፅ ያሳያል።

በአጠቃላይ ውሃ ለሰው ልጅ በጣም ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል። ስለሆነም በተለይ ለመጠጥ አገልግሎት የሚውለው ውሃ እንዳይበከልና ለጤና ጠንቅ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### የውሃ መሀንዲሷ ትምህርት

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ተገቢ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ፡፡

ሀ. ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት በጥቅሉ ምን ምን ናቸው?

ለ. የምንባቡ ዋና ዋና ሐሳቦች ምን ምን ናቸው?

### ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ተገቢ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. ማሚሚት ለ. ማመንጨት ሐ. ክምችት መ. ተጋለጡ

### መነጠል

የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ዘመናዊነት ለ. ወርሃዊ ሐ. ቆላማ መ. ቀለማም

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. ውሃ ለምን ይጠቅማል?

ለ. በአንድ አካባቢ በቂ ውሃ ከሌለ የሚከሰቱ ችግሮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

ሐ. የዓለማችን ሕዝብ ብዙውን ውሃ ለምን አገልግሎት ይጠቀማል?

### ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ፍቻቸውን ከሰው ጠይቃችሁ ለጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አስረዱ፡፡

ሀ. ሕይወት ለ. መበከል ሐ. ጠንቅ መ. ኃይል

### መጻፍ

ውሃ ከቤት ውጭ ስላለው ጠቀሜታ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን ተጠቅማችሁ ሁለት አንቀፆች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

## 3ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**የውሃ መሀንዲሷ ትምህርት**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. አዛውንቱ "ውሃ ቢደርቅ ዓሣ ያልቅ" ሲሉ ምን ለማስረዳት ፈልገው ነው?

ለ. ወንዞችን በአግባቡ ለመጠቀም ምን መደረግ አለበት?

ሐ. በተበከለ ውሃ የሚመጡ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?

### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን በአጫጭር ዐረፍተ ነገሮች ግለጹ።

ሀ. ኃይል ማመንጫ
ለ. ግብርና
ሐ. ጥንቃቄ
መ. ውሃ ማከም
ሠ. ውሃ ማጠራቀም

### መነጠል

በሚከተሉት ቃላት ያሉ ቅጥያዎችን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ።

| ቅጥያ ያላቸው ቃላት | ቅጥያ | ዋና ቃል |
|---|---|---|
| ከርሳም | | |
| ሀገራዊ | | |
| ዓይናማ | | |
| መልካም | | |
| ቤተሰባዊ | | |
| ሰማያዊ | | |

### መፃፍ

አምስት አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገሮችን ጽፋችሁ አንብቡ።

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።
   ሀ. የውሃ ብክለትን እንዴት መከላከል ይቻላል?
   ለ. በመስኖ ውሃ ምን ምን ማብቀል እንችላለን?
   ሐ. ከምድራችን ሃያሁለት ከመቶ የሚሆነው ውሃ ለምን አገልግሎት ይውላል?
2. ምንባቡን መሠረት አድርጋችሁ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።
   ሀ. ውሃ ባይኖር በሰው ልጆች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ምን ምን ናቸው?
   ለ. ተክሎች የሚጠወልጉት በምን ምክንያት ነው?
   ሐ. ሁለቱ የመስኖ አጠቃቀም ዘዴዎች ምን ምን ይባላሉ?

## ቃላት

1. ለተሠመሩት ቃላት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ስጡ።
   ሀ. የጠብታ መስኖ ውሃ <u>ቆጣቢ</u> ነው።
   ለ. ውሃ ለኃይል <u>ማመንጫ</u> ያገለግላል።
2. በሚከተሉት ቃላት ዐረፍተነገሮችን ፃፉ።።
   ሀ. ማፅዳት ለ. መሠረት ሐ. ቦይ መ. መንገድ

## መጻፍ

የውሃን ንጽሕና እንዴት መጠበቅና መንከባከብ እንዳለብን የሚያስረዱ ሁለት አንቀፆች ጽፋችሁ አንብቡ።

21ኛ
ሳምንት

# ግለንባብ

## ጤናማ አካባቢን መፍጠር



በአንድ የገጠር አካባቢ የነዋሪዎች ትልቁ ችግር በውሃወለድ በሽታዎች መጠቃት ነበር። በአካባቢው የሚገኘው ጤናጣቢያ ባለሙያዎች ያስተዋሉትም ይህንኑ ነበር። የጤና ጣቢያው ሠራተኞች ሁልጊዜ ጧት ጧት ለታካሚዎች ትምህርት ይሰጣሉ።

አንድ ቀን ጧት የጤና ባለሙያዎች፣ "የዛሬው ትምህርት ርዕስ የውሃ ብክለትና የሚያስከትለው ችግር ይሆናል" አሉና ማብራሪያቸውን ጀመሩ። "ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ" በሚለው አባባል ጀመሩና ጥያቄያቸውን አስከተሉ።

✶✶✶ "መምህሩ ቀጥለው ምን የሚሉ ይመስላችኋል?" ✶✶✶

"ለመሆኑ የውሃወለድ በሽታ የሚመጣው በምንድን ነው?" ብለው ንግግራቸውን ቀጠሉ። "በሽታ በተለይም የውሃወለድ በሽታ የሚመጣው በውሃ ብክለት ነው። የውሃ ብክለት መንስኤዎች ደግሞ ከቤት ውስጥ የሚወጣ ቆሻሻ፣ ከፋብሪካና ከኢንዱስትሪ የሚለቀቅ ፍሳሽና ተረፈ ምርት ዋናዎቹ ናቸው። የሰው አይነምድርና ሽንት፣ የእንስሳት እበት፣ ፋንድያና ሽንት ከውሃ ጋር

ሲቀላቀሉ የውሃ ብክለትን በማስከተል ለተቅማጥና ለሌሎች ውሃወለድ በሽታዎች ይዳርጋሉ። በመሆኑም የውሃ ብክለት ትልቅ የጤና ችግር ነው" አሉ።

"የተበከለ ውሃ የሚያስከትለው ሌላው ችግር ምንድን ነው?" ንግግራቸውን ቀጠሉ። "የሐይቅ፣ የባሕር ውሃ ከተበከለ በውሃ ውስጥ የሚኖሩና ለምግብነት የሚያገለግሉ እንደዓሣ ያሉ ፍጥረታት ይጠፋሉ፤ ይሞታሉ። ዕፅዋት ይጠወልጋሉ፤ ይደርቃሉ። ይህም የምግብ እጥረትን ያስከትላል።

ውሃ ከተበከለ ለመጠጥ ጥቅም አይውልም። ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ሳይንሳዊ የማጣሪያ ዘዴን በመጠቀም ነው። ይህን ለማድረግ ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል። በመሆኑም፣ ውሃን መበከል የውሃ ብክነትን ያስከትላል። የውሃ ብክነትም የውሃ እጥረትን ሊያስከትል ይችላል። ውሃን አላግባብ መጠቀም፣ መሬቱን ቁልቁል ማረስ፣ የክረምት ውሃን አለማጠራቀም የውሃ ብክነት መንስኤዎች ናቸው።

የውሃ ብክለትን ለመከላከል በካይ ነገሮች ከምንጮችና ከወንዞች እንዳይቀላቀሉ ማድረግ፣ በውሃማ አካባቢዎች ቆሻሻ አለመድፋት፣ የፋብሪካ ቆሻሻን ከውሃማ አካላት ጋር አለመቀላቀል፣ መጸዳጃ ቤቶችን ከውሃ ማራቅ፣ በውሃ አካባቢ አለመጸዳዳት ተገቢ ነው" በማለት ገለጻቸውን ቋጩ። ትምህርቱን በተከታታይ በመስጠታቸውና የውሃ ብክለት መጠን በመቀነሱ በውሃወለድ በሽታ ወደጤና ጣቢያ የሚመጡ ታካሚዎች ቁጥር ቀነሰ።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### የውሃ ብክለት መንስኤዎች

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶችን በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ ስጡ።**

ሀ. የውሃ ብክለት ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ለውሃ ብክለት መንስኤዎች ምን ምን ናቸው? ዘርዝሯቸው።

ሐ. የጽሑፉን ዋና ሀሳብ በአራት ዓረፍተነገሮች ግለጹ።

### ቃላት

**ለሚከተሉት ቃላት ዓውዳዊ ፍቻቸውን በቃላችሁ ስጡ።**

ሀ. ተዘዋዋሪ  ለ. ውሃወለድ  ሐ. ፍሳሽ  መ. መልቀቅ

### ማጣመር

**ለሚከተሉት ቃላት ተስማሚ መድረሻ ቅጥያዎች መርጣችሁ በመጨመር ቃላቱን እንደገና ጻፉ።**

| ቃላት | ቅጥያዎች | ምሥርት ቃል |
|---|---|---|
| ዓለምአቀፍ | | |
| ቀለም | | |
| ስስት | -ኣማ-ነት | |
| ልብ | -ኣም-ነት | |
| ሰንሰለት | -ኣዊ-ነት | |
| ክልል | | |
| ውሃ | | ውሃማነት |

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

**ለጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ አቅርቡ።**

ሀ. ውሃ እንዳይበከል ምን ማድረግ ይገባል?

ለ. በጤና ጣቢያዎች ለታካሚዎች ቁጥር መቀነስ ምክንያቶቹ ምን ምን ናቸው?

ሐ. የተቅማጥ በሽታ እንዴት ይከሰታል?

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ሀ. ብክለት ለ. ግዴለሽነት ሐ. አላግባብ

## መጻፍ

"የአካባቢ ንጽሕና አጠባበቅ" በሚል ርእስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሁለት አንቀጾችን በቡድን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የውሃ ብክለት መንስኤዎች

በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ ተገቢ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. እንስሳት ውሃን እንዴት ሊበክሉ ይችላሉ?

ለ. በውሃ ብክለት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት?

ሐ. ንጹሕ ውሃ የምንለው ምን ዓይነት ነው? አብራሩ።

## ቃላት

በ"ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ"ለ" ረድፍ ተስማሚያቸውን በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መኖሪያ | ሀ. መቆሸሽ |
| 2. አካል | ለ. የውሃ መፋሰሻ |
| 3. ቦይ | ሐ. መጠለያ |
| 4. ብክለት | መ. ተንቀሳቃሽ |
| 5. ተዘዋዋሪ | ሠ. ሰውነት |

## መነጠል

የሚከተሉትን ባለ ቅጥያ ቃላት ቅጥያዎቻቸውን ከዋናው ቃል ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. መምህሮች ሐ. አስተማሪዎች ሠ. ጤናማ

ለ. አካላዊ መ. እንደቦታው

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።
   ሀ. "ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ" የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ምን ያስገነዝበናል?
   ለ. ውሃ ተበከለ የምንለው ምን ሲሆን ይመስላችኋል?
2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።
   ሀ. ውሃን የሚበክሉ ሰውሠራሽ ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ ባጭሩ ግለጹ።
   ለ. ለዓሣዎች መሞት ወይም ቁጥር መቀነስ ምክንያቶቹ ምን ምን ናቸው?
   ሐ. በውሃ ብክለት ሳቢያ ምን ሊከሰት ይችላል?

## ቃላት

ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረግ ዐውዳዊ ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ።

ሀ. ከአካባቢው <u>የሚለቀቅ</u> ፍሳሽ በጉድጓድ ውስጥ መጠራቀም አለበት።

ለ. ከኢንዱስትሪዎች የሚወጣው <u>ተረፈ ምርት</u> በተገቢው ቦታ መቀመጥ አለበት።

ሐ. መሬትን <u>ቁልቁል</u> ማረስ አፈርን ለጐርፍ አደጋ ያጋልጣል።

መ. የውሃ <u>እጥረት</u> እንዴት ይከሰታል?


## መጻፍ

"የውሃ ብክለት መንስኤዎች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋና መልዕክት ተገቢ ስርዓተነጥቦችን በመጠቀም በሁለት አንቀጾች አሳጥራችሁ ጻፉ።

# 22ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### የመገናኛ ብዙኀን ዓይነቶች



መገናኛ ብዙኀን ለሰው ልጆች የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች ናቸው:: በአንድ ጊዜ በርካታ መረጃዎችን ለበርካታ ሰዎች ያሰራጫሉ፤ እንዲሁም ተፈላጊ መረጃዎችን ከበርካታ ሰዎች ለመቀበልም ያስችላሉ:: ከመገናኛ ብዘኀን ዓይነቶች መካከል ሬድዮንን፣ ቴሌቪዥንን፣ ጋዜጣን፣ መፅሄትንና በራሪ ወረቀቶችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል::

ሬዲዮ የዕለትና የሰአታት ዜናዎች፣ አዋጆች፣ ማስታወቂያዎች፣ መግለጫዎች፣ ትምህርታዊ መልዕክቶች፣ ሙዚቃዎች ወዘተ ይተላለፋበታል:: በሬዲዮ የሚተላለፉት ሁሉም መረጃዎች በጆሮ የሚደመጡ ስለሆኑ ለተማሩም ሆነ ላልተማሩ ሰዎች እኩል ይሰራጫሉ::*

ቴሌቪዥንም እንዲሁ በሬዲዮ የሚተላላፉት መረጃዎች ሁሉ ይተላለፋበታል:: ሆኖም ቴሌቪዥን ከሬዲዮ የሚለየው መረጃዎችን በሁለቱም በድምፅና በምስል የሚያቀርብ በመሆኑ ነው:: በዚህም የተነሳ በበርካታ ሰዎች ተመራጭ ሊሆን ይችላል::

ጋዜጣ፣ መፅሄትና በራሪ ወረቀቶች ደግሞ ሁሉንም መረጃዎች በድምፅ ሳይሆን በህትመት የሚያስተላልፉ በመሆናቸው የህትመት የመገናኛ ዘዴዎች ይባላሉ:: በነዚህ የመገናኛ ዘዴዎች አማካይነት ተገቢ መረጃዎችን ለማግኘት ግን በትንሹ መረጃዎቹ በሚታተሙባቸው ቋንቋዎች የማንበብ ችሎታ እንዲኖር ያስፈልጋል:: ጋዜጣ በአብዛኛው በእለት፣ አልፎ አልፎም በሳምንት መረጃዎችን ለአንባቢዎች ያደርሳል:: በጋዜጣ ከሚተላለፉት መረጃዎች መካከል ዜና ዋነኛው ነው:: መፅሄት ግን እንደጋዜጣ ሁሉ መረጃዎችን በቀን ወይም በሳምንት አያስተላልፍም:: በመፅሄት የሚተላለፉት መረጃዎች እንደየሁኔታው በወር ወይም በሶስት ወይም በአራት ወር ወይም በመንፈቅ ወይም በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል:: በዚህም የተነሳ የመረጃዎቹ ዓይነቶች በጋዜጣ ከሚተላለፉት የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ:: የበራሪ ወረቀቶች ግን አጫጭር ትምህርቶች፣ አድራሻዎች፣ የተቋማት ዋና ዋና

አገልግሎቶች ወዘተ የሚተላለፉባቸው በመሆናቸው እንደመፅሄትና እንደጋዜጣ በጊዜ የተገደቡ አይደሉም።

ከላይ ከተጠቀሱት የመገናኛ ብዙኀን ዓይነቶች የሚለየው ኢንተርኔት ነው። ኢንተርኔት በፅሁፍ፣ በምስልና በድምፅ አማካይነት መረጃዎች እጅግ ፈጣን በሆነ መንገድ ይተላለፉበታል። የኢንተርኔት መረጃዎች በጊዜና በቦታ የተገደቡ አይደሉም። የተለያዩ ኮምፒዩተሮችንና የእጅ ስልኮችን በመጠቀም በመረጃ መረቦች አማካይነት መረጃዎችን ከየትኛውም የዓለም አገሮች በአጭር ጊዜ ማንኛውንም መረጃ ማግኘት ይቻላል። በዚህም የተነሳ ከሌሎቹ የመገናኛ ብዙኀን ዓይነቶች መካከል በቀዳሚነት ተመራጭ እየሆነ መጥቷል።

በአጠቃላይ መገናኛ ብዙኀን በሰው ልጆች መካከል የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር በማድረግ፣ ሰዎችን በማስተማርና በማዝናናት ወዘተ በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው። በተለይም በአሁኑ ጊዜ የመረጃዎች አስፈላጊነትና ጠቃሚነት እየጨመረ በመምጣቱ የመገናኛ ብዙኀን ተፈላጊነትም በዚያው መጠን ጨምሯል። በአሁኑ ጊዜ በመገናኛ ብዙኀን አማካይነት የዓለም ህዝቦች ይበልጥ እየተግባቡና እየተዋወቁ፣ ባህላቸውንና እውቀታቸውን እየተካፈሉ ይገኛሉ።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### የማይታየው ብርሃን

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ስልክ የተፈለሰፈው መቼ ነው?

ለ. ቴሌቪዥን ምን ዓይነት የመገናኛ መሣሪያ ነው?

ሐ. ሰዎች የተለያዩ መረጃዎችን የሚያገኙባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?

መ. ከመገናኛ ዘዴዎች "ጉድ" የተባለለት የመጀመሪያው ፈጠራ ምንድን ነው?

### ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. ግለሰባዊ ለ. አጣመረ ሐ. አሳየ መ. ብርሃን

### መነጠል

የሚከተሉትን ጥምር ቃላት በብዙ ቁጥር ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ወሬ ነጋሪ → ወሬ ነጋሪዎች

ሀ. ልብቢስ ለ. ሰርቶአደር ሐ. ቤተሰብ መ. ነገረፈጅ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልሶችን ጻፉ፡፡

ሀ. የመገናኛ ብዙኀን አገልግሎት ባይኖር ምን ችግር ሊያጋጥም የሚችል ይመስላችኋል?

ለ. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት የህትመት መገናኛ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ኢንተርኔት ለምን አገልግሎት ይውላል?

### ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ፡፡

ሀ. ድምፅ ለ. ቀዳሚ ሐ. ማዝናናት

2. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩባቸው፡፡

ሀ. ገደበ ለ. ማስተላለፍ ሐ. ምስል መ. መረጃ

### መጻፍ

በሬድዮና በጋዜጣ መካከል ያለውን የአገልግሎት አንድነትና ልዩነት የሚገልጽ አጭር ጽሑፍ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የማይታየው ብርሃን

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።

ሀ. የመገናኛ ብዙኀን ጠቀሜታዎች ምን ምን ናቸው?

ለ. ከቦታ ቦታ የሚተላለፈው የድምፅ ግብዓት ሌላው ስሙ ምንድን ነው?

## ቃላት

ቀጥለው ከቀረቡት ቃላት መርጣችሁ ክፍት ቦታዎችን አሟሉ።

| ታዳሚዎች፣ ምስል፣ አትኩሮት፣ ኮምፒዩተር፣ መረጃ |
|---|

ሀ. የስብሰባችን ________ ጠቃሚ አስተያየቶችን ሰጡ።

ለ. ታሪክ ለመጻፍ ተጨባጭ ________ ሊኖር ይገባል።

ሐ. ________ ዘመናዊ የመጻፊያ መሣሪያ ነው።

መ. የአድማጭን ________ የሚስብ ንግግር አደረገች።

ሠ. ትምህርትን በድምፅና በ________ አስደግፎ ማቅረብ ይጠቅማል።

## ማጣመር

1. የሚከተሉትን ጥምር ቃላት በብዙ ቁጥር ጻፉ።

| ዋና ቃል | ብዙ ቁጥር |
|---|---|
| መኖሪያቤት | |
| ሥራፈት | |
| ቃልአባይ | |
| ቃልአቀባይ | |
| ሥራወዳድ | |

2. የሚከተሉትን ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ጋር አጣምራችሁ ጻፉ።

ሀ. ስለ - ፈጠር - ኣችሁ ________ ለ. ከ - ሠራ - ህ ________

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. በሬዲዮ አማካይነት የሚተላለፉ መልእክቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. በሬዲዮ ማስታወቂያዎችን አዳምጣችሁ ታውቃላችሁ?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከተለመዱት የመገናኛ ብዙኀን የተለየው ምንድን ነው?

ለ. በጋዜጣና መጽሔት የህትመት መገናኛዎች መካከል ምን ልዩነትና አንድነት አለ?

ሐ. ሁሉም የማህበረሰብ አባላት በጋራ የሚገለገሉበት የመገናኛ ብዙሃን ምን ተብሎ ይጠራል?

መ. በቴሌቪዥንና በሬዲዮ መካከል ያሉትን ልዩነቶች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ አቅርቡ።

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ሀ. ኅትመት ለ. ተመራጭ ሐ. ማሰራጨት መ. ተቋም

2. ቀጥሎ ከቀረቡት ዐረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ፃፉ።

ሀ. መገናኛ ብዙኀን <u>የመልዕክት</u> ማስተላለፊያ መሳሪያዎች ናቸው። _______

ለ. መገናኛ ብዙኀን መረጃዎችን ከበርካታ ሰዎች <u>ለመቀበል</u> ያስችላሉ። _______

ሐ. የበራሪ ወረቀቶች መረጃዎች በጊዜ <u>የተገደቡ</u> አይደሉም። _______

መ. ቴሌቪዥን የተመልካቹን ስሜት <u>ይስባል</u>። _______


## መጻፍ

"የጋዜጣ ጥቅም" በሚል ርዕስ ባለሙያ ጠይቃችሁ አጭር ጽሑፍ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ ።

# 23ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ልበብርሀኖቹ



በአንድ ወቅት በሰውሰራሽ አደጋ ምክንያት ዓይናቸውን ያጡ ሁለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ነበሩ። የዓይናቸውን ብርሀን ያጡት በልጅነታቸው ነበር። ከልጅነታቸው ጀምሮ የስነፅሁፍና የተረት መፅሀፎችን እያነበቡና የሬዲዮ ፕሮግራሞችን እያዳመጡ አድገዋል።

✶✶✶ *"ዓይነሥውራን የሚያነቡት በምን መንገድ ነው? የሥነጽሑፍ ሥራዎችን ለህዝብ ማድረስ የሚያስችሉ የመገናኛ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?"* ✶✶✶

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በነበሩበት ጊዜ በብሬል የሚፅፏቸውን መጣጥፎች በትምህርትቤቱ ሚኒሚዲያ ያቀርቡ ነበር። የእነሱን የሚኒሚዲያ ዝግጅት ያዳምጡ የነበሩ የትምህርትቤቱ ማህበረሰብ አባላት አድናቆታቸውን በተለያዩ መንገዶች ይገልፁላቸው፣ "ልበብርሀኖቹ" እያሉም ያወድሷቸው ነበር። ዩኒቨርስቲ ከገቡ በኋላም በብሬል የተፃፉ ልቦለዶችንና ለትምህርታቸው የሚያስፈልጉ መፃህፍትን በመዳሰስ አንብበዋል። በድምፅ የተቀዱ በርካታ የልቦለድና የኢልቦለድ መፃህፍትንና መጣጥፎችን አዳምጠዋል።


የአንደኛ ዓመት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በነበሩበት ጊዜ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የስነፅሁፍ ውድድር ማስታወቂያ ማውጣቱን በሬዲዮ አዳመጡ። ማስታወቂያው ስራቸውን ለህዝብ ለማስተዋወቅ አነሳሳቸው። ዓይነስውራኑ በብሬል የፃፏቸውን ግጥሞችና አጫጭር ልቦለዶች በጓደኞቻቸው በወረቀት አጽፈው ለውድድር አቀረቡ። ከሳምንት በኋላ ውጤቱ በሬዲዮ ተነገረ። አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ በመውጣት ውድድሩን በማሸነፋቸው እያንዳንዳቸው አንዳንድ

ሬዲዮ ተሸለሙ፡፡ ይህም ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤታቸው የሚኒሚዲያ ቀጥሎ በስነፅሁፍ እውቅና ያገኙበት አጋጣሚ ነበር፡፡ በዚህም በመበረታታት በዋና ዋና የህትመት መገናኛ ዘዴዎች በርካታ መጣጥፎችንና ግጥሞችን ለማቅረብ ቻሉ፡፡ በመጨረሻም የ“ጥበብ ማዕድ” ና “የሕይወት ፍሬ” የተሰኙ ሁለት መፅሀፎች በጋራ አሳተሙ፡፡ በዚህም ዝናን እያተረፉ መጡ፡፡

በስነፅሁፍ ዝናን በማትረፋቸው ልበብርሃኖቹ ተጠቃሚ መሆን ቻሉ፡፡ የፈጠራ ችሎታቸውን በስነፅሁፎቻቸው በማስመስከራቸው ደስተኛ ሆኑ፡፡

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ



#### የጋዜጣና የመጽሔት አገልግሎት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ጋዜጣና መጽሔት የሚይዟቸው መረጃዎች ምን ምን ናቸው?

ለ. በትምህርትቤት የሚዘጋጁ ጋዜጦችና መጽሔቶች የሚያተኩሩባቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

### መነጠል

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ባለቅጥያ ቃላት ነጣጥላችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ዓለማቀፋዊነት ለ. ኢትዮጵያዊነት

2. ቀጥሎ የቀረቡትን ባለ ቅጥያ ቃላት ቅጥያውን ከዋናው ቃል ነጥላችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. በመኪና ለ. እንደተማሪ ሐ. ከዛፍላይ መ. ወደትምህርትቤት

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ርእሱ ስለምን ሊገልፅ እንደሚችል ገምታችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ?

ሐ. በሥዕሉና በርእሱ መካከል ያለውን ግንኙነት ግለፁ?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ፡፡
   ሀ. ተማሪዎቹ የሥነጽሑፍ እውቀታቸውን የበለጠ እንዲያሳድጉ ግፊት የፈጠረላቸው ምንድን ነው?
   ለ. ልበብርሀኖቹ በጋራ ያሳተሟቸው መፅሐፎች ብዛት ስንት ነው? ርዕሳቸውስ?

## ቃላት

**የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን ለጓደኞቻችሁ በጽሑፍ አብራሩላቸው፡፡**

ሀ. ስነጽሑፍ   ለ. ሚኒሚዲያ   ሐ. መጽሐፍ   መ. አጋጣሚ   ሠ. መጣጥፍ

## መጻፍ

የአካል ጉዳት ካለባቸው ጠንካራ ሰዎች የምታውቋቸውን አንዳቸውን በመምረጥ ስለጠንካራ ሥራዎቻቸው ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሁለት አንቀጾችን ጻፉ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የጋዜጣና የመጽሔት አገልግሎት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ ስጡ፡፡**

ሀ. መጽሔት በይዘቱ ከመጽሐፍ በምን ይለያል?
ለ. ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችንና መጻሕፍትን በማንበብ ምን ጥቅም ይገኛል?
ሐ. ተማሪዎች የመጻፍና የፈጠራ ችሎታቸውን የሚያሻሽሉት እንዴት ነው?

## ቃላት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምሳሌው መሠረት መልሶችን በጽሑፍ ስጡ፡፡**

ሀ. በረረ ብሎ <u>በራሪ</u> ቢል በከለ ብሎ ________ ይላል፡፡
ለ. ጻፈ ብሎ <u>መጻፍ</u> ቢል ገለጠ ብሎ ________ ይላል፡፡
ሐ. ጻፈ ብሎ <u>መጻፊያ</u> ቢል ገለጠ ብሎ ________ ይላል፡፡

## መነጠል

ከአሁን በፊት በተለማመዳችሁት መሠረት "-ኣዊ" እና "-ነት" የሚሉ ቅጥያዎች ያሉባቸውን አራት ቃላት ፈልጋችሁ በመጻፍ ቅጥያዎቹን ከዋናው ቃል በመነጠል አሳዩ፡፡

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. ባለታሪኮቹ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ባደረገው የሥነጽሑፍ ውድድር አሸንፈው እውቅና ማግኘታቸው ያስገኘላቸው ጥቅም ምንድን ነው?

ለ. ባለታሪኮቹ በሚኒሚዲያ ያቀርቧቸው የነበሩ ዝግጅቶች ምን ምን ነበሩ?

### ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. አተረፈ ለ. ውድድር ሐ. ፈጠራ

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጿቸው፡፡

ሀ. በማስመስከራቸው
ሐ. የጥበብ ማዕድ
ለ. ልበብርሃን
መ. እውቅና ያገኙበት


### መጻፍ

የጽሑፉ ባለታሪኮች ያከናወኗቸውን ድርጊቶች በራሳችሁ አባባል ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሁለት አንቀጾችን ጻፉ፡፡

# 24ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ሚኒሚዲያ



ሚኒሚዲያ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ተንቀሳቃሽ ሚኒሚዲያ በድምፅ ማጉያ አማካይነት መልእክት ለሰዎች ይተላለፍበታል፤ ማስታዎቂያዎችም ይነገሩበታል። በዚህም መልእክትን በአንድ ጊዜ ለብዙ ሰዎች ማዳረስ ይቻላል። የማይንቀሳቀስ ሚኒሚዲያ ግን ከአንድ ቦታ ብቻ መልእክት በቋሚነት ይተላለፍበታል።

ሚኒሚዲያ በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያቤቶች አካባቢ ሊቋቋም ይችላል። በዚህም መሠረት የመሥሪያቤቱን ሠራተኞች ያስተምራል፤ ያዝናናል። የመሥሪያቤቱን አሠራር ለማሻሻል እንዲቻል አስተያየት ይሰጥበታል። የመሥሪያቤቱን የዕለትተዕለት ተግባራት በተመለከተ ዜናዎች ይቀርቡበታል።

በትምህርትቤት የሚሠራበት የሚኒሚዲያ ዓይነት ደግሞ በትምህርትቤት የተለያዩ ሥራዎች ይከናወኑበታል። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥሩ ሥነምግባር ይዘው እንዲያድጉ ትምህርት ይሰጥበታል፤ የትምህርትቤት ደንቦች ለተማሪዎች ይገለጹበታል። በተጨማሪም ተማሪዎች በንድፈሐሳብ የሚማሩትን ትምህርት በተግባር ይፈትሹበታል፤ እውቀታቸውንም ያዳብሩበታል።

በአጠቃላይ ሚኒሚዲያ የተቋማትን ማኅበረሰብ አመለካከት ለመለወጥም ሆነ ለማስተሳሰር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ማኅበረሰቦች ስለልማት፣ ስለትምህርት፣ ስለአስተዳደር፣ ስለጤና፣ ስለባህልና ስለማኅበራዊ እሴቶች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

#### ስርጉትና ቢኒያም

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ::

ሀ. ከመጻሕፍት ምን ምን ቁምነገሮች ይገኛሉ?

ለ. ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲዎች በከፍተኛ ማዕረግ ለመመረቅ ምን ማድረግ አለባቸው?

ሐ. ከመጻሕፍት የሚገኙ ቁምነገሮች በሚዲያ ለትምህርትቤቱ ማኅበረሰብ ከመቅረባቸው በፊት ምን መደረግ አለባቸው?

### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በቃላችሁ አብራሩ::

ሀ. ጭብጥ ለ. ሙያ ሐ. ማሻሻል መ.ጠራ

### መነጠል

1. የሚከተሉትን የመነሻ ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ፃፉ::

   ሀ. እንደወረደ ለ. ለትምህርትቤት ሐ. ከሾፌር መ. ወደአገር

2. የሚከተሉትን ቃላት መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ::

   ሀ. በጋዜጣዎች ሐ. ስለአዳመጣችሁ ሠ. ስለጥያቄዎች

   ለ. እንደአካባቢያችን መ. ከጋዜጠኛነት ረ. ከመጽሔቶች

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ ስጡ::

   ሀ. ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ?

   ለ. በሥዕሉና በርእሱ መካከል ምን ግንኙነት አስተዋላችሁ?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ።
   ሀ. በትምህርትቤት ሚኒሚዲያ ምን ምን መልእክቶች ይተላለፋሉ?
   ለ. ሚኒሚዲያ በስንት ይከፈላል? ተግባራቸውን ግለጹ።

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን በቃል አብራሩ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. አደረሰ | መ. ግንዛቤ | ሰ. ማዝናናት |
| ለ. ገለጹ | ሠ. ነደፈ | ሸ. ጠቀመ |
| ሐ. ተግባር | ረ. አሻሻለ | |

## መጻፍ

የምንባቡን ዋና መልዕክት በራሳችሁ አባባል አሳጥራችሁ በሁለት አንቀጾች ጽፋችሁ አንብቡ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ስርጉትና ቢኒያም

የምንባቡን ዋና መልእክት በሁለት ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ።
   ሀ. አለፉ   ለ. ተመረቁ   ሐ. ጓጉ   መ. አነበነበ

## ማጣመርና መነጠል

1. የሚከተሉትን ቃላት መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ለይታችሁ ጻፉ።

   ምሳሌ፡- እንደወዛደሮች = እንደ - ወዛደር - ኦች = ወዛደር (ዋና ቃል)

| | |
|---|---|
| ሀ. ስለከፈለች | መ. ስለእድገታችን |
| ለ. እንደግንዛቤሽ | ሠ. በጤናችን |
| ሐ. ከአርሶአደሮች | ረ. ወደአካባቢህ |

2. በ "ሀ" ክፍል ያሉትን ቃላት በ "ለ" ክፍል ካሉት ቅጥያዎች ጋር በማዛመድ ባለቅጥያ ቃላት መስርቱ። (አንድ ቅጥያ ከአንድ በላይ ዋና ቃላት ጋር ሊዛመድ ይችላል።)

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ማኅበር | ሀ.-ኦች |
| 2. ቁምነገር | ለ. -ዎች |
| 3. ተሞክሮ | ሐ. -ኣዊ |
| 4. ሙዚቃ | መ. -ነት |
| 5. ጉዳይ | ሠ. -ኛ |
| 6. መረጃ | |
| 7. ዓለም | |
| 8. ልማት | |

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

### ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሠረት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ።

ምሳሌ፡- ሀ. ብዙኀን = ጥቂቶች
ለ. እድገት ________
ሐ. ጠቃሚ ________
መ. ይዘው ________
ሠ. ተንቀሳቃሽ ________
ረ. ቁምነገረኛ ________

2. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. ጎላ
ለ. ደንቦች
ሐ. ዜና
መ. ተንቀሳቃሽ

3. የሚከተሉትን ቃላት በምንባቡ ባላቸው ዐውድ መሠረት ዓረፍተነገሮችን ሠርታችሁ ፍቻቸውን ጻፉ።

ሀ. ደረሰ ለ. ተማረ ሐ. አለማ መ. ፈተሸ ሠ. ተለያየ

## መጻፍ

በቡድን ሆናችሁ ከተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች መካከል የእናንተ ምርጫ የትኛው እንደሆነ በምክንያት የሚገልፅ አንድ አንቀፅ ፃፉ።

25ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

# እማ ትርፌ

በአንድ አካባቢ እማ ትርፌና አባ ገረመው የሚባሉ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ በትዳር አብረው መኖር ከጀመሩ ሃያ ዓመት ሆኗቸዋል፡፡ አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ እየተባባሉ ይተጋገዛሉ፡፡ አንደኛው ሌላውን ያዳምጣል፤ በቤታቸው ጉዳይ በጋራ ይመካከራሉ፤ ይወስናሉ፤ ይሠራሉ፡፡ የተስማሙባቸውን ሐሳቦች ወደተግባር ይለውጣሉ፡፡

እማ ትርፌ ጠንካራና ሥራ ወዳድ ሴት ናቸው፡፡ ሸቀጦችን ከሱቅ፣ አትክልትና ፍራፍሬን ከመጋዝን እየተረከቡ በጉልት ገበያ ይቸረችራሉ፡፡ ባለቤታቸው አባ ገረመው ደግሞ ከብቶችን በማርባት ወተት ይሸጣሉ፤ ከብቶችን አድልበው ይሸጣሉ፡፡

እማ ትርፌ በጉልት ገበያ በቸርቻሪነት ለረጅም ጊዜ በመሥራታቸው በገበያተኛው ዘንድ ታዋቂ ናቸው፡፡ የሳምንት ቀለብ ለመግዛት ወደገበያ የሚሄዱ ደንበኞቻቸው ሳይጉበኟቸው አይመለሱም፡፡ በሐቀኝነታቸው ሰዎች ይወዷቸዋል፡፡ እማ ትርፌም "ደንበኛ ንጉሥ ነው" በሚል ደንበኞቻቸውን ያከብራሉ፡፡

✶✶✶ "ደንበኛ ንጉሥ ነው" ሲባል ምን ማለት ነው? ባለታሪኮቹ በትዳር ዓለም ለረጅም ዘመን የመቆየታቸው ምሥጢር ምን ይመስላችኋል?✶✶✶

እማ ትርፌ ከጅምላ ነጋዴዎች ቡና ሲገዙ ተረፍረፍ ጨመርመር አድርገው ይሰጧቸዋል፡፡ እሳቸውም ከደንበኞቻቸው ብዙ ትርፍ ሳይፈልጉ መረቅረቅ አድርገው ይሸጣሉ፡፡ ከገዢ ጋር ተስማምተው የገንዘብና የዕቃ ልውውጡን በደስታ ያከናውናሉ፡፡ ፍልቅልቅና ተጫዋች በመሆናቸው ገዢዎችም ደስ ብሏቸው ይገዟቸዋል፡፡ እማ ትርፌ በአብዛኛው ከሌሎች የጉልት ቸርቻሪዎች ባነሰ ዋጋ ይሸጣሉ፡፡

በአንድ ወቅት አንዲት ደንበኛቸው፣ “እማ ትርፌ፣ ቅቤ የለዎትም?” በማለት ትጠይቃለች። “ለዛሬስ የለኝም ልጄ!” አሏት። እማ ትርፌ ቅቤ ይዘው አያውቁም። ወተታቸውን እየናጡ ቅቤ መሸጥ አሰቡ። ወተቱን አጠራቅመው መናጥ ጀመሩ። ገበያው ደራላቸው። ቅቤ ፈላጊው በዛ። የገንዘብ አቅማቸውም እየጨመረ መጣ። ሥራቸውንም በሂደት ላቅ ወዳለ ዘርፍ ማሸጋገር ቻሉ። በዚህም ደስ እያላቸው ቀሪ ሕይወታቸውን መኖር ቻሉ።

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

ሻጭና ገዢ

### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በፅሁፍ ግለጹ፡፡

ሀ. ኪሳራ ለ. መለካት ሐ. ልውውጥ መ. ሸያጭ ሠ. ቸርቻሪ

### ማጣመር

የሚከተሉትን ጥምር ቃላት በብዙ ቁጥር ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ብረትምጣድ = ብረትምጣዶች

ሀ. ላባደር ለ. አርሶአደር ሐ. ሆደባሻ መ. ልቦለድ ሠ. ሥራአጥ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ሻጪ ምንድን ነው?

ለ. ገዢ ምንድን ነው? ከሻጪ ጋርስ ምን ግንኙነት አለው?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት አጫጭር መልሶችን በፅሁፍ ስጡ፡፡

ሀ. ጅምላ ነጋዴ ከቸርቻሪ ነጋዴ በምን ይለያል?

ለ. ብዙ ደንበኞች ከእማ ትርፌ የሚገዙት ለምንድን ነው?

ሐ. ነጋዴዎች ደንበኞቻቸውን ለመሳብ ምን ማድረግ ያለባቸው ይመስላችኋል?

### ቃላት

ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ፡፡

ሀ. ብዙ ትርፍ ሳይፈልጉ <u>መረቅረቅ</u> አድርገው ይሸጣሉ፡፡

ለ. በገበያተኛው ዘንድ <u>ታዋቂ</u> ነጋዴ ናቸው፡፡

ሐ. ወተቱን አጠራቅሞ <u>መናጥ</u> ቅቤ ለማግኘት ይረዳል፡፡

መ. የገንዘብ አቅማቸው <u>አደገ</u>፡፡

## መጻፍ

“እማ ትርፌ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ዋና መልዕክት በራሳችሁ አባባል አሳጥራችሁ በሁለት አንቀጾች ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ሻጭና ገዢ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. “የዋጋ ቅናሽ ያደርጋል ታናሽ” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. “ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ” የሚለው የአበው ምሳሌ መልእክት ምንድን ነው?

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት በምንባቡ ባላቸው ዐውድ መሠረት ፍቻቸውን ስጡ፡፡

ሀ. ጅምላ ለ. አሻሚ ሐ. ሻጭ መ. የሚታይ ሠ. መከራከር

2. ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ጥቂት በርካታ

ሀ. ደስታ ለ. አጠራቀመ ሐ. ጥራት መ. ገዛ

## መነጠል

1. የተለያዩ አምስት ጥምር ቃላትን በመጻፍ፣ ቃላቱን ነጣጥላችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ዝናብአጠር የሚለው ጥምር ቃል “ዝናብ + አጠረ” ይሆናሉ፡፡

2. የሚከተሉት ባለቅጥያ ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ ቅጥያዎቻቸውን ከዋናው ቃል ነጣጥላችሁ በመጻፍ አንብቡ፡፡

ሀ. በቤታችሁ ለ. ከመጋዘን ሐ. በውስጥ መ. ከቤቱ ላይ ሠ. ስለትምህርት

## መጻፍ

የዓረፍተነገሮችን መልዕክት በማያዛባ መልኩ ቃላቱን በቅደምተከተል ጻፏቸው::

ሀ. ሥራ ወዳድ እማ ትርፌ ሰው ናቸው ጠንካራ::

ለ. የለዎትም እማ ትርፌ ቅቤ?

ሐ. ድልብ ሸጡ በሬዎችን አባ ገረመው::

# 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ በቃላችሁ መልሱ::

ሀ. አንድ ነጋዴ ኪሳራ የሚገጥመው ምን ሲሆን ነው?

ለ. ገዢን (ደንበኛን) በሣቅና በፈገግታ ማስተናገድ ለምን የሚጠቅም ይመስላችኋል?

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በፅሑፍ ስጡ::

ሀ. እማ ትርፌ በተሰማሩበት የንግድ ዘርፍ ቢከሥሩ ምን ያጋጥማቸው ነበር?

ለ. "ለዛሬ ቅቤ የለኝም ልጄ" ሲሉ ምን ማድረግ አስበው ነው?

ሐ. በችርቻሮና በጅምላ ነጋዴ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት አለ?

## ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረግ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው ዐውድ መሠረት ፍቻቸውን ስጡ::

ሀ. ጨመረ ለ. ላቅ ያለ ሐ. ሐቀኛ መ. ርካሽ

## መጻፍ

በቡድን በቡድን ሆናችሁ "የጽሕፈት መሣሪያዎች አቅራቢ ነጋዴ ብሆን ኖሮ" በሚለው መንደርደሪያ ሀሳብ መነሻነት አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ አንብቡ::

## 26ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ገንዘብ



ገንዘብ ለመገበያያ እንዲሆን በመንግስት የሚሰየም ህጋዊ ቁስ ነው። ገንዘብን በመጠቀም እቃንና አገልግሎትን መግዛትና እዳንም መክፍል ይቻላል። በጥንት ጊዜ አሞሌ ጨው፣ የዝሆን ጥርስ፣ አልማዝና ወርቅ ለመገበያያነት ያገለግሉ ነበር። ይሁን እንጂ ቋሚ ተመን ስላልነበራቸው የገንዘብን ያህል ግብይትን የሚያፋጥኑ አልነበሩም።

ገንዘብ የተለያየ ቋሚ ዋጋ ባላቸው ህጋዊ ኖቶች ይወከላል። ለምሳሌ አሁን በአገልግሎት ላይ ያለው የኢትዮጵያ ገንዘብ ስድስት ዓይነት ሳንቲሞችና አምስት ዓይነት የብር ኖቶች አሉት። በሳንቲም አንፃር አንድ ሳንቲም፣ አምስት ሳንቲም፣ አስር ሳንቲም፣ ሃያ አምስት ሳንቲም፣ ሃምሳ ሳንቲምና መቶ ሳንቲም(አንድ ብር) ይጠቀሳሉ። አንድ ብር፣ አምስት ብር፣ አስር ብር፣ ሃምሳ ብርና መቶ ብር ደግሞ የብር ኖቶች ናቸው ።

✶✶✶ "ምንባቡ ቀጥሎ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?"✶✶✶

የገንዘብ ኖቶች ዋጋ በአገሮች የሀብት ክምችትና የእድገት ልዩነት ምክንያት በየወቅቱ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ የአሜሪካ ዶላርና የኢትዮጵያ ብር በተጠቀሱት ምክንያቶች በየጊዜው የዋጋ ልዩነት ይኖራቸዋል። በአንድ ወቅት አንድ የአሜሪካ ዶላርና አንድ የኢትዮጵያ ብር እኩል ምንዛሬ ላይኖራቸው ይችላል። ከአንዱ ገንዘብ ወደሌላው የሚደረገው ልውውጥ በወቅቱ ባለው በሁለቱ አገሮች የምንዛሬ ተመን መሰረት የሚከናወን ይሆናል።

የአንድ አገር የገንዘብ ኖት ጊዜው ሲያልፍበት እንደተራ ወረቀት ሊቆጠር ይችላል።

ለምሳሌ በደርግ ዘመነመንግስት ያገልግል የነበረው የኢትዮጵያ ብር በአሁኑ ጊዜ ከተራ ወረቀት ተለይቶ አይታይም።

በአጠቃላይ ገንዘብ ከአንድ አገር ሀብት፣ እድገት፣ የንግድ ልውውጥና የህዝብ ብዛት መጠን አንፃር ተመጥኖ ታትሞ ለመገበያያነት ያገለግላል። ህጋዊ መገበያያም በመሆኑ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አለው።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ሰላማዊት "ጠንቃቄ"**

### ቃላት

1. ለሚከተሉት ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. አያሌ | መ. አጣጣመ | ሰ. ራእይ |
| ለ. ዘወትር | ሠ. አጤኑ | ሸ. ሕልም |
| ሐ. ትሸፍናለች | ረ. ቅጽል | |

2. ከላይ ከ "ሀ - ሸ" በተዘረዘሩት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥርታችሁ አንብቡ፡፡

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. የሚከተለውን ጥያቄ በቃላችሁ መልሱ፡፡
   "ገንዘብ" የሚለው ርዕስ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሶቻቸውን በፅሑፍ ስጡ፡፡
   - ሀ. በኢትዮጵያ ስንት ዓይነት ሳንቲሞች አሉ?
   - ለ. በጥንታዊ የመገበያያ ቁሶች የነበረው ችግር ምን ነበር?
   - ሐ. የመገበያያ ገንዘብ ባይኖር ኖሮ ሰዎች ምን ይገጥማቸው ነበር?

### ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሠርታችሁ ዐውዳዊ ፍቻቸውን ግለጹ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. መገበያያ | ሐ. ተራ | ሠ. ገንዘብ |
| ለ. ልውውጥ | መ. ምንዛሬ | ረ. ማተም |

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ምንነት በቃላችሁ ግለጹ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ወርቅ | ሐ. አሞሌ ጨው | ሠ. ሳንቲሞች |
| ለ. የብር ኖት | መ. የዝሆን ጥርስ | |

## መጻፍ

“ገንዘብ” የሚለውን ምንባብ ሦስተኛ አንቀጽ በራሳችሁ አባባል አሳጥራችሁ ጻፉ::

## 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ሰላማዊት “ጠንቃቄ”

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን ስጡ::

ሀ. ባንክ ለምን ያገለግላል?

ለ. “ጠንቃቄ” የሚለው ቃል ምንን ይገልጻል?

ሐ. የባለታሪኳ ራእይ ምን ነበር?

መ. የኢትዮጵያ የብር ኖቶችና ሳንቲሞች ምን ምን ናቸው?

## ቃላት

በ “ሀ” ረድፍ ያሉትን ቃላት ፍቾቻቸውን ከ “ለ” ረድፍ መርጣችሁ አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እርቃን | ሀ. ተስፋ |
| 2. ጥቅም | ለ. ማከማቸት |
| 3. ማጠራቀም | ሐ. ፋይዳ |
| 4. ምኞት | መ. ራቁት |

## ማጣመርና መነጠል

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥምር ሀረጋት ወደ ብዙ ቁጥር ለውጣችሁ ጻፉ::

ሀ. ከገንዘብያዥ ሐ. በፍርድቤት ሠ. ከማዘጋጃቤት

ለ. በጤናጣቢያ መ. ወደጤናኬላ ረ. ወደመዝገብቤት

2. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ዋናውን ቃል ከቅጥያው በመነጠል ጽፋችሁ አንብቡ::

ሀ. ለዜጎች ሐ. ስለገንዘብ ሠ. በወጥነት

ለ. በቁሶች መ. በሳንቲሞች

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ::

ሀ. ገንዘብ ምንድን ነው?

ለ. የአሜሪካ የገንዘብ ኖት ምን ይባላል?

ሐ. የተለያዩ የብር ኖቶችና ሳንቲሞች መኖራቸው በግብይት ወቅት ያለው ፋይዳ ምንድን ነው?

### ቃላት

1. በምንባቡ መሠረት ተስማሚ ቃላትን በመምረጥ ክፍት ቦታዎችን አሟሉ::

| ተራቁስ፣ ምንዛሬ፣ ወጥ፣ ህጋዊ |
|---|

ሀ. አልማዝና ወርቅ ________ የሆነ ዋጋ የላቸውም::

ለ. ያገልግሎት ጊዜው ያለፈበት የገንዘብ ኖት ________ ይሆናል::

ሐ. ከአንዱ ገንዘብ ወደሌላው የሚደረግ የገንዘብ ለውጥ ________ ይባላል::

መ. በአንድ ሀገር ህዝብ ተቀባይነት ያለው ገንዘብ _______ መገበያያ ነው::

2. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን በምንባቡ መሠረት ጻፉ::

ሀ. ምጣኔ　　ሐ. ጥቅም　　ሠ. የሀብት ክምችት

ለ. የዋጋ ልዩነት　　መ. ዘመነ መንግሥት

### መጻፍ

ያነበባችሁትን ጽሑፍ በራሳችሁ አባባል አሳጥራችሁ በሁለት አንቀፆች ጽፋችሁ አንብቡ::

# 27ኛ ሳምንት

## ግለንባብ

### ወይ ነዶ!

አቶ ሙሉቀን ገዙ በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ አስር ውስጥ ይኖራሉ፡፡ በአካባቢው ታዋቂ ነጋዴ ናቸው፡፡ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ አጃና ምስር ይሸጣሉ፡፡ እህሎቻቸውን በመሸጥ ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችን ይገዛሉ፡፡ ከቤት ውስጥ አገልግሎት መግዣ የተረፈውን ብርና ሳንቲም በሚፈለግ ጊዜ እጠቀማለሁ በሚል ሀሳብ ባዘጋጁት አነስተኛ ሳጥን ውስጥ ያጠራቅማሉ፡፡

አቶ ሙሉቀን በዚህ ሁኔታ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ያጠራቀሙት ገንዘብ ሃያ አምስት ሺህ ብር ደረሰ፡፡ ይህንን ገንዘብ የያዘ ሣጥን ቤት ውስጥ ትቶ መሄድ እያሳሰባቸው መጣ፡፡ ይሁን እንጂ በአካባቢያቸው በሚገኝ ንግድ ባንክ ገንዘብ መቆጠብ እንዳለባቸው ግንዛቤው የላቸውም፡፡ ምክንያቱም በንግድ ባንክ የሚደረገውን ቅስቀሳ (ማስታወቂያ) የእኔ ብለው ባለመከታተላቸው ነው፡፡ በመሆኑም ገንዘቡን ልብ ሊባል በማይችል ስፍራ ወይም በአልባሌ ቦታ ለማስቀመጥ አሰቡ፡፡ ይህንን ጉዳይም ለባለቤታቸው ለወይዘሮ የአለምዘውድ ቢያማክሯቸውም ባለቤታቸው ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ አቶ ሙሉቀንም ከሁኔታው አሳሳቢነት በመነሳት ገንዘብን ማንም የቤተሰቡ አባል ሳያያቸው በፍራሽ ውስጥ ደበቁት፡፡

★★★ "ገንዘብን በአልባሌ ቦታዎች ላይ ማስቀመጥ ምን ጉዳት አለው?
የታሪኩ መጨረሻ ምን የሚሆን ይመስላችኋል??"★★★

አንድ ቀን የወይዘሮ አለምዘውድ ወንድም የሆኑት አቶ አንተነህ ልጃቸውን ስለሚድሩ የቤተሰቡ አባል በሙሉ ወደሰርግ ቤቱ ተጓዙ፡፡ በዚህ ጊዜም በዕለቱ እንደማይመለሱ ስለሚያውቁ ቤታቸውን በጥንቃቄ ቆልፈው በመሄዳቸው የቤታቸው ጉዳይ አላሳሰባቸውም ነበር፡፡ ምክንያቱም ከአሁን ቀደም በአካባቢያቸው አስጊ የሆነ ነገር ተፈጥሮ ስለማየውቅ ነው፡፡ ነገር ግን እንዳጋጣሚ ሆኖ ለሰርግ ባደሩበት ወቅት ሌባ ቤታቸውን ሰብሮ በመግባት ብርድ ልብሳቸውን ፣ፍራሻቸውን እንዲሁም ለመያዝ አመች የሆኑለትን ቁሳቁሶች በሙሉ ጠራርጎ ይሄዳል፡፡

የቤተሰቡ አባል የሰርጉ ማግስት ወደቤታቸው ሲመለሱ ያልጠበቁት ነገር ተከስቶ በማግኘታቸው ደነገጡ፡፡ አቶ ሙሉቀንም በተፈጠረው ሁኔታና በፈጸሙት ስህተት ተፀፀቱ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሚያገኙትን ገንዘብ በአቅራቢያቸው በሚገኘው ንግድ ባንክ ማስቀመጥ እንዳለባቸው በመረዳታቸው ገንዘባቸውን መቆጠብ ጀመሩ፡፡ ያለስጋት እየመነዘሩ መጠቀም እንዳለባቸውም በማረጋገጣቸው የባንኩ ደንበኛ ሆኑ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘባቸውን ለሚቆጥቡ ደንበኞቹ የዕጣ ኩፖን ያዘጋጃል፡፡ አቶ ሙሉቀንም የዕጣ ኩፓኑ ዕድል ተጠቃሚ በመሆናቸው መኪና ደረሳቸው፡፡ በተፈጠረው ሁኔታ በመደሰታቸው የባንክ አገልግሎቱን አስመልክተው ልምዳቸውን ለሌሎች ማካፈል ጀመሩ፡፡

## 1ኛ ቀን




### ማዳመጥ

#### ባንኮች

የሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. “ፋና ወጊ” ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በባንክ ቤቶች አጠራር “ቅርንጫፍ” ስንል ምን ማለታችን ነው?

ሐ. በኢትዮጵያ ፋና ወጊው ባንክ ማን ተብሎ ይጠራል?

መ. በባንክ ደብተርና በቼክ መካከል ምን ልዩነት አለ?

### ማጣመርና መነጠል

1. የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- እንደአገሩ   እንደ - አገር - ኡ

ሀ. እንደወትሮው   ለ. ፈቃደኞች   ሐ. ከባንኮች   መ. በገለባው

2. በ “ሀ” ረድፍ ላሉት ቃላት ተጣማሪያቸውን ከ “ለ” ረድፍ መርጣችሁ አጣምሩ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ግብረ | ሀ. ጥር |
| 2. ስመ | ለ. መልስ |
| 3. ዓይነ | ሐ. በል |
| 4. ሥጋ | መ. ገብ |

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ፡፡

ሀ. ከሥዕሎቹ ምን ተረዳችሁ?

ለ. ባንክ ከዕቁብ በምን የሚለይ ይመስላችኋል?

2. በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. ገንዘብን ከባንክ ውጭ ማስቀመጥ ምን ጉዳት ያመጣል?

ለ. ባለታሪኩ ገንዘባቸውን በፍራሽ ውስጥ ደብቀው ማስቀመጥ የፈለጉት ለምንድን ነው?

3. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሶችን ጻፉ።

ሀ. አቶ ሙሉቀን ከእህል ሽያጭ የሚያገኙትን ገንዘብ ለምን አገልግሎት ያውሉታል?

ለ. የአቶ ሙሉቀን ገንዘብ በሌባ የተወሠደው ለምንድን ነው?

ሐ. አስተማማኝ የገንዘብ ማስቀመጫ ምንድን ነው? ለምን?

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት በምንባቡ መሰረት ፍቻቸውን በፅሑፍ ስጡ።

ሀ. ተፀፀተ
ሐ. ስጋት
ሠ. ማጠራቀም
ለ. ታዋቂ
መ. ደበቀ
ረ. ገንዘብ

2. የሚከተሉትን አባባሎች ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. ደንበኛ ለ. ሰርግ ሐ. የዕጣ ኩፖን መ. ልምድ

## መጻፍ

"አቶ ሙሉቀንን ብሆን ኖሮ" በሚል መነሻ አጭር ፅሑፍ ፃፉ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ባንኮች

## ቃላት

ለሚከተሉት የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ስጡ።

ሀ. የምንዛሪዎችን ልውውጥ ማቀላጠፍ ለእድገት ይጠቅማል።

ለ. እውቅና የተሰጣቸው የገንዘብ ኖቶች ክብርና ትኩረት ይሰጣቸዋል።

ሐ. ባንኮች የገንዘብ ዝውውርን ከዘረፋና ከስርቆት ይጠብቃሉ።

## ማጣመር

1. የሚከተሉትን ቅጥያዎችና ዋና ቃላት አጣምራችሁ ጻፉ።

ሀ. እንደ ከሣ
ሐ. ለ ቤቱ
ሠ. ወደ አገሩ
ለ. ከ ልብ
መ. ከ አናቱ
ረ. ስለ ልጅ

2. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በማጣመር ወደአንድ ዓረፍተነገር ለውጣችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- ከበደ ከትምህርትቤት መጣ፡፡ ከበደ ምሳውን በላ፡፡
ከበደ ከትምህርትቤት መጥቶ ምሳውን በላ፡፡

ሀ. መጽሐፍ ገዛ፡፡ መጽሐፍ አነበበ፡፡

ለ. ፋጡማ ወደገበያ ሄደች፡፡ ፋጡማ አዲስ ቀሚስ ገዛች፡፡

ሐ. ራሱን አመመው፡፡ ወደሆስፒታል ሄደ፡፡

መ. ችግኝ ተከለች፡፡ ውሃ አጠጣች፡፡

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሶችን በቃላችሁ ስጡ፡፡

ሀ. ባለታሪኩ ገንዘብ የያዘውን ሳጥን ትቶ መሔድ ያሳሰባቸው ለምንድን ነው?

ለ. ገንዘብ በባንክ ማስቀመጥ ለምን ይረዳል?

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶች በጽሑፍ ስጡ፡፡

ሀ. አቶ ሙሉቀን ገንዘባቸውን በፍራሽ ውስጥ የደበቁት ለምንድን ነው?

ለ. የቤተሰቡ አባላት ቤታቸውን ትተው ዘመድ ቤት ያደሩት በምን ምክንያት ነው?

## ቃላት

በ "ሀ" ክፍል የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት ከ "ለ" ክፍል በማመሳሰል አዛምዱ

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| 1. | መቀስቀስ | ሀ. በነጋታው |
| 2. | ማግስት | ለ. ተገልጋይ |
| 3. | ተጠቃሚ | ሐ. ማስተዋወቅ |
| 4. | ቢያማክሩ | መ. አካባቢ |
| 5. | አቅራቢያ | ሠ. ቢያወያዩ |

## መጻፍ

"የምወደው የንግድ ዓይነት" በሚል ርእስ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሁለት አንቀጾችን ጽፋችሁ አንብቡ፡፡

## ግለንባብ

# የንግድ ሕጎች

የንግድ ሥራ ለመሥራት የሚያስችሉ በርካታ ሕጎች አሉ። ከነዚህ ሕጎች መካከል አንዱ የንግድ ፍቃድ ማውጣት ነው። የንግድ ፍቃድ በአንድ የንግድ ዘርፍ ለመሥራት ያስችላል፣ ሕጋዊ ከለላም ይሰጣል። አንድ ሰው በሚፈልገው የሥራ ዘርፍ ያለሥጋት መሥራት የሚችለው ሕጋዊ የንግድ ፍቃድ ሲኖረው ነው። መንግሥትም ግለሰቡ በሚፈልገው የንግድ ሥራ እንዲሰማራ የሚፈቅድለት የንግድ ፍቃድ ሲያወጣ ነው።

የንግድ ፍቃድ ያለምንም ሥጋት ለመሥራት ያስችላል። ማንኛውንም የንግድ ሥራ ሕጋዊ ፍቃድ ይዞ መሥራት ለንግድ አሠራር ሥርዓት የራሱ ድርሻ አለው። ፍቃድ ይዞ መሥራት ለሕግ ተገዢ መሆን ነው።

ባለንግድ ፍቃዱ ሥራውን ሳያቋርጥ ለመሥራት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት። ግብር መክፈል ለመንግሥትም ሆነ ለሌላው ማኅበረሰብ በጣም ይጠቅማል። የመንግሥት ተቋማት የጀርባ አጥንት የሆነውን በጀት የሚያገኙት ከግብር ነው።

ግብር ከፋዩ የሚከፍለው ገንዘብ መሠረተልማትን ለማሟላት ያስችላል። መንገድ፣ መብራት፣ ውሃና የመሳሰሉትን ለማሟላት ይውላል። ይህም ሁኔታ ሀገርን ላቅ ወዳለ ደረጃ ያሸጋግራል። በማኅበራዊ ጉዳይም የትምህርት ተቋማትን በማስፋፋት ዜጎችን ለማስተማር ያስችላል።

> ✶✶✶ “ህጋዊ ነጋዴ የሚባለው እንዴት ያለ ነው? ግብር መከፍል ምን ማለት ነው?”✶✶✶

ግብር ከፋዩ ተገቢ ግብር ለመክፈል ገቢና ወጪውን ለገቢዎች ማሳወቅ ይኖርበታል። ይህም የንግድ ሕጉ አንዱ አካል ነው። ግብር ከፋዩ መክፈል ከሚገባው በላይ ወይም በታች እንዳይከፍል የሚያደርገው ገቢ ወጪውን በወቅቱ ማሳወቅ ከቻለ ነው። በዚህም መሠረት የንግድ ፍቃዱን ማሳደስ ይችላል።

በአጠቃላይ የንግድ ሥራዎችን ለመሥራት የንግድ ሕጎችን ማክበርና መከተል ያስፈልጋል። ግብርን በወቅቱ መክፈል፣ ገቢና ወጪን ማሳወቅ፣ የተፈቀዱ ቁሳቁሶችን ብቻ መግዛትና መሸጥ እንዲሁም የንግድ ፍቃድን በየወቅቱ ማደስ የዜግነት ግዴታ ነው።

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

## ሕጋዊ ነጋዴዎች




### ቃላት

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ፡፡

ሀ. ግራ ተጋቡ  ለ. ልባም  ሐ. የዜግነት ግዴታ  መ. በልባቸው ቋጠሩ

### ማጣመርና መነጠል

1. የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጣጥላችሁ አውጡ፡፡

   ሀ. በህግ  ለ. ስለሥራው  ሐ. በመንገድ ላይ  መ. አንደመጣ

2. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በምሳሌው መሠረት አያይዛችሁ ጻፉ፡፡

ምሣሌ፡- ፋጡማ መጣች፡፡ አበበ ወደገበያ ሄደ፡፡

ፋጡማ እንደመጣች አበበ ወደገበያ ሄደ፡፡

ሀ. አዳሙ ቤት ሠራ፡፡ ቤተሰቦቹ መጡ፡፡

ለ. ማርታ ምሳዋን በላች፡፡ ወንድሟ ስልክ ደወለ፡፡

ሐ. አየለ ወደገበያ ሄደ፡፡ አባቱ ወደቤታቸው መጡ፡፡

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሶቻቸውን በቃላችሁ ስጡ፡፡

   ሀ. ሕጋዊ ነጋዴ የሚባለው እንዴት ያለ ነው?

   ለ. ግብር መክፈል ለምን ያስፈልጋል?

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን በቃላችሁ ስጡ።
   ሀ. ገቢና ወጪን ማሳወቅ ምን ጥቅም ያለው ይመስላችኋል?
   ለ. የንግድ ሥራን ለመሥራት ምን ያስፈልጋል?
   ሐ. የንግድ ሥራ የሚያስከስሰው መቼ ነው?
   መ. የንግድ ሕጎች ከሚባሉት ሁለቱን ጥቀሱ።

## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ፈቃድ | ሐ. ገቢ | ሠ. ማዕድን |
| ለ. ግብር | መ. ወጪ | ረ. ማስመጣት |

## መጻፍ

"ንግድና ታማኝነት" በሚል ርዕስ አንድ አጭር ጽሑፍ ጻፉ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ሕጋዊ ነጋዴዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሶቻቸውን በጽሑፍ ስጡ።
   ሀ. ከሕዝብ የሚሰበሰበው ግብር ለምን አገልግሎት የሚውል ይመስላችኋል?
   ለ. ያዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና ሐሳብ በአጭሩ በቃላችሁ ግለፁ።

## ቃላት

ካዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡት ቃላት ዐውዳዊ ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. ማፍራት   ለ. እድሳት   ሐ. ትርፋማ   መ. ፍትሐዊ

## መነጠልና ማጣመር

1. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት በምሳሌው መሠረት ነጣጥላችሁ አሳዩ።
   ምሳሌ፡- በፍርድላይ   በ   ፍርድ   ላይ
   ሀ. በአልጋላይ   ለ. በቤትውስጥ   ሐ. ስለመጡ   መ. እንደቀረበ

2. "በ-፣ ለ-፣ ከ-፣ ወደ-፣ ስለ-፣ እንደ-"ን ተጠቅማችሁ ዐረፍተ ነገሮችን አሟልታችሁ እንደገና ፃፉ ።

ሀ. አበበ __________ ገበያ ሄደ።

ለ. አልማዝ ________ እህቷ ጎበዝ ተማሪ ናት።

ሐ. አሊ ________ ወንድሙ ደብዳቤ ጻፈ።

መ. ________ አገሩ የማያስብ ቂል ነው።

ረ. ክፍላችን ________ መርጃ መሣሪያዎች የተሟላ ነው።

ሠ. ________ ሰሜን አቅጣጫ ንፋስ ነፈሰ።

## 4ኛ ቀን

## ማንበብ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ግብር ለአንድ ሀገር ያለው ፋይዳ ምንድን ነው?

ለ. ትክክለኛ ግብር ለመክፈል ከነጋዴዎች ምን ይጠበቃል?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የንግድ ፍቃድ ማውጣት (መያዝ) ለምን ይጠቅማል?

ለ. ሕጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ምን ምን የማድረግ መብቶች አሏቸው?

ሐ. የንግድ ፍቃድ ምንድን ነው?

## ቃላት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ ፍቻቸውን ስጡ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ማሳወቅ | ሐ. ላቀ | ሠ. አደሰ |
| ለ. መስክ | መ. ተከተለ | ረ. አገዘ |

## መጻፍ

"መንንገዢ" በሚል ርእስ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

# ግለንባብ

## ግለታሪኬ



አሁን የ26 ዓመት ወጣት ነኝ፡፡ በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ እገኛለሁ፡፡ ከመደበኛ ስራዬ ውጪ በማህበራዊ ተግባራት እሳተፋለሁ፡፡ በአካባቢ ፅዳት፣ በሰፈር መንገድ ግንባታ፣ በደን ልማትና በእንስሳት እንክብካቤ ተግባራት በፈቃደኝነት እሳተፋለሁ፡፡

ከሚላ ተስፋ እባለላሁ፡፡ የተወለድኩት በ1981 ዓ.ም. ነው፡፡ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነኝ፡፡ እንደማንኛውም የአካባቢያችን ልጆች አፈር እየፈጨሁ፣ እቃቃ እየተጫወትኩ ነው ያደኩት፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ በእድሜ የሚበልጡኝን ሁሉ አከብራለሁ፡፡

✶✶✶ “ምንባቡ ከዚህ ቀጥሎ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?”✶✶✶

የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን በአካባቢዬ በሚገኙ ትምህርትቤቶች አጠናቅቄያለሁ፡፡ በትምህርትቤት ቆይታየም ጥሩ ጥሩ ጓደኞች አፍርቻለሁ፡፡ ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋርም መልካም ግንኙነት ነበረኝ፡፡ ትምህርቴን ለማጥናትና የቤት ስራዬን በጊዜ ለመስራት እተጋ ነበር፡፡ በዚህም ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እስከአስራሁለተኛ ክፍል ድረስ ከፍተኛ ውጤት እያስመዘገብኩ ነው ያለፍኩት፡፡

የልጅነት ምኞቴ መሀንዲስ መሆን ነበር፡፡ ይህንንም በጥረቴ አሳክቸዋለሁ፡፡ በአሁኑ ወቅት በምኖርበት ክልል በአንድ የህንፃ ዲዛይንና ቁጥጥር መስሪያቤት በመስራት ላይ እገኛለሁ፡፡ የተለያዩ ዘመናዊ ህንፃዎችን ንድፍ አዘጋጃለሁ፤ ህንፃዎቹ በንድፉ መሰረት መገንባታቸውንም በመቆጣጠር በአግባቡ አማክራለሁ፡፡ በዚህም ስራዬ ውጤታማ ነኝ፡፡ ወደፊትም ሙያዬን በልምድና በትምህርት እያሻሻልኩ አገሬ በምታደርገው የእድገት ጉዞ የበኩሌን አስተዋፅኦ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡

## 1ኛ ቀን

### ማዳመጥ

**ግለታሪክ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ።**

ሀ. ግለታሪክ በቀላል ቋንቋ የሚጻፈው ለምንድን ነው?

ለ. ስለአንድ ሰው የተፃፈን ግለታሪክ ማንበብ ምን ጠቀሜታ አለው?

### ቃላት

**ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበቃላት ፍቻቸውን ጻፉ።**

ሀ. ስልት ለ. እርከን ሐ. ጉልህ መ. አስተዋጽዖ

### ማጣመርና መነጠል

1. በሚከተሉት ቃላት "ወደ-፣ ለ-፣ ከ-፣ ስለ-፣ በ-፣ እንደ-" በመጨመር ቃላት መሥርቱ።

ሀ. _____ ግል ሐ. _____ልምድ ሠ. _____እምነቷ

ለ. _____ ተመሳሳይ መ. _____ ቤት

2. የሚከተሉትን ቃላት ቅጥያዎች ከዋናው ቃል ነጥላችሁ ጻፉ።

ሀ. አዛውንቶች ለ. ሁለተኛ ሐ. ጓደኞች መ. ከአጠናሁ ሠ. መደበኛ

## 2ኛ ቀን

### ማንበብ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ መልሱ።**

ሀ. ባለታሪኳ በልጅነቷ ምን የመሆን ምኞት ነበራት?

ለ. ባለታሪኳ በየክፍል ደረጃው ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ያስቻላት ምንድን ነው?

### ቃላት

1. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ዐውዳዊ ፍቺ በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. ትጋት ለ. አሳካ ሐ. ፈቃደኝነት

2. ለሚከተሉት ቃላት የመዝገበቃላት ፍቻቸውን በጽሑፍ ስጡ።

ሀ. ታሪክ ለ. ማህበራዊ ሐ. እድገት መ. ንድፍ ሠ. ማፍራት ረ. ገነባ

## መጻፍ

የምንባቡን ዋና ሀሳብ በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ።

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### ግለታሪክ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. ግለታሪክ ምንድን ነው?

ለ. የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ስንት ዓይነት ናቸው? ምን ምን?

ሐ. ግለታሪክ መጻፍ ለምን ይጠቅማል?

## ቃላት

በ "ሀ" ረድፍ ያሉትን ቃላትና ሐረጋት ከ "ለ" ረድፍ ካሉት ጋር በማመሳሰል አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ማመን | ሀ. ተሞክሮ |
| 2. አስደናቂ | ለ. ከልብ መቀበል |
| 3. የሕይወት ልምድ | ሐ. የኑሮ መንገድ |
| 4. መጋራት | መ. አስገራሚ |
| 5. የሕይወት አቅጣጫ | ሠ. ተመሳሳይ አቋም |

## ማጣመር

1. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች አያያዦችን ተጠቅማችሁ በማጣመር አንድ አንድ ዓረፍተነገር አድርጓቸው።

ሀ. የቤት ሥራዬን በሰዓቱ እሠራለሁ።

ከአንደኛ እስከሦስተኛ ክፍል ተሸላሚ ነበርኩ።

ለ. ጠንካራ የሥራ እምነት አለኝ።

የተሳካ ኑሮ እኖራለሁ፡፡

2. በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት አስተካክላችሁ በክፍት ቦታዎች በማስገባት ዓረፍተነገሮችን አሟሉ፡፡

ሀ. ሠናይት ጎበዝ ተማሪ ________፡፡ (ነው)

ለ. ዛፎች በሌቦች ________፡፡ (ቆረጠ)

ሐ. ዓለሚቱ ወደ ትምህርትቤት ________፡፡ (ሄደ)

መ. ________ እንዳባቱ ጠንካራ ነው፡፡ (ልጅ፟ቷ)

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሶችን በቃላችሁ ስጡ፡፡

ሀ. የመሃንዲሶች ሥራ ምንድን ነው?

ለ. መልካም ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነው?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. የባለታሪኳ የወደፊት ፍላጎቷ ምንድን ነው?

ለ. ከሚላ አሁን የምትሠራበት መሥሪያቤት ምን ይባላል?

### ቃላት

1. ለሚከተሉት ሐረጋት ፍቻቸውን በፅሁፍ ስጡ፡፡

ሀ. የአካባቢ ፅዳት  ለ. ጓደኛ ማፍራት  ሐ. ማኅበራዊ ተግባር

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጧቸው፡፡

ምሳሌ፡- ግላዊ  ቡድናዊ

ሀ. ጀመረ ________  መ. ከፍተኛ ________

ለ. ልጅነት ________  ሠ. ማልማት ________

ሐ. አደገ ________

3. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ፡፡

ሀ. ወቅት  ለ. ተቆጣጠረ  ሐ. ሙያ

### መጻፍ

“ጓደኞቼ” በሚል ርእስ ሁለት አንቀጾችን ጻፉ፡፡

## ግለንባብ

### የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ

የግለሰብ የሕይወት ታሪክ የአንድን ግለሰብ ታሪክ ይመለከታል። ይህ ጽሑፍ እውነት የሆኑ ነገሮች የሚቀርቡበት እንጂ ፈጠራ አይደለም። ጽሑፉን የሚያዘጋጀው ሰው ስለባለታሪኩ አስተማማኝ መረጃዎችን መሰብሰብ አለበት። የሚፃፈው ታሪክ ከስሜት ውጭ የሆነ፣ በእውነት ላይ የተመሠረተ፣ በአንባብያን ዘንድ ተቀባይነትና ተነባቢነት እንዲኖረው ይጠበቃል።

✶✶✶ "የሕይወት ታሪክ የሚጻፍላቸው ሰዎች ምን ዓይነት ናቸው?"✶✶✶

የሕይወት ታሪክ የሚጻፍበት ዓላማ አለው። ከተጻፈው ታሪክ አንባብያን ትምህርት በማግኘት የራሳቸውን ሰብእና ለመገንባት እንዲረዳቸው ታስቦ ይጻፋል። ለምሳሌ የአፄ ቴዎድሮስ፣ የንግሥት ዘውዲቱ፣ የበላይ ዘለቀ፣ የአብርሃም ደቦጭ፣ የሞገስ አስገዶም፣ የአብዲሳ አጋ የሕይወት ታሪኮች በተለያዩ ጸሐፊዎች ተጽፈው ለንባብ ስለበቁ አስተማሪነታቸው የጎላ ነው።

የሕይወት ታሪካቸው የሚጻፍላቸው ግለሰቦች ታሪካቸው ወጣቱን ትውልድ ለማስተማር ይረዳል የተባሉት ብቻ መሆን ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፣ በአንድ ሀገር የሚገኙ ስመጥር ያገር መሪዎች፣ እውቅ ተመራማሪዎች፣ ሳይንቲስቶችና ጀግኖች የሀገሪቱ ሀብትና ቅርስ በመሆናቸው ታሪካቸው ተጽፎ ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ይገባል።

## 1ኛ ቀን



### ማዳመጥ

**የክብር ዶክተር ደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክ**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በጽሑፍ ግለጹ፡፡

ሀ. "ድርሰት" ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ሐዲስ ዓለማየሁ የሚታወቁት በምንድን ነው?

### ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ፡፡

ሀ. ደራሲ　　ለ. አርአያነት

### ማጣመርና መነጠል

ሀ. የሚከተሉትን ባለቅጥያ ቃላት ዋና ቃላቱንና ቅጥያዎችን ነጣጥላችሁ ጻፉ፡፡

1. ስለትምህርትቤታችን　　3. ከናንተ
2. እንደሥራህ　　4. ከገበሬዎች

ለ. በ "ሀ" ክፍል የሚገኙትን ተጠማሪ ቃላት በ "ለ" ክፍል ከሚገኙት ተጠማሪያቸው ጋር በማዛመድ ጥምር ቃላትን መሥርቱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እንጀራ ________ | ሀ. አደር |
| 2. ኩታ ________ | ለ. ገጠም |
| 3. ሠርቶ ________ | ሐ. አባት |
| 4. ውሃ ________ | መ. ገብ |
| 5. ውሎ ________ | ሠ. አዳሪ |

## 2ኛ ቀን

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ርእሱ ስለምን የሚያስረዳ ይመስላችኋል?

ለ. የሕይወት ታሪክ ጸሐፊዎች ጽሑፉን ሲያዘጋጁ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ፡፡

ሀ. የማንኛውም ሰው የሕይወት ታሪክ የማይጻፈው ለምንድን ነው?

ለ. የሕይወት ታሪክ ዋና ዓላማ ምንድን ነው?

## ቃላት

1. የሚከተሉትን ቃላት ፍቻቸውን በፅሁፍ ግለጹ፡፡

ሀ. ታሪክ  ለ. ልደት  ሐ. እድገት  መ. ገጠመኝ  ሠ. ገና

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ ባላቸው ዐውድ መሠረት ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ሀ. ተጨባጭ  ሐ. ምክንያት  ሠ. እንዲሸጋገር

ለ. ልቦለድ  መ. ባለዝና  ረ. ተጽፈው

## መጻፍ

በቡድን ሆናችሁ፣ በአካባቢያችሁ ያሉ አንድ ታዋቂ ሰው መርጣችሁ የሕይወት ታሪካቸውን ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# 3ኛ ቀን

## ማዳመጥ

### የደራሲ ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክ

## ቃላት

በሳጥኑ ውስጥ ካሉት ቃላት በመምረጥ ዓረፍተነገሮችን አሟሉ፡፡

| ወረራ፣ ዐብይ፣ ህያው፣ ዋስትና፣ ማበርከት |
| --- |

ሀ. የድርሰት ________ ተግባር ማስተማርና ማዝናናት ነው፡፡

ለ. የደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁ ሥራዎች ለዘላለም ________ ናቸው፡፡

ሐ. ሁሉም ሀገሩን ለማሳደግ የበኩሉን አስተዋጽ የ ________ አለበት፡፡

መ. ሰዎች የኑሯቸውን ________ በሥራ አረጋገጡ፡፡

ሠ. ባለታሪኩ የጣሊያንን ________ በመመከት ተሳትፈዋል፡፡

## ማጣመር

1. የሚከተሉትን ቃላትና ቅጥያዎች አጣምራችሁ ባለቅጥያ ቃላት መሥር

ሀ. ፈሊጥ - ኣዊ  ለ. ደረት -ኣም  ሐ. አስማት -ኧኛ  መ. እሾህ - ኣማ

2. የሚከተሉትን ጥንድ ጥንድ ዓረፍተነገሮች በማጣመር በአንድ ዓረፍተነገር ግለጿቸው::

ሀ. ንቧ አበባ ቀሰመች:: ንቧ ማር ሠራች::

ለ. ተክሎች ውሃ አገኙ:: ተክሎች በጥሩ ሁኔታ ጸደቁ::

ሐ. ዝናቡ ዘነበ:: ገበሬው ማሳውን ማረስ ጀመረ::

## 4ኛ ቀን

### ማንበብ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሶችን በጽሑፍ ስጡ::

ሀ. "የሕይወት ታሪክ የፈጠራ ጽሑፍ አይደለም" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. የፈጠራ ጽሑፍ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ ግለጹ::

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሶችን በጽሑፍ ስጡ::

ሀ. የመጨረሻውን አንቀጽ ሀሳብ በአንድ ዓረፍተነገር ለጓደኞቻችሁ ግለጹ::

ለ. የምንባቡን ዋና ሐሳብ በሦስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ?

### ቃላት

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገሮችን ሥሩ::

ሀ. ሥነጽሑፍ ለ. ህልውና ሐ. አሳማኝ መ. ተመራማሪ

2. በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ጥምር ቃላት ከ "ለ" ረድፍ ካሉት ፍቻቸው ጋር መርጣችሁ አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሆደባሻ | ሀ. ጠበቃ |
| 2. ነገረፈጅ | ለ. እርጉዝ |
| 3. ነፍሰጡር | ሐ. የመስኖ መሬት |
| 4. ደመግቡ | መ. ድንበርተኛ |
| 5. ውሃገብ | ሠ. መልከ መልካም |
| 6. ኩታገጠም | ረ. ቶሎ የሚቀየም |

### መጻፍ

ስለደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁ የተረዳችሁትን በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ::